


ከበዓሉ ግርማ

t.me/pdfbookscloud

# የቀይ ኮከብ ጥሪ

ከበዓሉ ግርማ

መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው።
© All Rights Reserved

መጀመሪያ እትም 1972 ዓ.ም
ሁለተኛ እትም 1999 ዓ.ም
ሦስተኛ እትም 2000 ዓ.ም
አራተኛ እትም 2010 ዓ.ም

በማንኩሳ ማተሚያ ቤት ታተመ

## ማሳሰቢያ

ይህ መጽሐፍ ልብወለድ ነው፡፡ በታሪኩ ውስጥ የተከሰቱት ባለታሪኮች (ገፀ - ባህርያት) ሁሉ ደራሲው የፈጠራቸው ናቸው፡፡ ባለ ታሪኮቹ በህይወት ከነበሩ፥ ወይም አሁን ካሉ ሰዎች ጋር ምንም አይነት ግንኙነት የላቸውም፡፡ የስም ወይም የባህርይ ተመሳሳይነት ያለ ቢመስል፥ የአጋጣሚ ነገር መሆኑን አንባብያን በቅድሚያ እንዲረዱልኝ እወዳለሁ፡፡

ደራሲው

# ምእራፍ ፩

ሰአት እላፊ የተቃረበ ቢሆንም፥ አዲስ አበባ እንደ ወትሮዋ በስልቹነት አዛግታ ከእንቅልፍ አዘቅት ውስጥ አልተጋደመችም። የውድቅቱ ጨለማ ሰላሙን አጥቶአል። በድቦችና በመንደር ውሾች ህብረ-ጩኸት ፈንታ የሽጉጥ፥ የመትረየስና የዲሞትፎር ተኩስ ጨለማውን እየሰነጠቀ ያስተጋባል - እንቅልፍ ነስቶ ሆድ እያሸበረ። በየቤቱ እንቅልፍ ያልዞረበት አይን አፍጥጦ ጣራ ጣራውን ይዳስሳል። ባሩድ የሸተታት ሚዳቋዋ ይመስል የሁሉም ጆሮ ተስሎ ቁሞአል።

ወይዘሮ አምሳለ እንደ ልማዳቸው ምሽቱ ሳይገፋ በጊዜ፥ ሁለት ብርጭቆ የአጃ አጥሚታቸውን ጠጥተው፥ ለጋ ቅቤአቸውን በሰርናቸው አንቆርቁረውና እንደ ጨረቃ ክብ የሆነች ትንሽ ፊታቸውን በቀዝቃዛ ወተት ከወለወሉ በሁዋላ፥ ከፊታቸው ላይ ጤዛ መስሎ የሚያብረቀርቅ ቅባት ተቀብተው ሲያበቁ፥ ሻሻቸውን እስከ ጆሮ ግንዳቸው ድረስ ዝርገድ አድርገው አልጋ ላይ ከወጡ የቆዩ ቢሆንም፥ እንደ ፈርጥ በሚንቦገቦገው ትላልቅ አይናቸው እንቅልፍ የሚሉት ጣእመ ነገር ከቶውንም አልዞረም። እንደ ጉርድ በርሜል ከአልጋ ውስጥ ይገላበጣሉ።

አቶ ጉልላትም እንደ ባለቤታቸው እንደ ወይዘሮ አምሳለ እንቅልፍ አጥተው በመቸገር፥ ስንደዶ የመሰለ አፍንጫቸውን ከአንሶላው ብቅ አድርገው፥ ወርዝቶ የሚታየውን መላጣቸውን እያብለጨለጩ፥ እንደ ጉድጉዋድ ውኃ ወደ ውስጥ የራቁትን አይኖቻቸውን ብልጭ ድርግም ያደርጋሉ፤ ወፍራም ሰውነታቸው አባይ ይዞት እንደሚሄድ ግንድ ከአልጋው ውስጥ ይገላበጣል።

‹‹ራዲዮውን አጥፋው! ይህን ራዲዮ የት አባቱ ወስጄ ልጣለው!›› አሉ ወይዘሮ አምሳለ፥ ተበሳጭተው።

‹‹ምን አገኘብታለሁ ብለህ ነው ይህን ራዲዮ ጠዋት ማታ የምትጎረጉረው?››

«ወሬ—ስለ አገራችን የጊዜው ሁኔታ! የኛ ራዲዮ ጣቢያ እንደሆን ከስድብ ሌላ ወሬ የለው! ትክክለኛ ወሬ የሚገኘው ከቢቢሲ፥ ከጀርመን ራዲዮ ጣቢያ፥ ከዶቼቬሌ፥ ከቮይስ ኦፍ አሜሪካ፥ ከሞቃዲሾ ራዲዮ ጣቢያ ነው. . .»

«ለወሬ የለው ፍሬ እቴ! ይልቅ አታደንቁረኝ — አጥፋው!» አሉ ወይዘሮ አምሳለ።

አቶ ጉልላት ሳይወዱ በግድ ቀና ብለው ራዲዮኑን አጠፉ። ከውጭ ራዲዮ ጣቢያ መለየት ፈፅሞ ደስ አይላቸውም። ከጣቢያ ጣቢያ እያማረጡ እሱኑ ሲጎረጉሩ ነበር የሚውሉት።

ራዲዮው ዝም ሲልባቸው ጊዜ፥ አቶ ጉልላት ከሩቅና ከቅርብ የሚሰማውን ተኩስ የምን አይነት መሳሪያ እንደሆነ በልባቸው ይገምቱ ጀመር።

ኩዋ! ኩዋ! ኩዋ! — ሽጉጥ።

ካካካካ! ካካካካ! — መትረየስ።

ዱዋ! ዱዋ! ዱዋ! ዱዋ! ዱዋ! — ዲሞትፎር።

«የመላኩ ያለህ! ይሄኛውስ እዚሁ ቤታችን አጠገብ ነው! ለመሆኑ የውጭው በር በደንብ ተዘግቶአል?»

«ስንቴ ልንገር!»

«አታመናጭቂኝ እንጂ! አሁንስ ከቀበሌ ተኩስ ባሰብኝ ምላስሽ! ሆድ ለባሰው ማጭድ አታውስው ይላል አማራ – እ።»

«ታዲያ ስንቴ መልስ ልስጥህ?! ከተጠራጠሩ ሂዶ ማየት ነው! ደርቤ–ስሙን ቄስ ይጥራው እቴ! በሄደ በስንት ጊዜው! ይህን ሰሞን ደሞ ዝም ብሎ አፌ ይገባል አስር አስር ጊዜ። – ስንታየሁ ነው በጊዜ በሩን የዘጋው» አሉ፥ እየተመናጨቁ።

ደርቤ፥ ከህፃንነት ጀምሮ አቶ ጉልላት ቤት ውስጥ በአሽከርነት ሲያገለግል ከቆየ በሁዋላ፥ አብዮቱ ከፈነዳ ወዲህ በሰላም ከቤታቸው ወጥቶ፥ በአቶ ጉልላት አማላጅነት በማስታወቂያና መርሀ ብሄር ሚኒስቴር ውስጥ ስራ ከያዘ ሁለት ዓመት አልፎት ነበር። ወይዘሮ አምሳለ ካዩት ሰንበት ብሎአል። ሰሞኑን ስሙ

እየመጣ ከአፋቸው ለምን እንደሚገባ ሊከሰትላቸው አልቻለም። ከቤታቸው ውስጥ በአሽከርነት በቆየበት ዘመን፥ በተፈነቱና በታማኝነቱ በጣም ይወዱት ስለነበረ፥ በተቆጡና በተበሳጩ ቁጥር ወይም አንድ ነገር ባስቸኳዋይ በፈለጉ ቁጥር፥ በመጀመሪያ የሚታያቸውና ስሙ አፋቸው የሚገባው ደርቤ ነበር። በአሳባቸው «ለዚህ ይሆን?» ብለው ዝም አሉ።

«እህ... እንቅልፍ አጥተሽ ነው መሰለኝ የምትነጫነጪው...»

«ኤዲያ! ሽዋዬ ይሙት – የሰውን ስሜት የማያውቅ ሰው ደስ አይለኝም። አውሬነት ነው» አሉና ወይዘሮ አምሳሉ፥ ተቆጥተው በመገላበጥ ጀርባቸውን አዞሩ።

አቶ ጉልላት የእሜቴን ስሜት አላጤኑም። እሳቸው ለራሳቸው ጆሮአቸው ቆሞ፥ ትናንሽ አይኖቻቸው ፈጥጠው፥ በሞራ ተሸፍኖ የደከመ ልባቸው ትር ትር እያለ፥ ከጨለማው በላይ ነግሶ የሚያስተጋባውን የተኩስ ጋጋታ በፍርሃት ያዳምጡ ነበር።

«ልጆቹ ደህና እንደሆኑ እስቲ ስልክ ደውለሽ ጠይቂ!» ብለው አዘዙ።

«ስንቴ ልደውል?!»

«ግድ የለሽም እንደ ገና ደውይ። የሚሰማኝ አጣሁ እንጂ እኔማ ሱቅ እንዳያድሩ ብዬ ነበር።»

«ወይ አበሳዬ» እያሉ ጉርድ በርሜል መሳይ ገላቸውን ጎትተው በመነሳት፥ ስልክ መደወል ጀመሩ። ከአጭር ቁመናቸው በላይ ጎልተው የሚታዩት ትላልቅ ጡቶቻቸው ነበሩ። እንደ ሱቅ በደረቱ የተሸከሙት ጡት የገዛ ጡታቸው አይመስልም፤ ህፃናት የሚጫወቱበትን የገና ላስቲክ ነፍተው በለሊት ልብሳቸው ውስጥ የከተቱት እንጂ! ከብዙ ዘመን ሙከራ በሁዋላ በስንት መከራ ቀለሙ ደብዘዝ እንዲል የተደረገው ንቅሳታቸው ከአጭር አንገታቸው ላይ ይታያል። ወደ ላይ ፍንድር ያለው ትልቅ ቂጣቸው፥ እንደ እርጉዝ ሴት ወደ ፊት ገፍቶ የተንጠለጠለው ሆዳቸውና ትንሽ ክብ ፊታቸው በአንድነት ሲታዩ፥ አሻንጉሊት ያስመስሉአቸዋል።

‹‹ተኝተዋል መሰለኝ ስልኩን አያነሱም፡፡ እሉ፥ ማዳመጫውን ከጆሮ ግንዳቸው ላይ አጣብቀው፡፡

‹‹የምን እንቅልፍ – በዚህ ሁሉ ተኩስ መሀል? የለም አንድ ነገር ቢሆን ነው!››

ወይዘሮ አምሳለ ስልኩን ዘጉ፡፡ አቶ ጉልላት ከወገባቸው ቀና ብለው ተቀመጡና፥ ‹‹እዚያ ሉቅ እንዳያድሩ ብዬ ነበር – ›› ከማለታቸው፥ ወይዘሮ አምሳለ ለጥቀው፥ ‹‹ከሰሙህ አትነግራቸውም ኖሮአል? ለወጉ አባት ነህ፡፡ እኔን እንደሁ ከመጤፍም አይቆጥሩኝ፡፡ኸረ – ኤዲያ! ባለጌን ካሳደገ የገደለ ይሻላል፡፡ ተሰማ እንደሆነ ጠጉሩን አጎፍሮ ጢሙን ማሳደግ ከጀመረ ወዲህ አንደኛውን መረን ወጥቶአል፡፡ ቁመቱ ረዝሞ ከመገርጀፉ የጢሙ ማስጠላት! እኔ ማዝነው በሂሩቴ ነው፡፡ እንደ አይን ጠፍታለች፡፡ ሽቶውን፥ ልብሱን፥ ጫማውን ከየት እንደምታመጣው አላውቅም፡፡ የት ውላ እንደምትመጣ የሚያውቅ የለም፡፡ ሲጠይቁዋት ‹‹ኡፋ!›› ብላ በሩን ወርውራ ትወጣለች፡፡ በር ዘግታ የምትንሾካሾከው ከወንድምዋና ጠርብ ጠርብ ከሚያካክሉ – ትከሻቸው ካበጠ – ማንንም ከመጤፍ ከማይቆጥሩ ያጎፈሩ ጎረምሶች ጋር ነው፡፡ እኔ አላውቅም፡፡ በነሱ ምክንያት ቆሽቴ የሚደብንበት ምክንያት የለም፡፡ የነሱ ነገር በቅቶኛል›› ብለው በረጅሙ ተነፈሱ – በአንድ አፍታ ለተሰማ ጢም ያላቸው ጥላቻ በልባቸው ውስጥ ነፍስ ዘርቶ እየተንቀሳቀሰ፡፡

የተሰማ ቁመት መርዘምና የጢሙ መንዠርገግ – ዳዋ እንደ በላው የሰነፍ ገበሬ ማሳ – በጣም ስለሚያስቆጣቸው፥ ‹‹ልጄ ነው›› ብለው ለሰው ማስተዋወቅ ከተው ውለው አድረዋል፡፡ ከታናሽ ወንድማቸው ከጌታቸው ጋር መታየትም ካቆሙ ዘመን የላቸውም–ከርሱ ጋር መታየት ያንን የሚጠሉትን እድሜ አስታውሶ ስለሚያሳጣቸው፡፡ የውስጥ አዋቂ! ወንድምዎ ሸብቶአል! ሲላቸው፥ ‹‹ያለ እድሜው ነው የሸበተው፡፡ አንድ ፍሬ ልጅ ነው እኮ፡፡ ሽበት የዘራችን ነው›› ይላሉ፡፡

ስለ ራሳቸውም ቢሆን፥ ‹‹እህህ! እኔኮ ልጅ ነኝ፡፡ አንድ ፍሬ ልጅ ሁኜ ነው ያገባሁት፥ ገና በአስራ ሁለት አመቴ!›› እያሉ መኩነስነስ ስለሚያዘወትሩ

የእድሜ እኩዮቻቸው፥ «ማሚቱ መጣች!» እያለ ስለሚያሾፉባቸውና፥ ወጣት ሴቶችም – ሊመስሉአቸው በሚጠጉዋቸው ጊዜ – «እማማ» እያሉ ስለሚጠሩዋቸው፥ ዛፍ ያጣ ጉሬዛ ሆነው እያዘኑ ይበሳጫሉ – እድሜአቸው እንደ ጥላ እየኮበለለ ሲሄድ፥ ግንባራቸው ላይ በቀዝቃዛ ስውር እጁ አርሶ ያለፈውን ፈር አንድ በአንድ ቆጥረው የቀይ ኮከብ ጥሪ እየተመለከቱ።

አቶ ጉልላት ተክዘው እየተፈላሰፉ፥ «ውሉ ጠፍቶ ከስሩ የተናጋ ህይወት። ወልዶ አሳድጎ ባእድ መሆን። ከጊዜው ነው ከሌላ አይደለም» አሉ፥ ለሚስታቸው ሳይሆን ለራሳቸው ጆሮ እያጉረመረሙ። ጥቂት አሰቡና፥ «ታዲያ አሁን ምን ይሻላል?» ብለው ጠየቁ።

«ምኑን?»

«ልጆቹን ነዋ!»

«የሚሻለውማ መተኛት ነው! ሌላ ምን ማድረግ ይቻላል?»

«እስቲ ደሞ ጌታቸው ቤት ደውዪ። መቼም ይሄኔ እንደ ልማዱ ስክሮ ተኝቶ ይሆናል።

«የሱ ስካር ምኑ ቅጡ። ደሞዙን ሁሉ አንድ ሳንቲም ሳያስቀር ይጠጣበታል። ሚስቱ በቁመናዋ መንምና እየሞተች ነው—በስጋት። ያ ማስታወቂያ ሚኒስቴር–አሁን ደሞ ምን ብለውታል ልጄ–እዎን መርሀ ብሄር ሚኒስቴር–ምን እንዳስነካው አላውቅም!» ብለው የጌታቸውን መንማና ሰውነትና ሸበት፥ የሚስቱን ከሰውነት መውጣትና ዘወትር ማልቀስ በአይነ ህሊናቸው እየቀረፁ፥ ስልኩን ደወሉ። ስልኩን ያነሳችው የጌታቸው ባለቤት ትእግስት ነበረች። የተለመደውን ሰላምታ ከተለዋወጡ በሁዋላ፥ «ምን ነው ይተናነቅሻል? ታለቅሺያለሽ እንዴ? ደህናም አይደላችሁ? ምን ሁናችሁአል?» በማለት ጥያቄን በጥያቄ ላይ እየደራረቡ፥ ቁርጥ ቁርጥ ባለ ትንፋሽ ጠየቁዋት።

«ደህና ነን። የለም አላለቀስኩም። አልቅሼ ምን ልሆን?» ብላ በጎረና ድምፅ መልስ ስትሰጥ ትሰማለች–ትእግስት–እየተነፋነፈች።

‹‹የኢዮብን ትእግስት ነው የሰጠሽ ልጄ፡፡ ስምን መልአክ ያወጣዋል አሉ፡፡ ፊቴ ባትሆኝም እንባሽ ይታየኛል፡፡ ለመሆኑ ስፈራችሁ እንዴት ነው?››

‹‹ተኩሱ ይቀልጣል፡፡ በጣም ያስፈራል፡፡ ሰግቼ ወደ እርስዎ ልደውል ስል ነው ለትንሽ የቀደሙኝ...››

‹‹እኛም ዘንድ ተኩሱ እንደ በረዶ ይወርዳል፡፡ ከመጣው መአት እግዜር ይሰውረን ማለት ነው እንጂ ተኩሱስ አይጣል ነው፡፡ ለመሆኑ ጌቱ እንዴት ነው?››

‹‹ተኝቶአል... እንቅልፍ አልወሰደውም... ግን መነሳት አይችልም– ልታነጋግሩት ፈልገሁ እንደሆን?››

‹‹ተኝቶ እየጠጣ ነው?››

‹‹ይመስለኛል፡፡››

‹‹ለምን መጠጡን አትቀሚውም?››

‹‹በምን አቅሜ? ይግደለኝ ብለሁ ነው?››

‹‹እርሱ የሞተ እንደሁ? ሁዋላ እንደ ጲላጦስ እጅ መታጠብ ይቻላል?›› አሉዋት፣ የስጋ ጉዳይ አላስችል ብሉአቸው፡፡ ወዲያውኑ መለስ ብለው፣ ትእግስትንም ላለማስቀየም፣ ‹‹ዳሩ ምን ታደርጊ ልጄ! አበሳ ነው፡፡ የሰው ነገር አይቀበል – ቢመክሩት አይሰማ! ጠርሙስን የሙጥኝ ብሎ መሞት – በቤታችን እንኩዋን የለ! ልክፍት ነው፡፡ እዚያ ማስታወቂያ ሚኒስቴር ያቀመሱት ነገር ይኖራል፡፡ ለመሆኑ መቼ ነው የተኛው?››

‹‹ሶስት ቀን ሆኖታል፡፡ ስራም አይሄድ፡፡ ከመስሪያ ቤቱም ይደውላሉ፡፡ በር ዘግቶ ዝም ይላል...››

‹‹ያው እንደ ልማዱ ከጠርሙስ ጋር ሱባኤ ገብቶአል በይኛ! የተጠናወተው ሰይጣን አለ–ሌላም አይደል፡፡ ያዳቆነ ሰይጣን ሳያቀስ አይለቅም አሉ፡፡ ይኸው ነው መሞቻው›› አሉ፣ አዝነው ሆዳቸውን ባር ባር እያላቸው፡፡

‹‹አባባ ደህና ናቸው?››

የቀይ ኮከብ ጥሪ

ዱዋ! ዱዋ! ዱዋ! ዱዋ! ዱዋ!

‹‹የመላኩ ያለህ! ዛሬስ አላሳደሩንም! ጥይቱስ አያልቅባቸውም እንዴ?››

‹‹ምነው አርፈህ ብትተኛ – ጉልላቴ›› ብለው አሁንም ጠጋ አሉ፥ ወይዘሮ አምሳለ።

አቶ ጉልላት የሸቶው መልእክት አልደረሳቸውም – ሀሳባቸውን በሙሉ የውጭው ተኩስና የውስጣቸው መፈላሰፍ ይዞታል።

‹‹እንዲያው!. . . አዬዬ! ጉድና ጅራት ከወደሁዋላ!›› አሉ። ‹‹እነዚያን መሳሪያዎች የሰም እናስረክብ ስልሽ ቅበር ባትይኝ ምን ነበረበት!›› አሉ፥ እያቃሰቱ።

ወይዘሮ አምሳለ እንደ ቆሰለ አውሬ ተቆጥተው ከተጋደሙበት ብድግ አሉ። የብስጭትና የማፈር ስሜት የሚፈራረቅበት መልክ ከኮብ ትንሽ ፊታቸው ላይ ይነበብ ነበር። ‹‹ተነስተህ ሄደህ አስረክባ! ማስረከብ ልማዳችሁ ነው!›› አሉ፥ ከጣራው በላይ በነገሰና ስልቱን በሳተ ድምፅ።

‹‹ምን የማስረከብ ልማድ ነው የምትይኝ!››

‹‹ሁሉን!›› አሉ፥ ሻሻቸውን እያስተካከሉ።

‹‹እኮ እኛ እነማን ነን – ልማዳችሁ ነው ስትይ?››

‹‹ሁላችሁም! ሁላችሁም! ! እየነው ጉዱን እቴ!››

‹‹የቱን ጉድ?››

‹‹የወኔን መሞት ጉድ አልኩህ! ይገባህ እንደሆን? የሰው ስሜት የማይገባው ሰው በድን ነው። ወንዶች ስትባሉ ወኔ አልባ በድን ሁናችሁአል!››

‹‹የመሳሪያውን ነገር ስላነሳሁ አሁን ይህ ሁሉ ውርጅብኝ ያስፈልጋል?››

‹‹ሄደህ አስረክብ አልኩህ! ራስ ደጃዝማቹ ሁሉ አስረክበዋል – እጅን ጭምር። ከጦር ኃይሎች ከፖሊስ ሰራዊትና ከብሄራዊ ጦር አስተባባሪ ኮሚቴ የተሰጠ መግለጫ!››

‹‹አበድሽ እንዴ!››

‹‹ኦ ሆ ሆ ሆ! . . . ጉዱን አየነው እቴ! ራስ እገሌ–ደጃዝማች እገሌ – ጄኔራል – ክቡር አቶ እገሌ–ለባሬ ስምንት ሰአት ጀምሮ አራተኛ ክፍለ ጦር ድረስ መጥተው እጃቸውን እንዲሰጡ፥ በተባለው ሰአት መጥተው እጃቸውን ባይሰጡ ቤት ንብረታቸው እንዲወረስ የተወሰነ መሆኑን እናስታውቃለን! ካደፈጠበት መጥቶ ‹‹መጣን፥ እዚህ ደርሰናል›› እያለ እጁን ያልሰጠ ማን ነበር?››

መድፉ ሳይተኮስ ቦምቡ ሳይፈነዱ
ያ ሁሉ መኩዋንንት እንደ በግ ተነዱ

‹‹አንተም ሂድ መሳሪያህን አስረክብ!››

‹‹አብደሻል መሰለኝ››

‹‹ሲያልፍም አይነካኝ!››

‹‹እንግዲያውስ በውድቅት ጨለማ ሙት ወቃሽ አትሁኝ!››

‹‹ሙት ወቃሽ አልከኝ? እውነትም ሙት ወቃሽ! የወንድ ያለህ ነው የምለው፥ አልገባህም እንጂ! አህሀሀ! – ንጉሱን ከስልጣን ለማውረድ የወጣ አዋጅ! ቁጥር አንድ አዝባር ምን ነበር እቴ? ከዛሬ መስከረም ሁለት ፲፱፻፷፯ ዓ.ም. ጀምሮ ንጉሱ ከስልጣን ወርደዋል – ጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ! ንጉሱ ተጎትቶ ሲሄድ እንዲት ውሻ ብቻ አስከትሎ–አየነው ጉዱን እቴ! ንጉሱ ከተነኩ ኢትዮጵያ የእምቡዋይ ካብ ትሆናለች – አገሪትዋ በደም ትዋኛለች–ምድር ቀውጢ ትሆናለች – ብርሃን ይጨልማል፤ ተብሎ እንዳልተፎከረ ሁሉ!! ‹‹ዋይ ዋይ ንጉሱ፥ ከእንግዲህ ቀረ በዘር መንገሱ::!!›› እየተባለ ሲዘፈን፥ ‹‹አቤት! አቤት! እግዚኦ›› ከማለት ሌላ ጣቱን እንኩዋን ያነሳ ወንድ አላየንም!››

‹‹በአማላጂትዋ ተይኝ ነው የምልሽ – አንቺ ሴት!››

‹‹የገጠርን መሬት የህዝብ ለማድረግ የወጣ አዋጅ!››

‹‹እብደት ነው የያዘሽ! ጨርሶ እብደት ነው!››

ነበር – አብዮት የሚሉት ጣጣ ባይመጣ ኖሮ!›› በማለት ለመጀመርያ ጊዜ ክፉኛ ተቆጩ። ራሳቸውንም ታዘቡት። የህይወት ጥምባት ሸተታቸው። ክርፋት ክርፋት አላቸው። ሞገድ እያንገላታት መልህቋዋን የምትጥልበት ያጣች መርከብ ይመስል ልባቸው ተንሳፈፈ።

ሁለቱም እንቅልፍ ሊወስዳቸው አልቻለም – ወይዘሮ አምሳለ ተናቅሁ ብለው እየተብከነከኑ – የሸቶአቸው መአዛ ራሳቸውን መልሶ በማወድ እያስጠላቸው – አቶ ጉልላት የቀበሌ ተኩስ እያስበረገጋቸው። ሲያጉዋራ ዲሞትፎሩ–ሰማዩ–ተገምሶ የወደቀ ይመስል ነበር። እንኩዋን የተኛን የሞተን ከመቃብር የሚቀሰቅስ ያህል ነበር የጥይቱ ዶፍ።

አቶ ጉልላት ከወይዘሮ አምሳለ ተለይተው ብርድ ከፍርሃት ጋር ተዳምሮ እያንቀጠቀጣቸው፥ ተጨንቆ ግሎ ጭንቅላታቸው ውሉ በጠፋ አሳብ – ‹‹ነጭ ሽብር! ቀይ ሽብር! የመደብ ትግል! አድሃሪ፥ ተራማጅ ብሎ ነገር፥ ሽብር! ሽብር! ሽብር! የመደብ ትግል እያሉ አገር ባይበጠብጡ፥ የማንም አፈር ገፊ፥ የፈጫይና የእንጨት ሰባሪ ልጅ ሁላ ከመሬት ተነስቶ አገር ያቀና፥ ያስተዳድር ይመስል–ከእንጨት ተመርጦ ለታቦት፥ ከሰው ታጭቶ ለሹመት መሆኑን እረስተው!. . .›› ‹‹ጨዋ የጨዋ ልጅ እንደ አውሬ እየታደነ. . . እህህ . . . የራሄል ጩኸት–የናቡከደነፆር ህልም–ስምንተኛው ሽህ. . .››

ኩዋ! ኩዋ! ኩዋ! – ሽጉጥ።

ክክክክክክ–መትረየስ።

ዱዋ ዱዋ–ዲሞትፎር።

‹‹የመላኩ ያለህ! የሉቃስ ወንጌል ጩርሶት የለ? – ህዝብ በህዝብ ላይ፥ መንግስትም በመንግስት ላይ ይነሳል. . .ታላቅም የምድር መናወጥ በልዩ ልዩ ስፍራ–ቸነፈር ረሀብም ይሆናል. . .››

ኩዋ! ኩዋ! ሽጉጥ።

ዱዋ! ዱዋ! ዱዋ! ዲሞትፎር።

‹‹የመላኩ ያለህ! ምዕአት ለጨዋ ልጅ! አድሃሪ እያሉ! የናሁከደነዖር ሀልም. . . የሽክላ እግር. . . የሽክላ እግር!›› እያሉ እንቅልፍ ሸለብ እንዳደረጋቸው ቀን በጥላቻ የሰሙዋቸው የአብዮት ጥበቃ ጉዋዶች መፈክሮች –

‹‹አድሃሪያን በሰፊ ህዝብ ክንድ ይደመሰሳሉ!

በአድሃርያን ላይ ቀይ ሽብር ይፋፋማል!

ዲሞን በዲሞትፎር!

ነጭ ሽብር በቀይ ሽብር ይመታል!

ቀይ ሽብር የአብዮቱ አለኝታ ነው!

ነው! ነው! ነው!››

መጥተው በጆሮአቸው ውስጥ እንደ ምዕአት ደወል እያስተጋቡ፥ ሁሉም ግራ እጁን አንስቶ ወደ እርሳቸው ጥርሱን እንደ ሲኦል ጋሻ ጃግሬ አግጦ እያንቀጫቀጨ ሲጠጋቸው በአይነ ህሊናቸው እየታያቸው ወባ እንደ ያዘው ሰው ሰውነታቸው በሙሉ በላብ ተጠምቆ ሳለ፥ እየበረዳቸው በመባነን፡-

‹‹የመላኩ ያለህ! ጊዜ የማይወልደው ጉድ የለ! ጨዋ የጨዋ ልጅ ሞላጫ ድሀን ፈርቶ እየባነነ ሲያድር–እንደ ድኩላ ሰግቶ! ደሞ የቃላቱ ጋጋታ! ለጆሮ የማይጥም እንደ አባጨጉዋሬ የሚኮሰኩስ – ሻካራ! ፊውዳሊዝም – ቢሮክራሲያዊ ካፒታሊዝም – ኢምፔሪያሊዝም–ፊውዶ ቡርዧዋ– አናርኮ – ፋሺስት – ትሮትስካይት – ቀኝ መንገደኛ – ፊዲስት – የመደብ ጠላት – አድሃሪ ብሎ ነገር! በማናውቀው ቋዋንቋዋ መቀባጠር – የባቤል ግንብ – ማን ምን እንደሚናገር ሲጠፋ ሁዋላ ሲናድ እንደ እንቢዋይ ካብ–››

ኩዋ! ኩዋ! ኩዋ!

ከከከከከ! – ከከከከከ!

ዱዋ! ዱዋ! ዱዋ!

‹‹የመላኩ ያለህ! ዛሬስ አምረዋል እነዚህ ቀበሌዎች:: እህህ ሆሆሆ! ጉድ ነው ኮ! ኢድህ - ኢ.ህ.አ.ፓ-ኢ. ኤል. ኤፍ. ፒ.ኤል. ኤፍ–ስልዋህድ . ኢምፔሪያሊስቶች – አድሃሪ የአረብ ገዥ መደቦች – ቀኝ መንገደኞች – ጠባብ ብሄረተኞች – የብሄር ትምክህተኞች–ሰርጎ ገቦች–የተራማጅ ካባ ለባሾች– የቀብር ባህታውያን–ቢሮክራቶች–አድሃሪዎች–ሰላም የሌለው ሰላም ላይሰጥ! ፈሪ ላመሉ ጥላውን ሲጠራጠር! የፈሪ ዱላ መብዛቱ? ‹‹እናሸንፋለን! እናሸንፋለን! ድንቁም ታሸንፋለች!

‹‹ደሞ አዲሶቹ አማልክት መብዛታቸው – ካርል ማርክስ–ኤንግልስ–ሌኒን! ያልተባረከ ትውልድ! አሽክላዎች! ከውኃ ላይ የሚሳፈፍ ኩበት – ከእበት ላይ የፈሉ ትሎች – አባይ እንደሚያገላብጠው ግንድ ማደሪያ የሌላቸው – ጉዶች – የምድር ጉዶች! ግና ምን ያደርጋል ድስት ጥዶ ማልቀስ፣ ቀድሞ ነበር እንጂ አልሞ መደቆስ! በፊት ቀረ:: ያንን ሽማግሌ እግዜር ይይለትና! እሱም ዙፋኑም ላይተርፋ አሳልፎ ሲሰጠን– እንደ ይሁዳ:: የይሁዳ አንበሳ– ትንቢት ነበር ለካ! ይዝፈኑብን – ይዝፈኑብን ጠዋት ማታ – የፍየል ወጠጤን - የፍየል ወጠጤ ትካሻው ያበጠ ልቡ ያበጠበት፣ እንዋጋ ብሎ ከነብር ላከበት:: የማትረባ ፍየል ዘጠኝ ትወልዳለች፣ ልጆችዋም ያልቃሉ እስዋም ትሞታለች– አይ ጉድ! የጊዜ ነገር! ጊዜና ሽርሙጣን ያመነ – ጉም የዘገነ!!›› እያሉ ሲገላበጡ፣ እንቅልፍ ማጣቱ አይናቸውን እያቃጠላቸው – ሌሊቱ እየረዘመባቸው ይሄድ ነበር. . . .

# ምእራፍ ፪

ለአነ አቶ ጉልላት ቀበሌ ተመራጮች ጊዜው ከንፍ አውጥቶ እንደ መብረር ያህል ነበር–ሲሮጥ–ሴኮንዶች ደቂቃዎችን እየወለዱ፥ ደቂቃዎች ሰአቶች እየተኩ ሲሄዱ። ወርዱ አስር ስፋቱ አስራ አምስት ሜትር በሆነው የቀበሌው አዳራሽ ውስጥ አስቸኳዋይ ስብሰባ ከጀመሩ ከአራት ሰአት በላይ ቢሆናቸው እንጂ አያንስም። ነገር ግን፥ የጊዜው ኮብላሉ መሄድ አልታወቃቸውም። የታወጀው ሰአት እላፊ የትና የት አልፎአል።

አስቸኳዋይ ስብሰባ የተደረገበት ዋና አላማ፥ በፊት የነበረውን የቀበሌውን የአብዮት ጥበቃ ሊቀ መንበር ትጥቅ አስፈትቶ ከስልጣን በማውረድ ከቁጥጥር ስር ለማዋልና፥ በምትኩ ሌላ የአብዮት ጥበቃ ሊቀ መንበር ለመምረጥ ነበር። አባሎቹ በሙሉ (በግምት አንድ ስድሳ ይሆናሉ) ወደ ስብሰባው አዳራሽ ሲገቡ በመካከላቸውም ፍፁም የመግባባት መንፈስ ስለነበረ፥ የቀሞውን የአብዮት ጥበቃ ሊቀ መንበር ሳያስበው በድንገት ይዘው ትጥቅ ለማስፈታትና ከቁጥጥር ስር ለማዋል ጊዜ አልፈጀባቸውም። ከፍርሃት የተነሳ እያንዳንዱ የቀበሌው ተመራጭ በሆዱ ይዞት የቆየው ጉዳይ ስለነበረ፥ ሁሉም ሲፈራ ሲቸር እንጂ ምንም በመካከላቸው አንድ አይነት የመግባባት መንፈስ በሰረፀበት ጊዜ ላንዳፍታ እንኳን ያመነታ አልተገኘም፤ ያመነታ ተመታ፤ ያልጠረጠረ ተመነጠረ የጊዜው ሁኔታ፥ ይልቁንም ሲያንታርካቸው የቆየውና ጊዜ ፈጅቶ ያንን ያህል ያስመሻቸው፥ በምትኩ ሌላ የአብዮት ጥበቃ ሊቀ መንበር የመምረጡ ጉዳይ ነበር።

እያንዳንዱ አባል ካለፈው መራራ ልምድ ባገኘው ትምህርት መሰረት ከሌላ የፍርሃት አዘቅት፥ ከሌላ የስጋት ኑሮ ወጥመድ ውስጥ ለመውደቅ እንዳልፈለገ ያስታውቃል። ስለሆነም፥ የፈጀውን ጊዜ ቢፈጅም ምርጫው በከፍተኛ ጥንቃቄ መካሄድ ነበረበት። የቸኮለ ማንም አልነበረም።

ላምን ተብሎ–ላለፉት ሶስት ወራት እስካለፉት ጥቂት ሰአቶች ድረስ፥ እያንዳንዱ የአብዮት ጥበቃ አባልም ሆነ የቀበሌው ሊቀመንበር፥ በቀድሞው የአብዮት ጥበቃ ሊቀ መንበር አምባገነን ተፅዕኖ ስር በታላቅ ፍርሃትና ስጋት ያሳለፉት እያንዳንድዋ የመከራ ደቂቃ ከአእምሮው ውስጥ አልወጣችም።

ከመካከላቸው ያች የመከራ ደቂቃ ገና ያላለፈች እየመሰለው፣ ከፉኛ የሚዘገንነውም ነበር። በዚያች ቀውጢ ሰአት ከመካከላቸው ወጥመድ እንደገባች አይጥ ለመኖር እየቃተተ፣ ሞት ሳይቀር ለህይወቱ እየሳሳ ሳይወድ በፍርሃት ለፈፀመው ድርጊት፣ ህሊናው ቆስሎ በመምገል ያልገለማው ማን ነበር? ማንም አልነበረም።

ከሊቀ መንበሩ ፊት ካለው ወደ አንድ ጎን ያጋደለ፣ ቀለሙ ይህ ነው ተብሎ ሊነገርለት ከማይችል አሮጌ ጠረጴዛ ላይ፣ አዲስ ክላሺን አጋድሞ፣ ከቀጭን ወገቡ ላይ፣ በግራ ጎኑ በኩል፣ ባለስውር ምላስ ኮልት ፴፰ ሽጉጥ ሽጦ የተቀመጠው የአስመራጭ ኮሚቴ ሊቀ መንበር፣ የተዘጋ ጉሮሮውን በትንፋሹ ጠራረገና፣ ቀልተው በሚታዩት ትላልቅ አይኖቹ ሁሉንም አንድ በአንድ ካማተረ በሁዋላ፣ ‹‹ጉዋዶች፣ እስካሁን ሰፋ ያለ ዲሞክራሲያዊ ውይይት አካሂደናል። ለምርጫ በእናንተው ጠቋሚነት የቀረቡትም ስድስት ጉዋዶች ስለ አቋዋማቸው አንድ ባንድ ገልፀውልናል። ጊዜውም እየሄደ ነው። ጭቁን እንደምትሰሙት ሁሉ ከውጭ የመደብ ትግሉ እየተጡዋጡዋፈ ነው። ወቅት! ሁሉ በየቦታው ዘብ መቆም አለበት። በዚህ ወሳኝና መራራ የትግል ስለዚህ ወደ ምርጫው እንድናመራ ቤቱን እጠይቃለሁ፣›› አለ፣ ሳይታወቀው በአንድ እጁ ከፊቱ የተጋደመውን ‹‹ክላሺን›› እንደ ህፃን ልጅ እየደባበሰ፣ ከግራና ከቀኙ ሁለት ሌሎች ሰዎች ተቀምጠዋል። አንዱ ግንባረ ፈጣጣ ሌላው ደግሞ አይነ ሸውራራ ብጤ ናቸው።

ቤቱ በሲጋራ ጢስ ታፍኖ ዛር የሚወርድበት የቃልቻ እልፍኝ አልመሰለም። ለላብ ተብሎ ከብብት ውስጥ የሚቀቡትም ቅባት ሆነ፣ ጊም ከተላጩ በሁዋላ የሚርከፈከፈው ሽቶ ክፍሉን አያውደውም። የኮሌታው ንጣት ከሩቅ አይን የሚስብ ሽሚዝ ከመኸርጎርጎሩ የተነሳ የሚያጥወለውል ክራባት፣ ባለፈው ምሽት በኤምባሲ ኮክቴል የቦዘነ አይን የሚሸፍን ጥቁር የፀሀይ መነፅር አይታይም።

አይን የሚወጋው ደግሞ፣ ኖራው ለቆ ምርጉ ያፈጠጠው ግድግዳ ብርሃንዋ የደበዘዘና ከረጂም ገመድ እርቃንዋን የተንጠለጠለች ባለሸሯ ሻማ አምፑል፣ ክራባት ያላነቀው አንገት፣ ለብዙ ጊዜ ምላጭ ያልጎበኘው ጊም ነበር።

አንዱ ከመካከላቸው ድምፁን ከፍ አድርጎ «ለጓጓብ» በማለት እጁን አወጣ። ሁሉም መለስ ብለው ተመለከቱት። እያንዳንዱ አባል ለማን ድምፁን እንደሚሰጥ በጥሞና ያሰላስል ነበርና ጆሮ የማይለንጥቀው ድምፁ አሸበራቸው። በድንገት ከተቀመጠበት ብድግ ብሎ፥ «በቀድሞው ሊቀመንበርኛ በግብረ አበሮቹ ላይ አብዮታዊ ፍርድ ሳንሰጥ ወደ ምርጫው መሄድ የለብንም። አንገብጋቢው ጥያቄ ፍርዱ ነው እንጂ ምርጫው አይደለም» አለና ተቀመጠ።

የአስመራጭ ኮሚቴው ሊቀ መንበር እንደመናደድ ብሎ፥ መጥረቢያ መሳይ ፊቱን በይበልጥ ሳለና፥ «የተሰነዘረው አሳብ ከደንብ ውጭ ነው» አለ። «ምርጫው ወይስ ፍርዱ የትኛው ይቅደም? በሚለው አሳብ ቅድም ቤቱ በሰፊው ሲከራከርበት ከቆየ በሁዋላ፥ ምርጫው ይቅደም ተብሎ በአብዛኛው ድምፅ ያለቀለት ጉዳይ ነው። ስለዚህ፥ አሁን ቤቱን እንደ ገና የምጠይቀው ወደ ድምፅ መስጠቱ ስነ ስርአት እንድናመራ ነው። በተስማማነው መሰረት ድምፅ አሰጣጡ በምስጢር ይሆናል። አሁን ድምፅ የምትሰጡበትን ወረቀት ማደል እንጀምራለን።»

ያች ወሳኝ ሰአት በመድረስዋ ድምፅ ለመስጠት ተቻኩሎ በታደለው ወረቀት ላይ የተጠየቀውን ምልክት ያደረገ አልነበርም። ግማሹ ውሀ እንደምትጠጣ ዶሮ ወደ ላይ አንጋጦ፥ የተቀረው ደግሞ አሳብ እንደተጫነው ፈላስፋ አቀርቅሮ ያስብ ነበር። የትናንቱ ፍርሃትና ጭንቀት እያንዳንዱ አእምሮ ውስጥ ትኩስ ነበር። ግን የትናንቱ ጥፋት፣ ያለፈው የፍርሃትና የመከራ ሰአት እንዳይደገም ዋስትናው ምንድር ነው? የሚልም ጥያቄ በአእምሮአቸው ውስጥ ሳይመላለስ አልቀረም። በትግል፥ ትግል ደግሞ ያለቆራጥነት አይሆንም የሚል መልስ ያገኙ ይመስላል። አብዛኛዎቹ ከታደላቸው ወረቀት ላይ ምልክት ማድረግ ጀመሩ። ለእርዳታ ወደ አስመራጭ ኮሚቴው ሊቀ መንበር የሄዱት ከአስር አይበልጡም ነበር።

ሁሉም ድምፅ የሰጠበትን ወረቀት መመለስ ጀመረ። በተጨማሪ ብቅ የሚል ሰው መጥፋቱን በማየት ሊቀመንበሩ ትንሽ ቆየና፥ «የምርጫውን ወረቀት ያልመለሰ አንዳለ?» ብሎ ፈገግ በማለት ጠየቀ። ሁሉም ተያዩ።

«እኔ ገና ነኝ» አለ፥ በድንገት ከመካከላቸው አንዱ።

‹‹ምንነው ጉዋድ?››

‹‹መቁረጥ አቃተኝ!››

‹‹ለምን?›› ብሎ ጠየቀ፥ ሊቀ መንበሩ እየሳቀ።

‹‹ድምፅ መስጠት እንደ ዋዛ የሚታይ አለመሆኑ ዛሬ ነው የተከሰተልኝ። እና ተጨነቅሁ›› አለ፥ ቁም ነገር በተመላበት ሁኔታ።

በአዎንታ ራሱን ያልነቀነቀ ሰው በቤቱ ውስጥ አልነበረም። ለማንኛውም ነገር መልስ የማያጣው ሊቀ መንበር፥ ከፊቱ ላይ የነበረውን ፈገግታ ሳያጨልም፥ ‹‹አዎን ጉዋድ፥ ድምፅ መስጠት አስቸጋሪ ነገር ነው። ጭንቀትህ የንቃት ምልክት ነው። ቢሆንም፥ ጊዜና ጠላት ቆመው አይጠብቁንም። ስለዚህ መቁረጥ ያስፈልጋል›› በማለት አበረታታው።

ጉዋዱ፥ በመረጠው እጩ ስም አኩዋያ ምልክቱን አድርጎ ወረቀቱን መለሰ። እንደ ድንጋይ ከብዶት የነበረው ልቡ ቁርጦ ውሳኔ ከሰጠ በሁዋላ ስለቀለለው፥ ከፊቱ ላይ የደስታ ስሜት በጉልህ ተፅፎ ይነበብ ነበር።

አስመራጭ ኮሚቴው ምልክት ተደርጎባቸው የተመለሱትን ወረቀቶች ገምግሞ የምርጫውን ውጤት ለማወቅ ጊዜ አልፈጀበትም። የቤቱ አባሎች የተጨነቁበትን የምርጫ ውጤት ለመስማት፥ ማን ይሆን? ማን ይሆን? እያሉ በጉጉት እንደሚጠባበቁት ሁሉ፥ የስድስቱም እጩዎች ልብ፥ ምንም እንኩዋ ሁሉም በንግግራቸው ወቅት የአብዮት ጥበቃ ሊቀ መንበር ሆኖ መመረጥ ከባድ ሀላፊነትንና መስዋእትነትን የሚጠይቅ መሆኑን ቢገነዘቡም፥ እኔ እሆን? እኔ እሆን? በማለት ልባቸው ድው፥ ድው፥ እያለ እንደ ከበሮ ይመታ ነበር። ስልጣን የማያጉዋጉዋው ሙት ብቻ ነው፥ እንዲሉ።

ሶስቱም አስመራጮች አፍ ለአፍ ገጥመው ለጥቂት ጊዜ በለሆሳስ ከተንሾካሾኩ በሁዋላ፥ ሊቀ መንበሩ በወረንጦ የማይለቀም ሽንጡን እያሳየ ብድግ ብሎ፥ ‹‹እሺ ጉዋዶች፥ ውጤቱን በናፍቆት የምትጠባበቁ ይመስለኛል- አይደለም እንዴ?›› ብሎ፥ የቤቱን ስሜት ለማጤን ያህል ንግግሩን ቆም አደረገ።

ፍፁም ፀጥታ የሰፈነበት ቤት ከመሆኑ የተነሳ፣ ምርጊ እንኳ ብትወድቅ ሳትሰማ አትቀርም። ከሁሉም ፊት ላይ ጉጉት የሚያንፀባርቅ ፈገግታ ይታያል። የሁሉም የልብ ትርታ ጨምሮ ነበር።

‹‹መቼም እንደምትሰሙ ውጭ የመደብ ትግሉ እየተጡዋጡዋፈ ነው። ለአድሃርያን ጨለማው የባሰ ጨለማ፣ ለጭቁኖች ግን ብርሃን ሆኗል። የምትሰሙት ተኩስ ለአድሃርያን ግብአተ መሬትን፣ ለጭቁኖች ብሩህ ተስፋን የሚያበስር ነው። ቀይ ሽብር!! ቀይ ሽብር!! ለኛ!! ለጭቁን መደቦች ሁሉ፣ መስተ አይደለም፣ አለኝታችን፣ የአብዮታችን ዋስትና እንጂ!››

ሁሉም ጆሮውን በማቆም ጉዋጉቶ የሚጠባበቀው የምርጫውን ውጤት ለመስማት እንደመሆኑ መጠን፣ ጉዋዱ እግረ–መንገድን የሚናገረውንም ሆነ፣ ከውጭ የሚቀልጠውን ተኩስ ከልብ ያጤነ አልነበረም።

‹‹እሺ እንግዲህ ጉዋዶች! ብዙ አዘገየሁአችሁ መሰለኝ። ዘጠኝ ድምፅ በማግኘት ሶስተኛ ተመራጭ በሆነው እንጀምር–››

ሁሉም አጉረምርመው፣ አቀማመጣቸውን በመለወጥ ከወንበሮቻቸው ላይ ተመቻቹ።

‹‹ጉዋድ ኡርጌ ደባላ ዘጠኝ ድምፅ በማግኘት ሶስተኛ ተመራጭ ሆኗል!›› ጭብጨባው ቀለጠ። ኡርጌን ለማየት ሁሉም ወዲህና ወዲያ ያማትር ነበር።

‹‹መልካም ነው። አስራ አንድ ድምፅ በማግኘት ጉዋድ ላጺሶ ሲልጆር ሁለተኛ ተመራጭና የአብዮት ጥበቃ ምክትል ሊቀ መንበር!!››

ጭብጨባው የአስመራጭ ኮሚቴውን ሊቀ መንበር ድምፅ ውጦ አስተጋባ። ከላጺሶ ጎን የተቀመጡት ጉዋዶች እየተነሱ በጋለ ስሜት ይጨብጡት ነበር። ግን ጊዜ አላጠፉም። ሁሉም ወደየወንበሩ ተመልሶ ተቀመጠ። ቤቱ ፀጥ አለ። ከፍተኛ ውጥረት የተመላበት ዝምታ በአዳራሹ ውስጥ ሰፈነ። አንዳንዶቹ ሲተነፍሱ ይሰማ ነበር። ሊቀ መንበሩም ሲቃ ይዞት ባጭሩ ባጭሩ ሲተነፍስ ይታይ ነበር።

‹‹ሰላሳ ድምፅ በማግኘት የቀበሌያችን የአብዮት ጥበቃ ሊቀ መንበር ሆኖ የተመረጠው ማን ይመስላችሁዋል?››

ከፍተኛ ማጉረምረም ሆነ፡፡

‹‹ጉዋድ ደርቤ ጉተማ!!››

ቤቱ በጭብጨባ፥ በሆታና በፉጨት ተናጋ፡፡ ጭብጨባው እንደ ክረምት ዝናብ ሳያባራ እየቀጠለ ለብዙ ጊዜ ቆየ. . .

ደርቤ ምስጋና ለማቅረብ ወደ መድረኩ ሲሄድ፥ ከድንጋጤው ብዛት እግሮቹ ይሞቱ ነበር፡፡ ሊቀ መንበሩ በጭብጨባ ተቀብለው እጁን ጨብጠ አቅፎ ከሳመው በሁዋላ፥ ስሜቱ ገንፍሎ፥ ከጠረጴዛው ላይ ተጋድሞ የነበረውን ክላሺን አንስቶ ሰጠው፡፡

ደርቤ ክላሺኑን ከራሱ በላይ ከፍ አድርጎ ለጉዋዶቹ ሲያሳይ፤ ሌላ ጭብጨባ፥ ሆታና ፉጨት እንደገና ከግድግዳ ግድግዳ እየተላተመ አስተጋባ፡፡

ጣምራ ጣምራ የሆኑ የእንባ ዘለላዎች የደርቤን ጉንጮች አቋርጠው ይወርዱ ነበር፡፡ ከወንዳ ወንድ፥ ውብ፥ ቀይ ዳማ ፊቱ ላይ የደስታ ሳይሆን የመደናገጥ ስሜት ይታያል፡፡ በረጂም ቁመናው ከመድረኩ ላይ ወጥቶ ሲቆም ከሰው በላይ ግዙፍ የሆነ መስሎ ይታይ ነበር፡፡

ጭብጨባው ሲያባራ ጠብቆ፥ ሊቀ መንበሩ መናገር ጀመረ፥ ‹‹ጉዋዶች፥ በምርጫችሁ ሁላችሁም እንደተደሰታችሁ አምናለሁ፡፡ ጉዋድ ደርቤ ቅድም በንግግሩ እንደ ገለፀው ሁሉ፥ ከህፃንነት ጀምሮ እስከ አብዮቱ ፍንዳታ ድረስ በሰው ቤት በአሽከርነት ሲያገለግል የቆየ ቢሆንም፥ ማታ ማታ በትግል እየተማረ አስራ ሁለተኛ ክፍል የደረሰ ታታሪ ወጣት ነው፡፡ ባሁኑ ጊዜ በንብረት ክፍል ፀሐፊነት በማስታወቂያና መርሀ ብሄር ሚኒስቴር ውስጥ በስራ ላይ ይገኛል፡፡ የአእምሮ ብስለቱንና አስተዋይነቱን የተገነዘቡ ሀቀኛ ጉዋዶች መልምለውት በየካቲት ፷፮ ፖለቲካ ትምህርት ቤት የርእዮተ አለም ትምህርት ከመከታተሉም በላይ ለሚያኮራ ጥረቱና ስመልካም ጠባዩ የምስጋና ወረቀት ከሽልማት ጋር አግኝቶአል፡፡ እኔ ከጠባዩ ውስጥ በጣም ጎልተው የሚታዩኝ ነገሮች ቢኖሩ ትህትናውና ለመማር ያለው ብርቱ ፍላጎቱ ናቸው፡፡

‹‹የቀሰመውን የርእዮተ አለም ትምህርት ከዘወትር አስተሳሰቡና ድርጊቱ ጋር የማዋሃድ፣ ማለትም ቲዎሪን ከተግባር ጋር አጣምሮ የመስራት ችሎታው የንኡስ ከበርቴዎች ልክስክስ ጠባይ እንደ አጉል ጀብደኛነት፣ ወላዋይነትና ከእኔ በላይ አዋቂ ለአሳር ነው ባይነትና የመሳሰሉትን ፍፁም አስወግዶ፣ ሀብቱ የሆነው ትህትናው ሳይለየው በሀቀኛነት ያለ ይሉኝታ የተጣለበትን ሀላፊነት በትግል የመወጣት ችሎታው ወደ ፊት በተግባር የሚታዩ ናቸው። ብዙዎቻችን ይህን የትግል ጎዳና ልንዘልቀው ቀርቶ ግማሽ መንገድም ለመሄድ አንችልም –

‹‹በአብዮታዊ ወኔ ታድመን፣ የወዛደሩን ርእዮተ አለም ቲዎሪ ከተግባር ጋር አጣምረን፣ በአብዮታዊ አስተሳሰብ አብዮታዊ ህይወት መኖር እጅግ አስቸጋሪ ነው። ለፈተናው ተሰገብግበው የሚቀርቡት ብዙዎች፣ ፈተናውን አልፈው የሚገኙት ግን ጥቂቶች ናቸው። ስለሆነም ነው፣ ጉዋዶች፣ በጥራት እንጂ በብዛት የማናምነው። የደብተራ ጋጋታ ቅዳሴውን አያሳምርም። ደባትር እንደ አሸን ፈልተዋል – ማርክስና ሌኒንን የሚያነበንቡ – ምስጢሩ ሳይገባቸው – ተሳስተው የሚያሳስቱ፣ እንደ ጥንቱ ደብተራ ጠዋት በቀኝ እጃቸው እያማተቡ ቀኝ ግራ እጃቸውን እንደ ሰይፍ የሚመዙብን ደባትር ብዙ ናቸው። ውሀ ቢወቅጡት መልሶ እንቦጭ እንዲሉ! ተከናንበው ቢመጡ ገልጦ የሚያይ የአብዮት ብርሃን ፈንጥቆአል። የፈነጠቀው ብርሃን አሁን እርቃናችንን አውጥቶ ባያሳየን የጊዜ ጉዳይ ነው!››

‹‹ከሁሉም በላይ አብዮቱ!

አብዮቱ!

ከሁሉም በላይ አብዮቱ!

አብዮቱ!

ከሁሉም በላይ አብዮቱ!››

አብዮቱ!

‹‹አሁን ለጉዋድ ደርቤ መድረኩን እለቃለሁ። አመሰግናለሁ።››

‹‹በተግባር!››

‹‹ለዲሞክራሲያዊ ማእከላዊነት እንታገላለን!››

‹‹በተግባር!››

‹‹ከሁሉም በላይ አብዮቱ!››

‹‹አብዮቱ!››

‹‹ከሁሉም በላይ አብዮቱ!››

‹‹አብዮቱ!››

ደርቤ በሰፊው ያሰበውን ንግግር ባጭሩ ገትቶ ከመድረኩ ሲወርድ አሳቡ ሁሉ ሌላ ቦታ ሂዶ ነበር። ያደረበት የህሊና ጭንቀት አልተለየውም። እና ከመስቀልኛ መንገድ ላይ ደርሶ በዚህ ወይስ በዚያ? በየትኛው ልሂድ? በማለት እንደተቸገረ መንገደኛ ያህል ነበር ጭንቀቱ። የሚጉዋዝበትን መንገድ ለመምረጥ አልቻለም። የገዛ ልቡ እንደ ድንጋይ ከበደው… ይቀልጥ የነበረው ጭብጨባ አልተሰማውም። በድንገ ነበር ጉዋዶች አንድ ባንድ እየመጡ የሚጨብጡት…

ደርቤ እንደተቀመጠና ቤቱም እንደተረጋጋ የቀበሌው ሊቀ መንበር ተነሳና፥ ‹‹አሁን፥ ባሳለፋችሁት ውሳኔ መሰረት ዋስይሁን፥ ከበደና ግብረ አበሮቹ ለአብዮታዊ ፍርድ ይቀርባሉ›› ከማለቱ ዲሞትፎር ጠብመንጃ ይዘው ካጠገቡ ቆመው የነበሩ ሁለት ጉዋዶች ከአዳራሹ እየተጣደፉ ወጡ።

ሁለት እጃቸውን ወደ ሁዋላ የፊጥኝ የታሰሩ ሶስት ሰዎችን አጅበው በሄዱበት ፍጥነት ተመልሰው መጡ። የቀድሞው የአብዮት ጥበቃ ሊቀ መንበር፥ ዋስይሁን ከበደ፥ ከሁሉም ቀደም ብሎ አንገቱን ደፍቶ ባጭር ባጭሩ እየተራመደ ይሄድ ነበር። ፍርሃት የሚሉት ነገር ሲያልፍም የነካው አይመስልም። ‹‹ትናንት ያጎበድዱልህ የነበሩት ሰዎች፥ ጊዜ ሲከዳ አይተውህ፥ በአደባባይ ስትሰቀል ቆመው ይስቃሉ›› የሚል አሳብ በአእምሮው ይመላለሳል። ‹‹ወይኔ ዋስይሁን! … ሳልቀድማቸው ለትንሽ ተቀደምኩ!››

ውስኪ እየተጎነጨ በአምስቱ ሰዎች ላይ የፈፀመው ግፍ አንሶ፣ ይባስ ብሎ ማምሻውን ደግሞ የፈፀመው የጭካኔ አገዳደል ነበር፣ ሌሎቹን የአብዮት ጥበቃ አባሎች ከመጠን በላይ አስቆጥቶ ፍርሃታቸውን በማስወገድ እንዲተባበሩ ያደረጋቸው። አንድ ከመካከላቸው ወኔ ይዞት፣ «ጎበዝ፣ ይህን በኛ ስም የሚፈፀመውን ግፍና ጭካኔ ዝም ብለን የምንመለከተው እስከመቼ ድረስ ነው? እኛስ ወንዶች አይደለንም ወይ?» ባለ ጊዜ ነበር፣ ሁሉም ተግባብተው፣ ሆኖም አንዱ የሌላውን ልብ ካለማመኑ የተነሳ እርስ በርሳቸው በአይነ ቁራኛ እየተጠባበቁ በማድፈጥ፣ ከሰይጣናዊ ተልእኮ እስኪመለስ ድረስ ጠብቀው፣ እርሱንና ግበረ አበሮቹን ትጥቅ በማስፈታት የያዙአቸው።

ዋሰይሁንም ቢሆን እሳት ከላሱ ግብረ አበሮቹ ጋር ሰይጣናዊ ተልእኮውን ፈፅሞ ወደ ቀበሌው በፍጥነት የተመለሰው አለምክንያት አልነበረም። ብልጥ በመሆኑ፣ ወደ ሁዋላ በቀሩት የአብዮት ጥበቃ አባሎች አይኑ-ውሀ ውስጥ ያነበበው ነገር ነበር። ተልእኮን ከፈፀመ በሁዋላ ከግብረ አበሮቹ ጋር በፍጥነት ወደ ቀበሌው የተመለሰው፣ በድርጊቱ ያልተባበሩትን የአብዮት ጥበቃ አባሎች ሁሉ ፀረ አብዮት ናቸው በማለት ይዞ ከጨረሳቸው በሁዋላ፣ በሌላ በኩል ደግሞ ዞር ብሎ በአምስቱ ሰዎች ላይ የፈፀመውን ኢሰብአዊ ድርጊት በእነርሱ ላይ በማላከክ፣ ያለፈ ህይወቱን ምእራፍ የዘጋና ምንም ጥቁር ነጥብ የሌለበት ለማስመሰል ነበር።

የጊዜ ጉዳይ ነበር። ይኸኔ ያለፈ ህይወት ታሪኩ ተፍቆ ዱካው ጠፍቶ አዲስ የህይወት ምእራፍ የሚጀምርበት ጊዜ ነበር። ግን የዚያ ተስፋ ደብዛ አሁን ጠፍቶአል-ዳግመኛ ላይመጣ! ሁለት እጆቹን ወደ ሁዋላ የፊጥኝ ታስሮ ማምሻውን ሊፈርድባቸው የነበሩት ሰዎች ሊፈርዱበት ቁጭ ብለው በማየቱ፣ «የጊዜ ጉዳይ ነው! ሞች ነኝ — — ቂል!» ብሎ በልቡ ጥርሱን ነከሰና አክ እንትፍ ብሎ የህይወቱን ምእራፍ ዘጋ። ከእንግዲህ ተስፋም ሆነ ፀፀት፣ ንዴትም ሆነ ቁጭት፣ ከልቡ ምንጭቅ ብለው ወጡ። ልቡ ባዶ፣ ሰውነቱ በድን ሆነ... ለሞት ሆነ ለህይወት፣ ለምንም ደንታ አልነበረውም...

ደርቤም እንደ ዋሰይሁን ልቡ ባዶ፣ ሰውነቱ በድን ሆኖ ይመለከተው ነበር። ሆኖም አይን ቢያተኩር ልቡና ካልታከለበት እውር ነውና፣ ለደርቤ

ዋስይሁን ከቦታው እንዳልነበር ነበር። የተጨነቀው የደርቤ ሀሲና ወደሌላ አለም ዘምቶ ነበረ... የተከለከለች ፍሬ ያለችበት አለም...

ሊቀመንበሩ ድምፁን ከፍ አድርጎ፣ «እሺ እንግዲህ ጉዋዶች፣ ዝርዝሩን ሰምታችሁዋል። አሁን ቤቱ ፍርዱን እንዲሰጥ እጠይቃለሁ» ባለበት ጊዜ ነበር፣ ደርቤ ጭልጥ ብሎ ከተጉዋዘበት የህሊና ጭንቀት ጎዳና ወጥቶ፣ አሁን ወዳለበት እውነታዊ አለም እንደ መባነን ብሎ የተመለሰው። ያለበትን አካባቢ እውነታ ካጤነና ዋስይሁን ከተመለከተ በሁዋላ ነበር፣ «ዛሬ ላንተ የደረሰችው ፅዋ ነገ የማን ትሆን?» የሚል ሀሳብ በድንገት እንደ ጥንግ ተወርውሮ አእምሮውን የመታው። እና፣ ለመጀመሪያ ጊዜ ከዚህ ቀደም የማያውቀው አንድ አይነት ፍርሃት መጥቶ ሰውነቱን እንደ ጉንዳን ወረረው - ቀዝቃዛ ላብ በጀርባው ወርዶ አሰመጠው። ከልቡ ጥልቀት ውስጥ ተዳፍኖ የኖረው ለሂሩት ጉልላት ያለው ሚስጢራዊ ስሜት፣ አሁን ካለበት እውነታ ጋር ባልተገናዘበ ሁኔታ ውስ እንደጠፋ ልቃቂት ተወሳስቦ ሀሊናውን ከማስጨነቅ አልፎ አስደነገጠው። የገዛ እራሳችን ስሜት አንዳንዴ ምን ያህል እንደሚያስፈራን ለተከሰተለት ብርድ እንደያዘው ሰው መላው ሰውነቱ ተንቀጠቀጠ። «እህ - ለካ እራሳችንንም መፍራት አለና! ስንቶቻችን በዚህ ፍርሃት ጥላ ስር እንኖር ይሆን?» በማለት ለአንድ አፍታ አሰበ።

«አብዮታዊ ቅጣት! አሁን!» በሚል ፍርድ ቤቱ በአንድነት አስተጋባ።

ሊቀ መንበሩ ከፍርዱ ይልቅ ለስነ ስርአቱ በይበልጥ የተቆረቆረ ይመስል፣ «አብዮታዊ ፍርድ አሁን! ማለት ብቻ አይበቃም» አለ።

«ሁላችንም አንድ ባንድ እጃችንን በማውጣት በነፍስ ወከፍ ድምፅ መስጠት አለብን። የተለየ ሀሳብ ያለው ሰው ካለ፣ የተለየበት ምክንያት ተገልፆ ይመዘገብለታል። ስለዚህ «አብዮታዊ ፍርድ አሁን» የሚለውን አሳብ የምትደግፉ እጃችሁን አውጡ» ካለ በሁዋላ፣ እያንዳንዱ ሰው የሚሰጠውን ድምፅ ለመመዝገብ ሲዘጋጅ፣ ደርቤ ድምፁን ከፍ አድርጎ፣ «ጥያቄ አለኝ» በማለት እጁን አወጣ።

ሊቀ መንበሩ ቀና ብሎ፣ «እሺ! ጉዋድ ሊቀ መንበር፣ ጉዋዶች፣ አሁን የማቀርበውን ጥያቄ ቅድም ባለማንሳቴ ይቅርታ እጠይቃለሁ። የማቀርበው

ራሳቸው መርምረው ባለው ሁኔታ ካጣሩ በሁዋላ፥ ፍርድም ራሳቸው ይሰጣሉና የኛ ቀበሌ በተናጠል ታይቶ የተለየ አሰራር ሊፈጥር ወይም ሊከተል አይችልም. . . የሚሉ አሳቦች እኩል ተራ በተራ እየተሰነዘሩ ክርክሩ ተጋግሎ ቤቱ እንደ ቡርኻዋ ፓርላማ ሲንጫጫ ከቆየ በሁዋላ፥ ደርቤ እንደ ገና እጁን ስላወጣ መድረኩ ተሰጠው።

‹‹ጉዋድ ሊቀ መንበር፥ ጉዋዶች፥ ከቤቱ ብዙ አሳቦች ተሰንዝረዋል። ዞሮ ዞሮ የክርክራችን መነሻና መድረሻ የሚያተኩረው የዲሞክራሲያዊ ማእከላዊነት አሠራር ይኑር ወይስ አይኑር በሚለው መሰረታዊ ጥያቄ ላይ ነው። የሰፊው ህዝብ አብዮት ግቡን እንዳይመታ የሚፈልጉ አድሃሪዎችና በአብዮተኛነት ስም ከሰፊው ህዝብ ትከሻ ላይ ባቁዋራጭ ለመውጣት የሚፈልጉ የስልጣን ጥመኞች፥ ማእከላዊነት ጠፍቶ የስርአተ - አልበኛነት አሰራር እንዲነግስ የሚፈልጉ ለመሆናቸው እኔ በበኩሌ አልጠራጠርም. . .

‹‹ጉዋዶች፥ ባሁኑ ወቅት፥ በተለይ የስልጣን ጥም እንዳበደች ውሻ የሚያክለፈልፋቸው ግለሰቦችና ቡድኖች ቀበሌዎችንን መሳሪያ ለማድረግ እንደሚፈልጉ ግልፅ ሆኖ እንዲታየን ያስፈልጋል። በስውር ዘዴያቸው በቀበሌዎች አካባቢ ስርአተ-አልበኛነት የሚነግስበትን ሁኔታ በመፍጠር፥ አንድም አብዮቱን ለመቀልበስ፥ አለዚያም ባቅዋራጭ የስልጣን ጥማቸውን ለማርካት በመፍጨርጨር ላይ ይገኛሉ። ቀበሌዎች የሰፊው ህዝብ አብዮት መሳሪያ እንጂ የግለሰቦችና የቡድኖች ስልጣን ጥም ማርኪያ እንዳይደሉ ከኔ የበለጠ እናንተ ታውቃላችሁ. . .

‹‹ጉዋዶች፥ ዋሲይሁንና ግብረ አበሮቹን ከቁጥጥራችን ስር አውለን የፊጥኝ ታስረው ከፊታችን እንዲቆሙ ያደረግንበትን ምክንያት መለስ ብለን እንመልከት። ያንዳንድ ግለሰቦችና ቡድኖች መሳሪያ በመሆን፥ በማን አለብኝነትና በአምባ-ገነንነት የዲሞክራሲያዊ ማእከላዊነትን አሰራር ደብዛ ከነአካቱው ስላጠፉ አይደለምን? እነርሱ ራሳቸው ጠርጥረው፥ እነሱው ይዘው እነሱው መርምረው፥ እነሱው ፍርድ ሰጥተው፥ እነሱው የፍርድ አስፈፃሚ በመሆናቸው አይደለምን? ታዲያ እኛ ደግሞ በተራችን ጠርጣሪ፥ መርማሪ ፍርድ ሰጭና አስፈፃሚ እንሁን ብለን ስንከራከር ራሳችንን በራሳችን መቃረን

አይሆንብንም - የለም ጉዋዶች፥ አዘማሚያችን ይህ አልመሰለኝም። እኔ እንደገባኝ ከሆነ ጭብጣችን፥ ዲሞክራሲያዊ ማእከላዊነት ይትር ነው!

‹‹ጉዋዶች፥ የዲሞክራሲዊ ማእከላዊነትን መርሀ መሰረት በማድረግ የሚከተለውን አሳብ አቀርባለሁ። ቅድም ከተነበበልን ዝርዝር ዘገባ ላይ ሁላችንም በመፈረም ዋስይሁንና ግብረ አበሮቼን ለበላይ አካል፥ ለመንግስት አሳልፈን መስጠት አለብን እንጂ እኛው ጠርጣሪ፥ እኛው መርማሪና ከሳሽ፥ እኛው ፍርድ ሰጭ መሆን የለብንም።››

ከባድ ፀጥታ በቤቱ ላይ ወደቀ። ደርቤ ባቀረበው ክርክር ምክንያት አቋማቸውን የለወጡ ብዙዎች ቢኖሩም፥ አንዳንዶቹ፥ ‹‹ነገ በነፃ ተለቆ የተመለሰ እንደሆን የት ልንገባ? ምን ሊውጠን? የለም፥ አሁኑኑ ብረትን መቀጥቀጥ በግለቱ ወቅት እንዲሉ። አሁኑኑ አብዮዋዊ እርምጃ መውሰድ አለብን። ያልቀደመ ተቀደመ፥ ያልጠረጠረ ተመነጠረ›› የሚል የአስተሳሰብ አቅጣጫ በመከተል ለክርክር የሚያቅማሙም ነበሩ። በመጨረሻ ቤቱ በቀረቡት ሁለት አሳቦች ላይ ድምፅ እንዲሰጥ በተጠየቀበት ጊዜ፥ የደርቤ አሳብ ያላንዳች ተቃውሞ በሙሉ ድምፅ ተደግፎ በማለፉ ሊቀ መንበሩን ገረመው።

በዋስይሁንና በግብረ አበሮቹ ፊት ላይ ደካማ ፈገግታ መታየት ጀመረ። አንድ ሰአት? አንድ ሌሊት? አንድ ቀን? ሳምንት፥ ወር? ማን ያውቃል?

ይህችን የምታጉዋጉዋ አለም ሳይወድ በግድ ተሰናብቶ፥ ዳግመኛ ላይመለስ፥ አንደኛውን ለመሄድ የሚፈልግ ማን አለ ሰው ልብ ምን ቢሆን ፍፁም ተስፋ አይቆርጥም። ሙት ብቻ ነው ተስፋ የሌለው። ፈገግታቸው ጨመረ። ግን በአንፃሩ፥ የደርቤ ልብ በአሳብ ባህር ውስጥ እየሰመጠ፥ ህሊናው እየተጨነቀ፥ ፊቱ እንደ ክረምት ሰማይ ጭጋግ እየለበሰ ይሄድ ነበር. . .

‹‹ከሁሉም በላይ አብዮቱ!››

‹‹አብዮቱ!››

‹‹አብዮቱ!››

‹‹አብዮቱ!››

[illegible]

[illegible]
[illegible]
[illegible]
[illegible]
[illegible]

Scan

# ምእራፍ ፫

ሂሩትም ሆነች ተሰማ ወይዘሮ አምሳለ ያደረጉትን የስልክ ጥሪ ሳይሰሙ ቀርተው አልነበረም-ዝም ያሉት፡፡

ስልክ ደወለ፡፡ ሁለቱም ተያዩ፡፡ አንድ አይነት የመግባባት መንፈስ በመካከላቸው ተፈጥሮ ነበር፡፡ ሆኖም ሶስተኛው ወጣት ትላልቅ አይኖቹን በስልኩ ላይ ተክሎ ለማንሳት የሚያቅማማ መሆኑን በመገንዘቡ፥ ‹‹እርሳው! እሮጊትዋ ናት›› አለች ሂሩት፤ ጥሬ እንደ ቃመች ዝንጀሮ የቀኝ ጉንጭዋን በጎረሰችው ጫት አሳብጣ፡፡ እጅዋም እግርዋም አያርፍም፡፡ ከሰፊው ክፍል ውስጥ አበባ ምንጣፍ ከወለሉ ላይ ዘርግተው መጅሊስ የገቡ ይመስል ሶስቱም ቁጭ ብለዋል፡፡ ሻይ በጀበና ቀርቦአል፡፡ ጫት ከያንዳንዱ ፊት ተከምሮአል፡፡ ሃድራው ወርዶአል፡፡

ቤቱ ከመንገድ ራቅ ያለ በመሆኑ የአላፊው የአግዳሚው ጫጫታ አይሰማም፡፡ ተኩስ አልፎ አልፎ ከሩቅ እንደ ክረምት ሰማይ ያጉረመርማል፡፡ ቤቱ የከተማ ቦታንና ትርፍ ቤቶችን ከመንግስት ቁጥር ስር ያዋለው አዋጅ ከመታወጁ በፊት ትንሽ ቀደም ብሎ ወደ ክትፎ ቤት የተለወጠ ቢሆንም፥ በፊት በወር አምስት መቶ ብር ኪራይ የሚያስገኝ ቪላ ነበር፡፡ ወይዘሮ አምሳለ ቤቱ እንዳይወረስባቸው ደህና ጉቦ በመስጠት ትርፍ ቤት መባሉ ቀርቶ በድርጅትነት ስለተመዘገበ፥ ለማስመሰል ያህል የክትፎ ንግድ ከፈቱበት እንጂ፥ ቤቱ ከሰዋራ ቦታ የተሰራ በመሆኑ ክትፎ ለመብላት ብቅ የሚልም ደንበኛ ብዙ አልነበረም፡፡

አፍሮውን አንጨፍሮ እንቅልፉም ትላልቅ አይኖቹን የሚያንከባልለው ወጣት በሂሩት እንደዚህ እርግጠኛ ሆኖ መናገር መንፈሱ አልረካም - ‹‹በምን አወቅሽ እሮጊትዋ መሆናቸውን? ወይስ ጫቱ ወልዩ አድርጎሻል?›› አላት፥ ኮስተር ብሎ ጫቱን እያኘከ፡፡

በተሰማ ልብ ውስጥ ጥርጣሬና ፍርሃት አደረ፡፡ እናቱ የሚጠሉበትን የተንቸረገገ ጢሙን አንድ ባንድ እየመዘዘ ወደ ታች ይስብ ጀመር፡፡ ውጭ እንደ ዶፍ የሚወርደው ተኩስ መንፈሱን ማወክ ከጀመረው ቆይቶአል - ‹‹ሂሩቴ፥ ሌላ ሰው ሊሆን ይችላል!›› አለ ተሰማ፥ አሳቡ ታውኮ፡፡

‹‹አሁንም የሰነዘርሺው ቀኖናዊ አስተያየት ነው፡፡ ሳይሽ አረካለሁ፡፡ ነፍሴም ጭምር ትረካለች›› አላት፡፡

‹‹ዘጋ ባክህ! ለትዝታዊ ስሜት ደንታ የለኝም፡፡ ወንዶች ስትባሉ ውሾች ናችሁ!›› አለችው፡፡

‹‹እሹ ለማዳ ውሻሽ ነኝ!›› አላት፡፡

ተሰማ ተበሳጭቶ፥ ‹‹አቁሙ ባካችሁን፡፡ የምትናገሩት ሁሉ ደስ አይለኝም፥›› ከማለቱ . . . .

ተፈራ አቋዋረጠውና፥ ‹‹ገርል ፍሬንድህ ስላልመጣች ነው ንግግራችን ያስጠላህ? እውነት ዛሬ እቴቱ የት ጠፋች?›› ብሎ ጠየቀው፥ እየቀለደ፡፡

‹‹እቴቱ ገደል ትግባ! ለቀልድ ጊዜ የለኝም፡፡ ይህን ሁሉ ተኩስ እየሰማችሁ ስትቀልዱ ይገርመኛል›› አለ ተሰማ፥ በስጭት ብሎ፡፡

‹‹ማሙሽዬ፥ አይዞህ፥ ፈርተህ አትጨነቅ፡፡ የተኩስ ጋጋታ የመርበድበድና የመደናገጥ ምልክት ነው - ሌላ አይምሰልህ፡፡ የመፍረክረክ ምልክት ነው፡፡ የባሰ ለማፍረክረክ ቅስቀሳችንና ነጥሎ የመምታት ተግባራችን በይበልጥ መፋፋም አለበት፡፡ ቀበሌ ከተዘጋ ለኛ በሩ ይከፈታል›› አለችና፥ ጫትዋን እኝክ እኝክ አደረገች፡፡

ስልኩ እንደ ገና ተደወለ፡፡ ሂሩት ስልኩ ስንት ጊዜ እንደሚጮህ በልብዋ መቁጠር ጀመረች፤ አንድ፥ ሁለት፥ ሶስት፥ አራት፥ አምስት. . . ‹‹አሁንም አሮጊትዋ ናት፤ ከመቼ ወዲህ ነው ደሞ ለኛ መጨነቅ የጀመረችው? ህይወትዋ ሁሉ መሬትዋ ነበር፤ እኛ በልብዋ ውስጥ ቦታም ሆነ ህልውና አልነበረንም. . . ትደውል አስር ጊዜ፡፡ አናነሳም፡፡ ትጨነቅ. . . የልጅ ፍቅር ምን እንደሆነ ይገባት እንደሆነ. . .››

ተሰማ ከሂሩት ጋር በአሳብ አልተስማማም፡፡ ሂሩት ስለ እናታቸው የተናገረችው ነገር ሀቅ ቢሆንም፥ ጆሮ ዳባ ልበስ ብሎ በእናቱ ጭንቀት ላይ ሌላ ጭንቀት መጨመር የማያስፈልግ ጭካኔ ሆኖ ስለተሰማው፥ ‹‹እንደገና ብትደውል ስልኩን አነሳለሁ፡፡ ለምን እናስጨንቃታለን? አባታችንም ቢሆን በጣም ይሰጋል›› አለ፥ ኮስተር ብሎ ወደ ሂሩት እየተመለከተ፡፡

‹‹ሂሩት ወለላዬ፥ እኔስ ዋስይሁን ቢኖር ይሻል ነበር እላለሁ። ለምን ብትይኝ፥ ድርጊቱ ሁሉ በቀበሌያችን ነዋሪዎች ዘንድ ለኛ ጥሩ ስሜት እያሳደረ ሄዶ ነበር። አንዳንድ ትብብርም ለማግኘት የቻልነው እሱ ህዝቡን በማጉላላቱና በማስቃየቱ ምልክት ነው። የቀበሌው ህዝብ የሚያቅፈው ሰው ከመጣ ግን የባሰ ችግር ላይ እንወድቃለን። በዙሪያ መንገድ ዋስይሁን ከሰማይ ወረደልን አጋራችን ነበር›› አላት።

‹‹የቀበሌ ተመራጭ ብሎ አጋር እኔ አላውቅም!›› አለችና፥ ጫትዋን እንደገና እኝክ እኝክ አደረገች።

‹‹ከፖለቲካ አንፃር ስትመለከተው ማለቴ ነው. . .››

‹‹ተፈ ልክ ነው። ዋስይሁን ካደረሰብን ጉዳት በፖለቲካ አንፃር የሰጠን ጥቅም ያመዝናል›› አለ ተሰማ።

‹‹ዘጉ! ፍሬን ያዙ! ጠላት የማያደርሰውን ጥፋት ጠብቆ ከመጠቀም፥ በራሳችን ጥረት መተማመን ይሻላል። ትናንት ከዲሞክራሲ ያጠናነው ነገር ይኸው ነው። ጠላቶቻችንን ወደ ባሰ ጥፋት በመገፋፋት ከህዝቡ ጋር የባሰ ቅራኔ እንዲፈጥሩ ማድረግ የእኛን ጥረት፥ ብስለት፥ ፍጥነትና ድፍረት ነው እንጂ የሚጠይቀው፥ የእነሱን ሞኝነት ወይም ድክመት ብቻ አይደለም›› አለችና፥ ሲጃራ አውጥታ አቀጣጠለች።

‹‹የእነርሱ ድክመት ለእኛ ጥንካሬ አይረዳም ነው የምትይው!›› አላት ተሰማ።

‹‹ዝጋ! ይልቅ ነገ በቀበሌያችን ቅስቀሳ ማድረግ የእኛ ተራ ነው። ተነገወዲያ ሰፈራችን ከምንጊዜውም ይበልጥ በአርማችን አሸብርቆ መገኘት አለበት። ቴስ - በበኩልህ ምን አድርገሃል?›› ብላ ጠየቀችውና ለራስዋና ለእነርሱም ሻይ በትናንሽ ብርጭቆ ቀዳች።

‹‹እኔ የሚሰቀሉትን አርማዎች ሁሉ አምጥቻለሁ. . .››

‹‹የሚበተኑትንስ ወረቀቶች?››

‹‹እሱንም ተረክቤአለሁ።››

‹‹ዝጋ ቴፑ! አንተ ምንም ነገር ሊገባህ አይችልም፡፡ በህሊናህ ውስጥ የሚጎጭ ነገር የለም፡፡ አንተ የሃሩሩ ጥላ ነህ! ሁሉን ነገር እንደ ቀልድ ነው የምትወስደው. . .››

‹‹አንተስ?›› አለችው እህቱ፥ ንቀት በተመላበት ሁኔታ፡፡

‹‹እኔ አልቀልድም፡፡ ሳንዘገይ አቀዋማችንን ማስተካከል አለብን፡፡ እውነቴን ነው፡፡ አገራችን ስትወረር፥ ወታደሩ መሀል ገብታችሁ፥ የምታካሂዱት አድሃሪ ጦርነት ነውና አትዋጉ እያላችሁ ቅስቀሳ አካሂዱ. . .እ. . . የጭቁን ብሄረሰቦችን መብት እስከ መገንጠል ድረስ አሁኑኑ እንደግፋለን በሉ፥ ወዛደሩ ምርቱን እንዲቀንስ ካገሪትዋ አቅም በላይ የሆነ የደመወዝ ጭማሪ እንዲጠይቅ አድርጉ፥ ወታደሩ እንዳይዋጋ ቅስቀሳ አካሂዱ፥ እየተባለ የሚሰጠን መመሪያ ሁሉ በኔ ግምት ትክክልና ሳይንሳዊ አይደለም. . .››

‹‹አላልኩም? የለየለት ባንዳ ሆኖአል እኮ!››

‹‹ባንዳነት አይደለም እባክህ! የህሊና ጉዳይ ነው፡፡ ለሰፊው ህዝብ ነፃነት፥ እኩልነት፥ ለጭቁኖች መደብ አንድነትና ለሶሻሊዝም እንዋጋለን፥ ፋኖ ተሰማራ፥ እንደ እነ ሆቺ ሚኒ እንደ እነ ቼ ጉቬራ! ብለን የተነሳን ወጣቶች ዛሬ ለስልጣን ብለን፥ ከፀረ ህዝብ፥ ፀረ - አንድነትና ፀረ - ሶሻያሊስት ሰፈር ገብተን መሰለፍ የለብንም፡፡ እዚህ አቀዋም ላይ ያደረሰን የስልጣን ጥያቄ ነው. . .››

‹‹ስልጣን ለፓርቲያችን ካልሆነ ለማን ሊሆን ነው ታዲያ? ለወታደር? ስንታገል የቆየነው ወታደር ስልጣን እንድይዝ ነው?›› ብሎ ተፈራ ጠየቀው፡፡

‹‹እባክህን ተወኝ! ራሱን ፓርቲ ነኝ ብሎ የሰየመ ሁሉ ፓርቲ ሊሆን አይችልም፡፡ እነላእከ ቅዠት ነው፡፡ አላምንበትም ነው የምልህ!›› አለው፥ ፍርጥም ብሎ፡፡

እህቱ በተጎለጎለት ትላልቅ ውብ አይኖችዋ በንቃት ተመለከተችውና፥ ‹‹ማሙሽ. . .እ. . .ብታምንበትም ባታምንበትም . . .እ. . . አንገትህ ድረስ ተዘፍቀህበታል፡፡ ከእንግዲህ መውጫ የለህም፡፡ ሁላችንም የለንም! ይህን በሚገባ ማወቅ አለብህ. . . ማሙሽ፡፡ ከሃዲዎች ምን እንደሚደረጉ

‹‹ደርቤ ጉተማ ነው እንዳትለኝ!›› አለች ሂሩት፥ መልሱን ለመስማት ተቻኩላ።

‹‹ነው! ተአምር ነው. . .የማይታመን ተአምር ነው. . .››

‹‹አይደረግም!›› አሉ እህትና ወንድም በአንድት፥ ጆሮአቸውን ለማመን እየተቸገሩ።

‹‹የባሰ ቢመጣስ? ብዬ አልነበረም ቅድም። ታይቶኝ ነው መሰለኝ! የሚገርም ነው!›› አለ ተፈራ።

‹‹ማን ነው ለመሆኑ የደወለልህ?›› ብላ ጠየቀችው ሂሩት፥ ተጠራጥራ።

‹‹የኮድ ስሙን ብቻ ነው የማውቀው። መሪ ጌታ ይባላል። የኛ ሰው ነው›› አላት።

ሂሩት ተገርማ፥ ‹‹ጉድና ጅራት ከወደሁዋላ ትላለች እናቴ! ፈፅሞ የማይታሰብ ነገር ነው!›› አለች።

ተፈራ ትንቢት የመናገር ችሎታውን እንዲያደንቁለት በማሰብ፥ ‹‹የባሰ ቢመጣስ ብዬ አልነበረም?›› አለ፥ ፈገግ ብሎ።

‹‹ዝጋ! የቃምከው ጫት ገልፆልህ ይሆናል! ጥያቄው አሁን ያንተ ወልይነት አይደለም። ማሰብ አለብን›› ብላ፥ ከንፈርዋን እየነከሰች ጣቶችዋን አንቁዋቁዋች። ጭንቅላትዋንም ወደ ቀኝ መታ አደረገች።

‹‹ሂሩት ወለላዬ፥ እውነትሽን ነው! ማሰብ አለብን። ውስጠ አዋቂ ጠላት ነው ኮ የተፈጠረብን።። አደገኛ ነው። ደርቤ ስለኛ የማያውቀው ምን ነገር አለ? ሁሉንም ነገር ያውቃል። ከእድገት በህብረት ዘመቻ ተደብቀን እንደ ቀረን ያውቃል። የትግል መስመራችን ምን እንደሆነ ከሀ እስከ ፐ ያውቃል። በድርጊት ያረጋገጥንለት ጉዳይ ነው። ሌላ የማያውቀው ምን ነገር አለ? ጉድ ነው ኮ! ውስጠ አዋቂ አደገኛ ነው. . .››

‹‹ታዲያ ኮ ምን እናድርግ! ውስጠ አዋቂ መሆኑን ተገንዝበናል። እሱን እንዳረጀ ሽክላ መልሰን መላልሰን መዝፈን የለብነም። ምን እንደምናደርግ

እናስብ ነው የምላችሁ!›› አለች ሂሩት፥ ትእግስትዋ አልቆባት፥ ጭንቅላትዋን አስር አስረ ጊዜ ወደ ቀኝ መታ እያደረገች።

‹‹ይህች ጥሪ ካደረች አትቆረጠምም ይባላል! እኔ ሳይቆይ መመታት አለበት እላለሁ። ለመከላከያ ጉዋዶች አሁኑኑ ደውዬ ማስታወቅ አለብኝ!›› ብሎ ውስኪውን በአንድ ትንፋሽ በመጨለጥ ቁና ቁና እየተነፈሰ፥ ወደ ስልክ ሊሄድ ሲል፥ ተሰማ ጢሙን አንድ ባንድ ስቦ ወደ ታች እየጎተተ፥ ‹‹ቆይ! ቆይ! አትቸኩል። የጅብ ችኩል ቀንድ ይነክሳል ሲሉ አልሰማህም? ረጋ በል። አትቸኩል። የቸኮለ አፍስሶ ለቀመ እንዳይሆን› አለው፥ ረጋ ብሎ።

‹‹አደገኛነቱ አልተከሰተልህም መሰለኝ! ነገሩ፥ ወይ ከኛ ወይ ከሱ መሆኑ ገብቶሃል? ጊዜ ካጠፋን ጠፊዎቹ እኛ እንሆናለን! ይገባሀል?››

‹‹ይገባኛል!›› አለ ተሰማ፥ ረጋ ብሎ ጢሙን እየሳበ። ቀጠለና፥ ‹‹የሚገባኝ ሌላም ነገር አለ›› አላት።

ሂሩት ትእግስትዋን ጨርሳ፥ ‹‹እንደምን ያለ?›› ብላ አፈጠጠችበት።

አሁንም ረጋ ብሎ፥ ‹‹ደርቤ አብሮ አደግ ወንድማችን ነው። ወላጆቻችን ማታ ማታ እንዲማር አድርገው ከኛ ጋር አሳድገውታል፡ በአጎታችን አማካይነት ስራም ስላስያዙት ባለውለታው መሆናቸውን ያውቃል። ደርቤ ውለታ የሚበላ ሰው አይደለም። ደርቤን ራሴን ያህል ነው የማውቀው፥ ራሴን አውቅ እንደሆነ። እና›› ከማለቱ፥ ሂሩት ነገሩን ካፉ ነጥቃ፥ ‹‹ዝጋ! መመታት አለበት!›› ብላ አፈጠጠችበት።

‹‹በአገራችን ውለታ እና ይሉኝታ የሚሉት ነገር አለ ለማለት ነው!››

‹‹የመደብ ትግሉስ!›› አለ ተፈራ።

‹‹የአብዛኞቻችን ንቃተ ህሊና፥ ማንኛውንም ነገር ከመደብ ትግል አንፃር ተመልክቶ ይሉኝታን፥ ውለታን፥ የስጋ ዝምድናንና ጉዋደኝነትን ጨርሶ ከመርሳት ደረጃ ላይ ገና. . ገና አልደረሰም. .››

‹‹ሰው እንዳስተመጠጡት አይገኝም ትላለች እናቴ! ተለውጦ እንደሆነስ? ዛሬ ነንቱ ተለውጦአል! ከራስ በላይ ነፋስ በማለት ሁሉም ለራሱ የሚሮጥበት

አድር ባይ የበዛበት ጊዜ ነው። በዚህ ሩጫ ውስጥ ይሉኝታን መፍራት፥ ውለታን መቁጠር የለም. . ተምኔታዊ አስተሳሰብክን አቁም! ዝ.ጋ!›› አለችና ወደ ተፈራ ፊትዋን አዙራ፥ ‹‹ይልቅ ስልኩን ደውል›› ብላ ካዘዘችው በሁዋላ፥ ‹‹እኛን ከግል ጥቅሙ የሚያስቀድምበት ምክንያት አይታየኝም። አሁን ትልቁ አንገብጋቢ ጥያቄ. . .ከኛ ወይ ከእርሱ ነው። ወንድም አለም! በዚያ ላይ ደግሞ ደርቤ ራሱን ከፍ ከፍ ለማድረግ ከፍተኛ ፍላጎት ያለው ሰው መሆኑን አውቃለሁ›› አለችው።

‹‹ባንቺ ምክንያት ይሆናል፥ ራሱን ከፍ ከፍ ለማድረግ የሚጥረው. . .››

‹‹ምን ማለትህ ነው!›› አለች ሂሩት፥ በጣም ተቆጥታ።

ሰውነትዋ ሁሉ ይንቀጠቀጥ ነበር። አይኖችዋ ተጎልጉለው ወጥተዋል። የታችኛው ከንፈርዋን ጣል አድርጋለች።

‹‹ተሰማ እህቱ በጣም የተናደደች መሆንዋ ስለገባው፥ ‹‹ምን አስቆጣሽ!›› አላት።

‹‹እንጃልህ!›› አለችው።

‹‹እህት አለም፥ ደርቤ ይወድሻል። መውደድ ስል ያፈቅርሻል ማለቴ ነው. . .››

‹‹የውሻ ልጅ፥ የምን ፍቅር!›› አለ ተፈራ፥ ቅናት አድርቦት።

‹‹አቁም ብዬሃለሁ!›› አለችና ሲጃራዋን ቡልቅ አደረገች፥ ጢሱ እስኪያፍናት ድረስ።

ድምፅዋ ስልቱን አጥቶአል። ጉሮሮዋ ለመዘጋት ደርሶአል። ንዴት ይተናነቃት ነበር።

ተሰማ በዚያው አላበቃም። ‹‹አዎን፥ ያመልክብሽ ነበር። ከቤት ወጥተሽ እስክትመለሺ ትእግስቱን ጨርሶ ጌታውን እንደሚጠብቅ ውሻ ይንጎራደድ ነበር። እግርሽን ካጠበ በሁዋላ እንዴት አድርጎ እንደሚስመው ትዝ ይልሻል፥ እህት አለም?›› አላት።

ሂሩት ንዴትዋን ልትቆጣጠረው አልቻለችም፡፡ ተፈራ መካከላቸው ባይገባ ኖሮ ጥፍሮችዋን አሹላ ጉሮሮውን ልታንቀው ነበር፡፡

ብርድ እንደ መታው ሰው እየተንቀጠቀጠች፥ ‹‹ሌላ የምታውቀው ምን ነገር አለ?›› ብላ ሊዘጋ በደረሰ ጉሮሮ ጠየቀችውና፥ ሲጃራ አውጥታ በማቀጣጠል ጢሱን ባንዳፍታ ጉም አስመሰለችው፡፡

ተፈራ ግራ ገብቶት አፉን ከፍቶ ቀርቶአል፡፡ ተሰማ እህቱን ትኩር ብሎ ለረጅም ጊዜ ተመለከተ፡፡ የሚያውቃት እህቱ መስላ አልታየችውም፡፡ አንድ ነገር ለመደበቅ እንደምትሞክር ገባው፡፡ አንድ ነገር ሸፋፍና ለማለፍ ስትፈልግ ሁልጊዜ አስቀድማ የምትናደድ መሆንዋን ያውቃል፡፡

‹‹ይሄው ነው፡፡ ሌላ የማውቀው የለም፡፡ ለማለት የፈለግሁት አደገኛ ሰው አይደለም፥ ስለዚህ አንቸኩል ለማለት ነው›› አላት፡፡

በረጅሙ ወደ ውጭ ተነፈሰችና፥ ‹‹የማይገባ ነገር አለ፡፡ አንድ ቀን ይገባህ ይሆናል፡፡ ወንድምና እህት ብንሆንም በብዙ መንገድ አንተዋወቅም›› ብላ ሲጃራዋን ማግ፥ ቡልቅ አደረገችና ወደ ተፈራ መለስ ብላ፥ ‹‹ለላእከ ደውለህ ንገረው፡፡ አስቸኩዋይ ነው በለው›› አለችና አዘዘችው፡፡

እህትና ወንድም ልብ ለልብ ተራርቀው ተያዩ፡፡

ተፈራ ስልኩን ደወለ . . .

የፖለቲካ ስራቸውን ቀጥለዋል:: ለጊዜው ተንገዳግዶ የነበረው ዙፋን ለሚቀጥለው ሶስት ሺህ ዘመን ቀና ብሎ የሚቆምበትን መሰረት እየጠገነ ነው:: እሰዎ ለከፋ አትሰጥም ነበር!

‹‹ሎሚ ተራ ተራ›› የተባለው ዘፈን ተወዳጅነትን እያገኘ ቢሄድም፣ ‹‹ትብለየን››፤ ‹‹እረ እየድማሙን››፤ ‹‹እንተዬን›› ገና ሊተካ አልቻለም. . .

ዝም ብሎ መጋደሙ ሰለቻት አላት - ሂሩትን:: ረፈድ ብሎ ስለ ነበረ መኝታዋም ወበቃት:: ከአልጋዋ ለመውረድ ስለ ሰነፈች ዝም ብላ በጀርባዋ ተጋድማ ቀረች:: ቀና ብላ የምታነበው መፅሀፍ አነሳች:: ‹‹ፍቅር እስከ መቃብር›› ነበር:: አንድ ጊዜ አንብባዋለች:: እንደ ገና ልታነበው ፈልጋ ነበር:: ማንበብ ጀመረች - የራስጌዋን መብራት አብርታ:: አሳብዋ እየባከነ ስላስቸገራት ማንበቡን ለመቀጠል አልቻለችም:: መፅሀፉን ወረወረችና ተነስታ ቴፕ - ሪኮርደርዋን ከፈተች:: ከጥቂት ጊዜ በሁዋላ ነበር፣ ቴፕ-ሪኮርደሩ የባትሪ ድንጋይ የሌለው መሆኑ ትዝ ያላት::

ጥላው የተነሳችው መኝታ ገሃነም መስሎ ስለታያት ሄዳ የመኝታ ቤትዋን መስኮት ከፈተች:: የጠዋትዋ ፀሀይ ብርሃን መኝታ ቤትዋን አጥለቀለቀው:: ውብ ቀን ነበር. . .

ሰማዩ ኩል መስሎ ተንጣሎአል:: አንድ ደመና ስለማይታበት ሰማዩ ከወትሮው ወደ ላይ የራቀ ይመስላል:: ንፁህ ቀዝቃዛ አየር ይነፍስ ነበር:: የተረበሸው መንፈስዋ በቀኑ ውበትም በቀዝቃዛው አየር ምክንያት ረጋ ማለት ቢጀምርም፣ ያደረባት ጭንቀት ሙሉ በሙሉ አልተለያትም::

‹‹ምን ነካኝ?›› አለች፣ ብስጭት ብላ::

የሆነችውን ልታውቅ አልቻለችም:: ቀዝቃዛውን አየር ወደ ሳንባዋ እየሳበች፣ ዝም ብላ በመስኮት ወደ ውጭ ትመለከት ነበር:: ሁለት ርግቦች ሲዳሩ አየች:

ከነጋ ቁርስ አላገኘችም: የምግብ ፍላጎት አልነበራትም: ግን ሰውነትዋ አንድ ነገር እንደሚፈልግ ይሰማት ነበር:: በስስ የሌሊት ልብስዋ ውስጥ እንደ

የቀይ ኮከብ ጥሪ

በረሃ ሎሚ ጉች ጉች ብለው የሚታዩትን ጡቶችዋን እያሻሸች፥ ሄዳ ፊትዋን በመስተዋት ተመለከተች።

ጥቁር የሀር ነዶ የመሰለው ጠጉርዋ አሻፈረኝ ብሎ በየአቅጣጫው ተበትኖአል። ልትዳኘው አልሞከረችም። እንደዚያው ተወችውና ጡቶችዋን ይዛ እያሻሸ ከመስተዋቱ ፊት ቆማ፥ መወዛወዝ ጀመረች። ወገብዋን እንደ እብድ ጥምልምል፥ እጥፍ፥ ዘርጋ ሳብ፥ ኩምትር፥ እያደረገች ስትወዛወዝ ከቆየች በሁዋላ ሮጣ ሄዳ አልጋዋ ላይ በመዘርጋት ስትንከባለል፥ በእግርዋ የራስጌዋን መብራት ገመድ ስለነካች፥ መብራቱ ከኮሞዲኖው ላይ ወድቆ ክሽ አለ።

ደርቤ የመኝታ ክፍልዋን በር ቀስ ብሎ አንኳኳ። ጡቶችዋን እንደ ያዘች መንከባለልዋን አቁማ፥ ‹‹ማን ነው?›› አለች።

‹‹ደርቤ ነኝ›› አላት።

‹‹ምን ትፈልጋለህ?››

‹‹አንድ ነገር ወድቆ የተሰበረ መስሎኝ ነው›› አላትና፥ ወደ ስራው ተመለሰ።

ሂሩት የመኝታ ክፍልዋን በር ከፈተችና ግራና ቀኝ ካማተረች በሁዋላ ‹‹ምን ነው ቤቱ ጭር አለ?›› አለች።

‹‹ማንም የለም። እሜቴ ጠዋት የወጡ ናቸው። ጌቶችም ስራ ሄደዋል፤ ተሰማና የቤት ሰራተኞችም ዛሬ የሚደረገውን ሰላማዊ ሰልፍ ለማየት ሄደዋል›› አላት።

‹‹የምን ሰልፍ!›› አለች።

‹‹የእስላሞች ሰላማዊ ሰልፍ›› አላት፡

‹‹የክርስቲያን ደሴት በሆነች አገር!›› ብላ ሳቀች።

ደርቤ መልስ አልሰጣትም። የቤት ዕዳት ስራውን ዝም ብሎ ቀበለ ሂሩት ዝም ብላ ስትመለከተው ከቆየች በሁዋላ፥ ድንገተኛ አሳብ [illegible] ራስዋን ልትቆጣጠር አልቻለችም።

‹‹ግባና የተሰበረውን የራስጌ መብራት አንሳ!›› አለችው።

የቤት ፅዳት ስራውን እርግፍ አድርጎ ትቶ፥ የታዘዘውን ለማድረግ ሰተት ብሎ ወደ መኝታ ክፍልዋ ገባ። በሩን ቆለፈች። ልቡ ስንጥቅ አለ፡

መኝታ ቤትዋ በጠረንዋ እውድ ብሎ ነበር። በሀይል ወደ ውስጥ ተንፍሶ ጠረንዋን ወደ ሳንባው እያስገባ፤ ወድቆ የተሰበረውን የራስጌ መብራት ለማንሳት ጎንበስ ሲል፥ ‹‹ስምህ ያስጠላኛል!›› አለችው።

ዝም አለ። የልቡ ትርታ እንደ ከበሮ የሚጮህ ስለ መሰለው አፈረ።

‹‹እሱን ተውውና እየኝ!›› አለችው።

ስራውን ትቶ መለስ አለ። አይን ለአይን ተጋጠሙ። ደርቤ አይኑን ሰበር አደረገ።

‹‹ከእግሬ ምናለህ!›› አለችው።

አንገቱን አቀርቅሮ፥ ‹‹ደስ ይሉኛል። እግርሽን ማጠብ ደስታ ይሰጠኛል›› አላት፥ ሰውነቱ እየተንቀጠቀጠ።

‹‹ደስታ የሚሰጥህ ከሆነ ሳመው›› አለችና የጠዋት ጫማዋን አውልቃ ጣለች። የሚያደርገው ነገር ጠፍቶት ዝም ብሎ ቆመ።

‹‹ታዲያስ?›› አለች።

ሄዶ ጥምጥም አለባት።

‹‹ንከሰኝ! ንከሰኝ! ›› አለች፥ በስሜት እየቃተተች። ነከሳት።

‹‹በሀይል! በሀይል! ›› አለችው፥›› ሊዘጋ በደረሰ ድምፅ። በሀይል ነከሳት።

የንክሻው ስሜት የሰጣት ደስታ ስለ ተሰማት ሲቃ የተመላበት ሳቅ እየተንከተከተች፥ ‹‹ጡቶቼን በሀይል ጨብጣቸው! ጭምቅ አድርገኝ!›› አለችው።

ባለ በሌለ ጉልበቱ ጭምቅ አድርጎ ያዛት። ሀሊናውን ስቶ ከአልጋው ላይ ይዞአት ወደቀ. . .

እሱ ፈዞ ቆመ የሚተኩሰው ሸሚዝ ተቃጥሎ ሲጠስ፥ ወይዘሮ አምሳለ ደርሰው፥ «ጉድ ፈላ ሰዎች! ምን ነካህ አንተ!» ብለው አስደነገጡት።

ሲያየው የሚተኩሰው ነጭ ሸሚዝ ተቃጥሎ ከስሎአል።

«ጉድ ነው! ጉድ ነው!» ብለው ሸሚዙን ተመለከቱና፥ «ብትሸጥም ዋጋውን ልትመልስ አትችልም» አሉ ተቆጥተው።

«ሳላውቀው ካውያው ግሉብኝ ነው» አላቸው ዋሽቶ።

«የሰም፥ ይህን ሰሞን ልብህን የሰለበው ነገር አለ። ቢጠሩህ አትሰማም፥ ቢነግሩህ አይገባህም፥ ሲበሉ የላኩህ ይመስል ነገር ትረሳለህ። ጎረመስክና ልብህ አበጠ መሰለኝ! እከከከከ! ከመቼ ወዲህ አንተ! የሰም፥ ልብህ ሸፍቷል. . .

«እኩልነት! ነፃነት ሲሉ ሰምተህ ነው መሰለኝ! ድንቄም እኩልነት እቴ! ቀጥ ብለህ ትሰራ እንደሆን ስራ! አለበለዚያ ከቤቴ ውጣልኝ!» ብለውት ሄዱ።

ማታ ራት ላይ ለባላቸው ደርቤ ስላደረሰው ጥፋት ሲነግሩዋቸው፥ አቶ ጉልላት፥ «አዎን ፈዞአል። ከአይን የሚቀድም ተፈ ነበር። ምን እንደነካው እግዜር ይወቅ» ብለው ዝም አሉ።

ሂሩት ትጠብቀው የነበረውን እድል ስላገኘች፥ «ማታ ማታ ትምህርት ቤት እሄዳለሁ እያለ የሚያመሸው ሌላ ቦታ ነው ሲሉ ሰምቻለሁ። ከቦዘኔዎች ጋር አፍ ለአፍ ገጥሞ ነው የሚያመሸው አሉ» ብላ ዋሸታ ነገረቻቸው።

«ለዚህ ነዋ!» አሉ ወይዘሮ አምሳለ።

«ምን ለመሆን ፈልጎ?» አሉ፥ አቶ ጉልላት እየተገረሙ።

«ምን መሆን ፈልጎ! ያልጠረጠረ ተመነጠረ አሉ ልጄ! ወመኔው ሁሉ ላቡ መቼ ተኛ! እምላክ የሰጠውን፥ ሰው ሊወስድ የሚችል ይመስል - ድሀው ሁሉ ጥርሱን እየነከሰብን ነው። እንዲያውም ትናንት በመንገድ ሳልፍ፥ በረንዳ አዳሪዎች፥ የተነቃነቀ ጥርስ ካልተነቀለ ጤና አይገኝም፥ ሲሉ ሰምቻለሁ። ባዳ ምጊዜም ባዳ ነው። ይልቅ ጉድ ሳያደርገን ከቤታችን እናባረው» አሉ።

ሂሩት የእናትዋን አሳብ በመደገፍ፥ ‹‹እማዬ ልክ ናት፡፡ አልነገርኩዋች እንጂ ባለፈው ሳምንት ምን አደረገ መሰላችሁ? ተፈራ ሊጠይቀን መ ‹‹ሲጃራ ግዛልኝ›› ቢለው፥ ‹‹እኔ አሽከርህ አይደለሁም›› አለው፡፡ ተወው›› ሲለው፥ የተናገረው አልበቃ ብሎት፥ ‹‹እኔ ካንተ አንሼ፥ አንተ በልጠህ የምንታይበት ምክንያት ምንድነው? አንተም ሰው፥ እኔም አንበላለጥም፡፡ ሱፍ ብትቀያይርና መኪና ብትነዳ ዋጋ የለውም!›› ብ ትከሻውን አሳይቶ ሄደ›› አለች፡፡

ኧረ! ለዚህም ደረሰ? ልቡ አብጦአል ብያለሁ፡፡ ነፃነት! እኩል የሚባሉትን ነገሮች ከሰሙ ወዲህ የድሆች ልብ ተነስቶአል፡፡ ድሀ በሀል ቅቤ ባይጠጣ አመዱ ይውጠው ነበር አሉ! የለም፥ ይህን መርዝ ከዚህ ካልነቀልን አይሆንም›› አሉ ወይዘሮ አምሳለ፡፡

እዚህ ላይ ሂሩት አልዋሸችም፡፡ ፈጥራ አልነበረም የተናገረችው፡፡ ደ የተፈራን አይን ማየት አይወድም፡፡ ከሂሩት ጋር ባየው ቁጥር አይኑ ይለብሳል፡፡

ሂሩት፥ ‹‹መቼ ይህ ብቻ ሆነና!›› ብላ፥ ‹‹በቀደም እለት ደግሞ በላ ሲመጣ ከበር አባረረው፡፡ ዱላም ቃጥቶት ነበር›› አለች፡፡

‹‹ይህችን ይወዳል! የራስ ደስሜን ልጅ! በምን ምክንያት በይ!›› አባትዋ ተቆጥተው፡፡

‹‹እኔ ምናውቃለሁ!›› ብላ አንገትዋን ወደ ቀኝ መታ አደረገች፡፡

‹‹ያስር መናጢ ልጅ! እዚህ ምን አይነት ሰው እንደሚመጣ የት ያውቃልና ነው! ጥሩልኝ! አሉ፥ አባትዋ በቁጣ፡፡

ደርቤ ተጠርቶ መጥቶ ሁለት እጆቹን ወደ ሁዋላ በማጣመር አቀ ቆመ፡፡

‹‹በምን ምክንያት ነው በል ሰዎች ሲመጡ አላስገባም እያ የምታስቸግረው! ያባትህ ቤት መሰለህ! በል ተናገር እስ!›› አሉት፡፡

ከአሽከርነትና ከስቃይ ከመገላገል ሌላ! እና ይዤያት ወደ መቃብር ብወርድስ? እንጆቴን እንዳላረረችው እንጆትዋን በጥሼ. .

«ግሩም ነው ከሚወድዋት ጋር ተያይዞ ወደ መቃብር መውረድ» እያለ በማሰብ ገድሎአት ለመሞት ሊቆርጥ ሲል፥ «የለም መጀመሪያ ሰው መሆኔን ማወቅ አለባት፡፡ አሳያታለሁ! ሰው የማይሆን የለም!» ብሎ ጋደም በማለት፥ ለህይወቱ እቅድ ያወጣ ጀመር፡፡

አስቀድሞ ጭንቅላቱ ውስጥ የገባ ነገር ቢኖር እግሩ ወደ ወሰደው አገር ኮብልሎ መጥፋት ነበር፡፡

ደርቤ ስለ ህይወቱ እቅድ በሚያወጣበት ወቅት አቶ ጉልላት በጠባዩ መለወጥ እየተገረሙ፥ «ያሳደግነው ልጅ ነው፡፡ ዝም ብለን ከቤት እናስወጣው ነው የምትይው» አሉዋቸው ባለቤታቸውን፡፡

«እባብ አንገትህ ላይ ጠምጥመህ ኑር፥ አንተ ከፈለግህ! እኔ ከዛሬ ወዲህ በቅቶኛል» አሉ፥ ቆጣ ብለው፡፡

«ጨንቆኝ ነው. . .»

«ስለገረፍከው አዘንከለት መሰለኝ! አዛኝ ቅቤ አንጓች ይላሉ፡፡ ድሀን ልክ ካላስገቡት የሰው ልክ አያውቅም፡፡ የሚያዝንላቸውን አይወዱም፡፡ አንተ አዲስ ሆኖብህ እንደሆን ነው እንጂ ዘሮቼ ሲገርፉ ነው የኖሩት ወዳጄ! ያኔ አገርም ሰላም ነበር» አሉ፥ ባለቤታቸውን በንቀት እየተመለከቱ፡፡

«የምልሽ አልገባሽም፡፡ ከኛው ጋር ይኑር ማለቴ አይደለም፡፡ ግን ውስጠ አዋቂ ነው፡፡ ጊዜውም አያስተማምንም፡፡ ወታደሩ እንደ ገና ማጉረምረም ጀምሮአል አሉ፡፡ አገሪትዋ ጤና የላትም፡፡ በሰላም እንሸኘው ማለቴ ነው» አሉዋቸውና ትራሳቸውን አመቻቹ፡፡

«ደብድበህ አባረው ማን አለህ!»

«ሰው የሚልሽን አትሰሚም! መሳሪያ እንደ ደብቅን ያውቃል፡፡ በሁዋላ አደገኛ ሰው ሊሆን ይችላል፥ አስቀይመን ካባረርነው፡፡ ስራ እናስይዘው ነው የምልሽ. . .»

‹‹ቀውጢ ቀን!›› አለ፥ ከሂሩት ጋር የተጋደመበትን ጥቂት ደቂቃዎች ካንጀቱ እየረገመ፡፡

‹‹ህይወቴን የለወጡ ጥቂት ደቂቃዎች›› ብሎ አሰበና፥ ያን ቀን ሞቼ ባረፍኩት ኖሮ ይህ ሁሉ አይደርስብኝም ነበር›› በማለት እድሉን ከፋፍ ካማረረ በሁዋላ፥ ‹‹ያ ጭንዋ ባይለክፈኝ! እግዜር ይይላት!›› ብሎ ተራገመ፡፡

‹‹ባትለክፈኝ! እንዲሁ በልቤ እየወደድኩዋት ብኖር፤ ቀዝቃዛ ህልሜ አለም ዛሬ እንደተሰበረ መስተዋት ደቆ ከፊቴ አይፈስም ነበር. . . ያን ቀዝቃዛ ፍቅር ጊዜ በሻረው ነበር. . . አሁን ግን ዘለአለም የማይድን የልብ ቁስል. . . የጥቂት ደቂቃዎች ቅርስ›› እያለ ሲያስብ ቆይቶ፥ ሂዶ የመኝታ ቤትዋን በር አንኩዋኩዋ፡፡

በሩ አልተዘጋም ነበር፡፡ ገብቶ ዝም ብሎ ቆመ፡፡ ከመፅሄት ውስጥ ቀዳ ያውጣችውን ባለቀለም ስእል ግድግዳ ላይ በጥንቃቄ ስትሰቅል አገኛት፡፡ አይኑ እንደ ሀረግ የሚሳበውን ዳሌዋን ተከትሎ ወደ ስእሉ አመራ፡፡ የንብ ንግስት ስእል ነበር የምትሰቅለው፡፡ ስእሉ ደስ አላለውም፡፡ ምን ውበት አይታበት ይሆን? ብሎ ተገረመ፡፡

የሚላት ነገር ጠፍቶት የቀትር መጋኛ እንደ መታው ሰው ፈዞ ቆሞ ቀረ፡፡

ስእሉን ሰቅላ ጨርሳ በልዩ ስሜት ስትመለከተው ቆየችና ዞር ስትል ደርቤን በማየትዋ ደንግጣ፥ ‹‹በጣም አስደነገጥከኝ፡፡ ምን ትፈልጋለህ?›› ብላ በቁጣ ቃል ጠየቀችው፡፡

‹‹ልሰናበትሽ ነው የመጣሁት፤ አሁን መሄዴ ነው›› አላት፥ ስልቱን ባጣ ድምፅ፡፡

‹እረ! መሄድህ ነው?›› አለች፥ ያለምንም ስሜት፡፡

‹‹አዎን›› ብሎ መለሰላት፡፡

‹‹እኬ፥ ቻዎ›› አለችውና ጀርባዋን ሰጠችው፡፡

[illegible]

[illegible]

[illegible]

[illegible]

Scanned with CamScanner

ጥምብ ወድቆ ማን ቆሞ ሊጠብቅ? የህሊና ልቅሶ ቦታ የለውም:: የማን ህሊና ሊያለቅስ እየገነና! በተራማጅ ቃላት ተሸፋፍኖ ይቅረብ እንጂ በመሰረቱ አብዛኛው የሚታገለው ለጥቅሙ ነው - ለስልጣን፣ ለእድገት፣ ለደመወዝ ጭማሪ:: ጥምብ ወድቆ የለ! እንደ ጆፌ አሞራ ጠንካራው ደካማውን እየገፋ ለመብጫቅ:: በውይይት ክበቦች አካባቢ የሚታየው ስነ-ልቡናዊ ክስተት ይሄው ነው:: ጠንካሮች ይኖራሉ፣ ደካሞች ይወድቃሉ:: ታዲያ እኔን ምን አስጨነቀኝ፣ በማለት ለድርጊቱ የሚያፅናና ምክንያት ለመፍጠር መሞከር ከጀመረ ውሉ ቢያድርም፣ ራሱን ሙሉ በሙሉ ለማሳመን እያቃተው ይቸገር ነበር::

አንድ አርብ ቀን፣ ከሰአት በሁዋላ - ቢሮው ሲገባ፣ ከሱ ቢሮ ለጥቃ የምትሰራው ፀሐፊ ሰአትዋን እየችና፣ ‹‹አንድ ደቂቃ ወደ ፊት ወይም ወደ ሁዋላ ዝንፍ አትልም:: ሰአቴን የማስተካክለው ባንተ ሆኖአል›› አለችው፣ እየተቅለሰለሰች::

ሰላምታ ከመለዋወጥ ሌላ ተነጋግረው አያውቁም:: ከነገርዋ ትዝ የሚለው ሽቶዋና ልብ ወለድ መፅሀፍ አዘውትራ የማንበብ ልምድዋ ነበር:: በተለይም፣ የምትቀባው ሽቱ ክፍሉን እውድ ያደርጋል:

ሰአቱን ተመለከተ:: ለዘጠኝ ሩብ ጉዳይ ሆኖአል:: ሁኔታውን በመከታተልዋ እየተገረመ፣ ‹‹ልማድ ሆኖብኝ ነው መሰለኝ›› አላት፣ የተሻለ መልስ ሊሰጣት ባለመቻሉ ቅር እያለው::

ማስቲካ እያኘከች መፅሀፍ ታነብ ነበር:: የምታመነዥክ ፍየል መስላ ታየችው::

መስቲካዋን ቀጭ ቀጭ ቀጭ አደረገችና፣ ‹‹እንደማይህ መካኒካዊ ህይወት ነው የምትኖረው›› ብላው፣ የከንፈር ቀለምዋን ላሰችና፣ ‹‹ዛሬ ይዘገይ ይሆን? ወይስ ቀደም ብሎ ይመጣ ይሆን? እያልኩ ሁልጊዜ ከራሴ ጋር እወራረዳለሁ›› አለችው::

ቤትዋ በጣም ሩቅ ስለሆነ ለምሳ አትሄድም:: ከፀሀፊ ደመወዝ ግማሹን ላሲይቼንቶ ላለማስረከብ ስትል ነበር ቢሮ ተጎልታ የምትውለው:: የምታነበውን መፅሀፍ አጥፋ ማስቲካዋን ቀጭ ቀጭ አደረገችና፣ ፍንጭትዋን እያሳየችው፣ ‹‹ታዲያ ይሄውልህ፣ ስለ ጊዜም ማሰብ የጀመርኩ ባንተ ምክንያት

ያ የተገረፈበት አኮርባጅና ቤት በሚያፀዳበት ጊዜ ሁሉ እየወዘ የሚያስቸግረው ባለ ስገባ ጎራዴ እዚያው ግድግዳ ላይ እንደተሰቀሉ ነበሩ።

‹‹ሻይ ወይም ቡና?›› ስትለው ገረዲቱ፥ ስለ ሳሎኑ ያለውን ትግ አቁዋረጠና የጠየቀችውን ትቶ፥ ‹‹ሂሩትን ነበር የምፈልገው›› አላት።

ገረዲቱ በልብዋ፥ ያልሰማ ጆሮ ከጎረቤት ያጣላል. . . እስዋ ፈላጊዋ ብዙ እንደ ጳጉሜ ውሻ. . . ኤጭ. . . ግን ምን ብታቀምሳቸው ይሆን? ጠዋ ማታ እየመጡ ሂሩት. . .ሂሩት የሚሉኝ! እያለች በልብዋ ስትመናጨ ወጣች. . .

ሙዚቃ ይሰማዋል። ከሂሩት መኝታ ቤት ይሆናል ብሎ አሰበ። ያ የን ንግስት ስእል ትዝ አለው። ሂሩት ብቅ አለች። ከዳሌዋ ሰፋ፥ ከወገቡ ሽንቀጥ፥ ከደረትዋ ኮራ ብላለች። የንብ ንግስት መስላ ታየችው።

በመጀመሪያ ማን እንደሆነ አላወቀችውም። በስዋ አይን ምንም ህልው የሌለው መናፍስት እንደ ሆነ ያህል ሆኖ ነበር የተሰማው። ማራኪ ውበት ትዝ አለው። ላንዳፍታ፥ ‹‹ንከሰኝ. . .ጭምቅ አድርገኝ . . .›› ያለችው ጆሮ ውስጥ ደወለ። ግን ፈፅሞ የማታውቀው መስላ ፊቱ ቆማለች። ግራ ገባው.
.

ከረጅም ዝምታ በሁዋላ ነበር፥ ‹‹ደርቤ ነህ እንዴ?›› በማለት ከንፈሯ የጥንቀት ማጥ ያፀነጣችው።

ረጅም መንገድ ተጉዞ የተመለሰ ያህል ሆኖ ነበር የተሰማው። ለዚያ ጥቂት ሴኮንድ በመሰከላቸው የተፈጠረው ርቀት የማይለካ ነበር።

‹‹ሂሩት፥ ልጠይቅሽ ነው የመጣሁት!›› ካላት በሁዋላ፥ ትኩረትዋን ወሀ በደብልጥ ለመሳብ ተቻኩሎ፥ ‹‹ተዳፈርክ ባትይኝ፥ ስጦታ ብዙ አምጥቼልሻለሁ›› አላትና ፥ አምባሩን ከኪሱ አውጥቶ ሰጣት።

ስሜት አልሰጣትም። አምባሩ ያለበትን ትንሽ ሳጥን ከፍታ፥ ምን አይነ ስጦታ እንዳመጣላት ለማየት እንክዋን አልፈለገችም።

‹‹ምን አሳሰበህ›› ብላ ዝም አለች።

እንቅልፍ እምቢ አለው። አይኑን በከደነ ቁጥር ምድርና ሰማይ ይገለባበጥበታል። የተኛበትም አልጋ መሬት ለቆ ይንሳፈፋል። በሀይል ቢያፈጥም አልሆነለትም። መጠጡ ልቡ ላይ እየፈላ መጥቶ በድንገት እን እሳተ ጎሞራ ፈነዳ. . .

ሲፈራ ሲቸር አይኑን ከደነ። እንቅልፍ ወሰደው። ጠዋት ሲነቃ ሐ ምታት ይዞ ይወቅረው ነበር። አንጎሉ ከራስ ቅሉ የተላቀቀ ይመስል ቀ ጎንበስ ባለ ቁጥር ጭንቅላቱ ይንቦጫቦጭ ነበር። የእጅ ቁስል ቆጠቆጠው፡ አዲስ መስተዋት መግዛት አለብኝ ብሎ አሰበ. . .

ቢሮው ሲደርስ፥ ፍኖት በአይንዋና፥ በቅንድብዋም ጭምር እየተናገረች ‹‹ምን ነው ዘገየህ ልጄ! የሞትክ መስሎኝ ነበር›› አለችው - በስሜት።

‹‹መካኒካዊ ህይወት ነው የምትኖረው›› ያለችውን እያስታወ ‹‹መኪናው አንዳንዴ ይቆማል›› አላት።

‹‹በዋድባም አንዳንዴ ይዘፈናል፥ ብትል ይሻል ነበር›› አለችና፥ ‹‹እህት አምባሩን ወደደችው?›› ብላ ጠየቀችው። ስታነብ የነበረውን መፅሀፍ ቀና አድርጋ።

ልብ ወለድ መፅሀፍ ከጠረጴዛዋ ላይ አይጠፋም። ሹራብ በማትሰራበት ጊዜ ሁሉ መፅሀፍ ማንበብ እንደምታዘወትር ያወቀው ካነጋገረችው ጊዜ ወዲ ነበር።

በመስኮት ወደ ውጭ እያየ፥ ‹‹በጣም ነው ደስ ያላት›› አለ የሱ ባልሆ ድምፅ።

ፊቱ ላይ የሚመላለሰውን ያልተዛመደ ጥላ አይታ ፍንጭትዋን ዘ አደረገችና፥ ‹‹ታዲያ ለምን ከፋህ?›› አለችው።

ደርቤ ትናንት የለበሰውን ልብስ አልቀየረም። ሆኖም ልብሱና ሰማ ነልተጣጣሙላትም። አምባሩን የገዛው ለእህቱ እንዳልሆነ ተጠራጠረች።

የቀይ ነገሩ...

«የከፋኝ እመስላለሁ?›› አላት፣ ወደ ውስጥ ጠልቀው የማየት ችሎታ ያላቸው የሚመስሉትን እንቁ መሳይ ብልጣ ብልጥ ትናንሽ አይኖችዋን እያሸሸ::

ፍኖት፣ አንድ አመል ነበራት:: የጀመረችውን መፅሀፍ ሳትጨርስ መተው አትወድም:: የታሪኩን መጨረሻ ሳታውቅ ስትቀር ያበሳጫታል:: መፅሀፍ ማንበብ ስትጀምር የታሪኩ ፍፃሜ ምን እንደሆነ ለማወቅ ትቸኩላለች:: ያንድ ልብ - ወለድ ውበት ከታሪኩ አፈፃፀም ላይ ነው ብላ ስለምታምንና ፍፃሜውን ለማወቅ ስለምትቸኩል፣ ስለ መፅሀፉ ይዘትና አላማ እምብዛም ግድ አልነበራትም::

ምስጢሩን ለማወቅ ፈልጋ ልብዋ ቆመ:: ደርቤም ምስጢራዊ ሆነባት:: እምባሩ ለእህቱ ከሆነ ለምን ከፋው? ካልሆነስ ለማን ነበር የገዛው? ማን አባትዋ ናት የኔን ምርጫ የምትንቀው? ወይስ ማን አጋዛህ ብላ ስትጠይቀው በምኝነት ነግሮአት ቀንታ ይሆን ያስቀየመችው? ታሪኩ ጣፈጣት:: የመጨረሻውን ለማወቅ ፈለገች::

በአይንዋ፣ በቅንድብዋ፣ በእጆችዋም ጭምር እየተናገረች፣ «ከእህትህ ጋር ሳይገጥም ቀርቶ፣ ምርጫዬ ሳያስደስታት ቀረ መሰለኝ!›› አለችው - ኮከባችን እያሾፈች::

ሂሩት፣ «ምን አሳሰበህ›› ያለችውን በማስታወስ ውስጥ ውስጡን እየበሸቀና በፍኖት ገደ-ቢስነት እየተናደደ፣ «በምርጫው በጣም ነው የተደሰተችው›› አላት፣ ቃላቱን እያኘከ::

የታሪኩ ፍፃሜ ምን እንደሚሆን ሳይገልፅ አንግቢን እየሳበ እንደሚሄድ ልብ - ወለድ አድርጋ አነበበችው:: አንዳንድ መፃህፍት ሲያስለችዋት ብዙ ምእራፎች ዘላ የመጨረሻውን ምእራፍ እንደምታነብ ሁሉ፣ የእውነቱን እንዲነግራት ፈልጋ «እውነት እሰዋ ማን ናት?›› ብላ ልትጠይቀው ነበር::

ላስቸከዋይ ጉዳይ ትፈለጋለህ ተብሎ ተጠርቶ ሄደ:: ታሪኩ ተንጠልጥሎ ስለቀረባት ተናዳ ጥርስዋን ነከሰች::

በሳምንቱ መጨረሻ ላይ፥ አርብ ከሰአት በሁዋላ ጠበቀችውና፥ ‹‹ጌታሁን ከዳህ አይደለም እንዴ? ወይስ እሱ ነው የከዳህ?›› አለችው፥ ጾታ የሚመስሉትን ትናንሽ ሳቂታ አይኖችዋን እያቁለጨለጨችበት፡፡

ባንዳፍታ አመዱ ቡን ብሎ፥ ‹‹የምን ጌታ?›› አላት፡፡

‹‹ጌታ›› ስትል ቶሎ ጭንቅላቱ ውስጥ የገባው የአስተዳደሩ ሹም ነበር፡፡

‹‹ጊዜን ማለቴ ነው›› አለችውና ፍንጭትዋን ብልጭ አደረገችበት፡፡

ከባድ ሸክም ከጀርባው እንደ ወረደለት ሰው በረጅሙ ተነፈሰና፥ ‹‹አንቺስ - ከመፅሀፍ ጋር ተጣላሽ?›› አላት፥ ለለውጥ ያህል መፅሀፍ በእጅዋ አልነበረም፡፡

‹‹የጀመርኩን ሳልጨርስ ሌላ መጀመር አስጠልቶኝ ነው. . . ሁለት መፅሀፍ ባንድ ጊዜ የማንበብ ልምድ የለኝም፡፡ ግን አንዱ ሲሰለቻቸው ወደ ሌላው እየዞሩ ባንድ ጊዜ ሁለት ሶስት መፃህፍት የሚያነቡ ሰዎች አሉ፡፡ እኔ እንደነሱ አይደለሁም፤ የጀመርኩትን ሳልጨርስ ወደ ሌላ መጋባት አልችልም›› አለችውና፥ ስትሻው የነበረው ዘዴ ድንገት ብልጭ ስላለላት ፈንድቃ፥ ‹‹ነገ ቲአትር ቤት አብረን ለምን አንገባም? ሁለት ቲኬት አለኝ፡፡ የማውቀው ደራሲ ነው፡፡ ቲአትሩን ለህዝብ ሲያቀርብ የመጀመሪያው ጊዜ ስለሆነ ያልጋበዘው ሰው የለም. . .›› ብላ ንግግርዋን ሳትጨርስ አቋረጣትና፥ ‹‹ሁሉን በነፃ ከጋበዘ ገንዘብ ከየት ሊያገኝ ነው ታዲያ?›› አላት፥ ስሜትዋ ተጋብቶበት፡፡

‹‹እምአእላፍ ለገንዘብ አይጨነቅም፡፡ ከድርሰት ሌላ ህይወት የለውም›› አለችና፥ ስለ እምአእላፍ ያላትን ትዝታ አስታውሳ፥ ‹‹የማንበብ ፍቅር እንዲያድርብኝ ያደረገኝ እሱ ነው፡፡ ለማንኛውም ነገር ድርሰቱ ጥሩ ይሁን አይሁን አላውቅም፡፡ የኬክ ጣፋጭነት የሚታወቀው ሲቀምሱት ነው ይባላል፡፡ ድርሰቱ ጥሩም ባይሆን ጥረቱን እናደንቅለታለን፡፡ እምአእላፍ ስለ ድርሰት ማውራትና መስማት በጣም ይወዳል፡፡ ዘጠኝ ወር ተሸክማና አምጣ ስትወልድ፥ ገና የምጥ ስቃይ ሳያልፍላት ህፃኑን በፍቅር አይን እንደምታይ እናት አይነት ነው ስሜቱ፡፡. . . ከኔ ጋር ትመጣለህ? እዚሁ ማዘጋጃ ቤት ቲአትር አዳራሽ ነው በዘጠኝ ሰአት›› ብላ፥ ፍንጭትዋን ብልጭ፥ አይኖችዋን

ቀልጭልጭ፥ ቅንድብዋን ከፍ ዝቅ አድርጋ ስሜቱን ባንድ ጊዜ አተረማመሰችበት፡፡

ደርቤ ቲአትር ቤት ገብቶ አያውቅም፡፡ ለድርሰትም ደንታ አልነበረውም፡፡ ግን እምቢ ሊላት አልቻለም . . .

ቀደም ብሎ ሂዶ ከአፄ ምኒልክ ሀውልት አጠገብ ወደ ማዘጋጃ ቤቱ ቲአትር ቤት ከሚያስገባው በር ላይ ሲጠብቃት ቆየ፡፡ ፀሀያማ ቀን ነበር፡፡ የተነደፈ ጥጥ የሚመስሉ ስስ ደመናዎች ከጠራ ሰማይ ላይ ተንጣለው ይታያሉ፡፡

ሂሩትን እያሰበ ቆሞ ሲተክዝ፥ ፍኖት ከሁዋላው መጥታ ማጅራቱን ነካ አደረገችው፡፡ ባንኖ ዞር አለ፡፡

‹‹ብዙ እንዳላስጠበቅሁህ ተስፋ አደርጋለሁ›› አለች፥ ፍንጭትዋን ብልጭ አድርጋ፡፡

ፊትዋ ላይ የሚታየው የጋለ ስሜት የፀሀያማው ቀን ነፀብራቅ ይመስላል፡፡ ሽቶዋ አፍንጫውን እውድ አደረገው፡፡

ነጭ ሱሪና አንገቱ ክፍት የሆነ ስስ ጥቁር ሹራብ ለብሳለች፡፡ የጡት ማያዣዋ በትንሹ ብቅ ብሎ ተመልካችን ይጠቅሳል፡፡

‹‹ሁልጊዜ ሱሪ የምትለብሺው ለምንድር ነው?›› ብሎ ጠየቃት፡፡ ቀሚስ ለብሳ አይቶአት አያውቅም፡፡

‹‹ያስጠላብኛል!›› አለችው፥ ወደ ቲአትር ቤቱ አዳራሽ ማምራት እንደ ጀመሩ፡፡

‹‹ያምርብሻል›› አላት፥ ከልቡ፡፡

ለብዙ ጊዜ እንደሚያውቃት ሆኖ ነበር የሚያነጋግራት፡፡

‹‹ለመከላከል ይረዳኛል ብዬ ነው ሱሪ የማዘወትረው፡፡ ወረሀ እግሬን ለመሸፈን ስል አይደለም›› ብላ ፈገግ አለች፡፡

‹‹ከምንድር ነው የምትከላከይው?››

የመድረኩ መብራትና ትእይንት ስለሳበው ደርቤ ፈዞ ቀረ። ሁኔታውን ስላየች፥ «መድረክ እኔንም ይስበኛል። የህይወት ቀንዕል ገፅታ ነው። ህይወት ራስዋ ሰፊ መድረክ ናት። ግን፥ የሚያሳዝነው የኛ ቲአትር ቤት መድረኮች ባዶ መሆናቸው ነው። ሁኔታው የህይወታችን ባዶነት ነፀብራቅ መስሎ ነው የሚታየኝ» አለችው።

ቲአትሩ አልተጀመረም። መጋረጃው የተከፈተው ድምፃውያኑ ተወዛዋዦችን ለማቅረብ ነበር። ፍኖት አልተደሰተችም። ድምፃውያኑ ከጥሩንባ ጋር፥ ድምፃውያኑና ጥሩምባው ደግሞ ከተወዛዋዦች ጋር ሲፎካከሩ መስማትና ማየት አስጠላት። ኩዋስ አበደች ተብሎ ጥለዛ የሚቀልጥበት የልጆች ጨዋታ መስሎ ነበር የሚታያት። የዘፈኑ መልእክትና የድምፃውያኑ ውዝዋዜ መቁነጥነጥና እጅ ማወናጨፍ ስላልተጣጣሙላት ተበሳጭታ ነበር፡ ቲአትር ያለ ኦርኬስትራ አጀብ ተመልካችን መሳብ የሚችልበት ጊዜ መቼ ይመጣ ይሆን? ብላ በልብዋ ተመኘች።

የሙዚቃው ክፍለ ጊዜ እንዳበቃ ፍኖት ጆሮዋን ኮረኮረችና፥ «ጥለዛው እንዴት ነበር?» አለችው።

ደርቤ ፈዞ ቀርቶ ነበር። ከመድረኩ ላይ አይኑን አልነቀለም።

«የምን ጥለዛ?» አላት፥ በግማሽ ልብ።

«ሙዚቃውን ማለቴ ነው» አለችው።

«ጥሩ ነበር» አላት፥ ኮስተር ብሎ።

«እንኩዋን ወደድከው። በሙዚቃና በቀለም አይነት መከራከር አይቻልም። የስሜት ጉዳይ ነው» ብላ ዝም አለች።

ስለ ኪነት አንዳንድ ነገሮችን ለመገምገም እንዲችል ባደርገው ጥሩ ነበ ብላ በልብዋ አሰበች። መፅሀፍ እያነበበን አሳብ ለአሳብ ለመለዋወጥ ብንችል እያለች ስታስብ ለደርቤ ያላት ስሜት ተማታባት። መጋረጃው ሲከፈት አልታወቃትም።

ባለስልጣኖች ከቢሮአቸው እንደ አይጥ እየተሽሎከሎኩ ይወጣሉ-ይገባሉ. ይደናገጣሉ-ይርበተበታሉ-የሚይዙትንና የሚጨብጡትን ያጣሉ። ብርሃኑ እያየለ ይሄዳል-እየፈካ-እያጥለቀለቀ. . .

ባለስልጣኖች ሲገቡና ሲወጡ ተላላኪዎች እጅ አይነሱም። ከተቀመጡበት አይነሱም። ባለስልጣኖች፥ ‹‹ጉዋዶች! ጉዋዶች!›› እያሉ እጅ ይነሳሉ። በገቡና በወጡ ቁጥር የጋለ ሰላምታ ያቀርባሉ። የደመቀ ፈገግታ ያሳያሉ።

ደወል. . .ደወል. . . የተለመደው ማኪያቶ፥ ሻይ ቡና፥ አምቦ ውሃ. . . ደወሉ ጋብ ሲል ተላላኪዎቹ አለቆቻቸውን ባወጡላቸው ቅፅል ስም እየጠሩ፥ እያንዳንዱ አለቃ በምን ሁኔታ እንዳደረ፥ ስብሰባ ላይ ነኝ በማለት በር ዘግቶ ምን በመስራት ላይ እንዳለ፥ አለቃና ፀሀፊ ምን በማድረግ ላይ እንዳሉ መግለፅ ይጀምራሉ።

ሆዱን እያከከ፥ ‹‹አለቃዬ የአራት ብር ከስድሳ ሳንቲም ሲጃራ በቀን ሲያጤስ እኔ ጥሬ አርብኝ አካለሁ›› እያለ በመደጋገም የሚናገረው ቀዳሚ ተዋናይ፥ አለቃው ቢሮ ገብቶ ሌሎች ተላላኪዎች ስለሱ የሚሉትን ሲነግረው ሲጀምር ቀልዱ ይለወጣል። ደርቤም መሳቅ ያቆመው ከዚሁ በሁዋላ ነበር።

ሁለተኛው ክፍለ ትእይንት፥ በውይይት ክበብ ስብሰባ ላይ፥ ‹‹ማን ነው ይሁዳ? ጭቁን ሆኖ ለጥቅም ጭቁኖችን አሳልፎ የሸጠ? ማን ነው እለ መደቡን የከዳ? በሚል ሀይለ ቃል ይጀምራል።

‹‹እና አድሃሪ ቢሮክራቶች ውይይት ክበቦችን እንደ ጦር ይፈራሉ ውይይት ክበቦችን ለማፍረስ የማይሸርቡት ሴራ የለም። ታዲያ እኛኑ ነው መልሰው መሳሪያ የሚያደርጉት - በይሁዳዎች እየተጠቀሙ. . .

‹‹ለስልጣን የቁዋመጡት ቡድኖችም መሳሪያ ሊያደርጉን ይፈልጋሉ እርስ በርሳችን እየከፋፈሉን. . .

‹‹ለግል ጥቅም የሚያሰፈስፉት መሳሪያ ሊያደርጉን ይፈልጋሉ እድምተኞቻቸው እያደረጉን. . .

‹‹ግን ውይይት ክበቦች የሰሬው ጭቁን ሰራተኛ ብሄራዊ ትምህርት ቤቶች ናቸው፡፡ እንማራለን! ከትግል እሳት ተፈትነን እንወጣለን! እናሸንፋለን! ይሁዳዎች ይወድማሉ!››

ደርቤ ዝም ይላል፡፡ ያልበዋል፡፡

በቲአትሩ መጨረሻ ላይ፥ ቀዳሚው ተዋናይ እንደ ይሁዳ እየተቅበዘበዘ ሂዶ በገመድ ራሱን ሲሰቅልና አሰቃውም እንደ ጲላጦስ እጁን ሲታጠብ መጋረጃው ይዘጋል. . .

የደርቤ ሰውነት ነፋስ እንደ መታው ቅጠል ይርገፈገፍ ነበር፡፡ ፍኖት ስለ ደርቤ ሁኔታ አላጤነችም፡፡ እምአእላፍ በቲአትሩ ምን መልእክት ለማስተላለፍ እንደ ፈለገ ነበር የምታሰላስለው፡፡

ከቲአትር ቤቱ አዳራሽ ወጥተው ደረጃውን ከወረዱ በሁዋላ፥ እምአእላፍ ከመውጫ በር ወደ ቀኝ ሲል ካለው ቡና ቤት ባንኮኒ ላይ ተደግፎ ሻይ ሲጠጣ ፍኖት ስላየችው፥ ወደሱ ሄደችና፥ ‹‹እንኳዋን ደስ አለህ፡፡ ጥሩ ነበር›› አለችው፡፡

‹‹ኤጭ!›› አላትና እጁን አወናጨፈ፡፡

ደርቤን አስተዋወቀችው፡፡

‹‹እ ያ ተጀምሮ ያላለቀ መፅሀፍ!›› አላት፥ መነፅሩን በጣቱ ካፍንጫው ላይ ወደ ላይ ገፋ አድርጎ፡፡

ደርቤ አልገባውም፡፡ ያ ሁሉ ሀይለ ቃል ከዚህ ስንጥር መሳይ ሰው እንዴት ሊወጣ ይችላል? እያለ ነበር የሚያስበው፡፡

እምአእላፍ አንድ ሀሙስ የቀረው ይመስላል፡ አንገቱ እንደ ሲባጎ ሲል ባላ ትታያለች፡፡ አንጀቱ ከጀርባው ጋር የተጣበቀ፥ ደረቱ የሰመጠ፥ ትከሻው የጎበጠ፥ ጠይም ፊቱ ጨጎጎት በሚመስል ጢም የተሸፈነ፥ ጠጉሩ ከመጠን በላይ ያጎፈረ ነበር፡፡ አይኖቹ ጥልቀት ካለው ጉድጉዋድ ውስጥ እንደሚታይ ውሀ ከመነፅሩ ሁዋላ ጭል ጭል እያሉ ይታያሉ፡፡ ከወሎ ረሀብ እልቂት እምልጠ ገና በማገገም ላይ ያለ መስሎ ታየው - ለደርቤ፡፡

ህብረተሰቡ በንቃት አይን ቢመለከተንና ዋጋ ባይሰጠን አይገርመኝም፡፡ ሀቅን ያልጨበጠ ኪነት ዋጋም ሆነ ዘላቂነት የለውም፡፡ የታሪክ አተላና ዝቃጭ ሆኖ ይቀራል. . .

«ለኪነት ዘላቂነትና ውበት የሚሰጠው ሀቅ ነው፡፡ ያለ ሀቅ ኪነት የለም፡፡ ኪነ ጥበባችን ድሀ ሆኖ የቆየው፥ ሀቅን ጨብጦ ባለመገኘቱ ነው፡፡ ይገባሽ እንደሆነ የምበሳጨው ለዚህ ነው. . .

«ለሀቅ ስለ ሀቅ መፃፍ አልችልም፡፡ ቲአትሬን እንደተመለካች ሁኔ ሳየው ሊያስታውቀኝ ነበር፡፡ ለምንድር ነው የፃፍኩት? ብዬ ራሴን ስጠይቅ ነው የመጣችሁት፡፡ ቴአትሩን ያቀረብኩት የህብረተሰቡን ሀቅ ለማንፀባረቅ እንዳልነበረ ገባኝ፡፡ ለዝናና ለገንዘብ ስል ነበር ማለት ነው፡፡ እና፥ ራሴን ታዘብኩት፡፡ ራሴን ጠላሁት›› አለና በረጅሙ ተነፈሰ፡፡

ደርቤ የሚያስበው ስለ ሌላ ነገር ነበር፡፡ በድንገት፥ «ዋናው ተዋናይ ራሱን እንዲሰቅል ለምን አደረክ? አለው፡፡

እምአእላፍ ፈገግ ሲል ደስ ይላል፡፡

«እኔ አይደለሁም እንዲሰቀል ያረኩት፡፡ ራሱ ነው›› አለው፡፡

«አንተ አይደለህም እንዴ ደራሲው?››

«ነኝ፡፡ ግን የፈጠርኳቸው ገፀ ባህርያት ከተፈጠሩ በሁዋላ፥ የየራሳቸው ህልውና አላቸው፡፡ወደሚፈልጉት አቅጣጫ ይመሩኛል እንጂ እኔ እንደ አሻንጉሊት አልጫወትባቸውም፡፡ የኔ ሚና የነሱን አስተሳሰብ፥ ስሜት፥ ፍላጎትና ውሳኔ ተከትሎ መፃፍ ነው›› ብሎ ሲያበቃ ለጠቀና፥ «በመሞቱ አዘንክለት መሰለኝ›› አለው፡፡

«መደቡን የከዳው ባለማወቁ ነው፡፡ መሞት አልነበረበትም!›› አለ ደርቤ፥ በድንገት ድምፁን ከፍ አድርጎ፡፡

ፍኖት ተገርማ ትኩር ብላ ተመለከተችው፡፡ የደም ስሮቹ ተገታትረው መልኩ ተለውጦ ነበር፡፡

‹‹ምናስቆጣህ ጃል! እኔ አልገደልኩም። ሲሞትም አላማከረኝም። ለመሞት ፈለገ - ሞተ። የኔ ሚና የያንዳንዱን ሰው ሀቅ ማቅረብ ነው›› አለና፥ ጫት አውጥቶ ጎረሰ።

‹‹አንድ ነገር አስታውሶት ይሆናል የተቆጣው›› አለች ፍኖት፥ በጥርስዋም በአይንዋም እየሳቀች።

ደርቤ በቁጣ፥ ‹‹ምንም ያስታውሰኝ ምን መሞት አልነበረበትም!›› ካለ በሁዋላ፥ ወደ እምአእላፍ እያተኮረ፥ ‹‹ምን ለማስተማር ነው የፃፍከው?›› አለው።

‹‹ምንም። እኔ አስተማሪ አይደለሁም። ማስተማር የደራሲ ተግባር አይመስለኝም። የኔ ተግባር ሀቅንና ውበትን መሻት ነው›› አለው፥ ድርሰቱ ከተመልካቾች ውስጥ ያንዱን ስሜት በመንካቱ እየተደሰተ።

ደርቤ ትእግስቱን ጨርሶ ነበር። የተናደደው በእምአእላፍ ሳይሆን በራሱ ነበር። መሪ ተዋናዩ እንደ አበደ ውሻ እየተቅበዘበዘ ሂዶ ራሱን ሲሰቅል ባሳቡ እየታየው የመንፈስ እረፍት አጥቶ ነበር። ወደ ፍኖት መለስ ብሎ ‹‹እንሂድ!›› አላት።

እምአእላፍ ከደርቤ ለመለየት አልፈለገም ነበር። ‹‹ፍኖት እንዳልጨረሰችው መፅሀፍ ታየው ይሆናል፥ ለኔ ግን ደስ የሚያሰኝ ባህርይ ነው›› ብሎ አሰበ።

እምአእላፍ ፈገግ ብሎ፥ ‹‹የጀመርሺውን ጥሩ መፅሀፍ ሳትጨርሺ ለእኔም ቸኩያለሁ አላውስሺም። እና ስለ መፅሀፉ ሌላ ጊዜ ታጫውቺኛለሽ። ዛሬ ምርቅን ማለት አለብኝ። ቻው›› ብሎአቸው ጫቱን እያኘከ ተለያቸው።

ደርቤና ፍኖት ተያይዘው ወጡ።

አፄ ምኒልክ አደባባይ አካባቢ ከድሮ ማዘጋጃ ቤት ፊት ለፊት ፍኖት ቀበና ብላ ሴይቼንቶ ካስቆመች በሁዋላ፥ ‹‹አትሸኘኝም?›› ብላ ደርቤን ጠየቀችው።

ደርቤ ምንም ሳይናገር ተከትሎአት ሴይቼንቶ ላይ ተሳፈረ። የተሳፈሩበት ሴይቼንቶ በደጃች ውቤ ሰፈር፥ በአፍንጮ በር፥ በየካቲት ፲፪ አደባባይ፥ አድርጎ ወደ ቀበና በፍጥነት ሲበር፥ ደርቤ ዝም ብሎ ስለ መሪው ተዋናይ መስቀል ያስብ ነበር።

ያባቱ ሬሳ ከወደቀበት ጫካ እንዲመጣ ተደርጎ ጢቆ ከተማ ላይ በገበያ ቀን መስቀሉ ትዝ አለውና፥ ሰውነቱን ዘገነነው። አይኖቹ እንባ አቀረሩ። በዚያ ቀውጢ ዘመን ከባለርስት ጋር ለመብቱ ሲታገል በጥይት ተደብድቦ የወደቀው አባቱ ከመቃብሩ ቀና ብሎ ቢያየኝ ምን ይለኝ ይሆን? ደረቅ ጡቶችዋ ደም እስኪወጣቸው ድረስ እያጠባችኝ፥ እስዋ ቆሎ አርባት አንጀትዋ ተጣብቆ የሞተችው እናቴስ ከድንጋይ ትራስ ላይ ቀና ብላ ብታየኝ ምን ትለኝ ይሆን? ብሎ አሰበ።

አባቴ ‹‹ወንበዴ ነው›› ተብሎ እንደ አውሬ ታድኖ ተገደለ። መብቱን አትንኩብኝ ከማለት ሌላ ምን ሀጢአት ሰራ! ይገርማል! እኔም ወንበዴነቱን አምኜና ተቀብዬ ነው እስከ ዛሬ የኖርኩት! አባቴ የሞተለትን አላማ የረገጥኩ ወንበዴ እኔ ነኝ። እስከ ዛሬ የት ነበርኩ? ሰው መሆን. . . አይ ሰው መሆን. . . ሞት ይገባኝ ነበር እንደ መሪው ተዋናይ. . . እያለ ሲያስብ የሴይቼንቶው መቆም አሳቡን አቋረጠው።

ከተሳፈሩበት ሴይቼንቶ ሲወርድ የተከሰተለት ነገር ቢኖር፥ ከእንግዲህ የተለወጠ ሰው መሆኑ ነበር። በዚያች ደቂቃ ብቻውን ለመሆን ተመኝቶ ነበር። ብቻውን ሆኖ ወደ ውስጡ በመመልከት ስለ ራሱ፥ ስላሳለፈው ህይወት፥ ስለ ወደፊት ኑሮው ስለ ሂሩት ለማሰብ ፈልጎ ነበር።

መንገድ ላይ ተሰናብቶአት ሌላ ሴይቼንቶ ይዞ ለመመለስ ሲያስብ፥ ፍኖት ቀድማው፥ ‹‹ቤቴ ቅርብ ነው። ሻይ ጠጥተህ ትሄዳለህ›› ብላው፥ ከሱ መልስ ሳትጠብቅ ወደ ቤትዋ ማምራት ጀመረች።

ተከትሎአት ሄደ።

ፍኖት የምትኖርበት ቤት ከዋናው መንገድ ትንሽ ራቅ ያለ ነበር። ቤትዋ ራሱን የቻለ አጥር ግቢ ሆኖ፥ ከቤቱ ፊት ለፊት ያለው ትንሽ መስክ በልዩ ልዩ አይነት የፅጌረዳ ተክል አይን ይማርካል። ከወንፊት ሽቦ የተሰሩ ሁለት

የዎፍ ጎጆዎች ከአበቦቹ መሀል ብቅ ብቅ ብለው ይታያሉ፡፡ ፍኖት አበቦችዋን በፍቅር አይን እየተመለከተች አልፋ ወደ ዎፍ ጎጆዎቹ ሄደችና፥ ምርቱ እህልና ውሀ እንዳላቸው ካየች በሁዋላ፥ ‹‹ሀኒንና ጆኒን ሳስተዋውቅህ›› አለችው ደርቤን፡፡

ሀኒና ጆኒ የመስቀል ዎፍ የሚመስሉ - ጅርባቸው ጥቁር ሀር፥ ልባቸው ወርቅማ የሆነ ውብ ነገሮች ነበሩ፡፡

ፅጌረዳ አበባዎቹ ፈንድተው ውበታቸውን ወደ ውጭ ገልብጠው በማውጣት እዩኝ እዩኝ እያሉ ደስ የሚለውን መአዛቸውን ከቀዝቃዛው አየር ጋር ደባልቀው በመርጨት ይስባሉ፡፡

ፍኖት በተመስጦ አበቦችዋን ከተመለከተች በሁዋላ፥ ‹‹ተፈጥሮ እንደ ሴት ናት፡፡ ሰውን የምትስብበት መንገድ አላት፡፡ ተፈጥሮ ውብ ሆና ውበትዋ ቆም ብለው የሚያደንቁና በውበትዋ የሚደሰቱ ጥቂቶች ናቸው፡፡ እና ተፈጥር ፍቅር የተነፈጋት ውብ ሴት ተመስላ ስለምትታየኝ፥ ታሳዝነኛለች እያለችው ቤት እንደ ገቡ፥ ‹‹መጣሁ›› ብላው ወደ ጉዋዳ ዘለቀች፡፡

እንግዳ ቤትዋ መጠነኛ ሆና በቀይ ሶፋዎች፥ በሰማያዊ የመስኮት መጋረጃዎችና በሰማያዊ ምንጣፍ ያጌጠች ነበረች፡፡ ውድ በሆኑ የአበባ ማስቀመጫዎች የፈነዱ ፅጌረዳ አበባዎች ተሞልተው አይን ከሚያርፍባቸው አንዳንድ ስፍራዎች ተቀምጠዋል፡፡ ከክፍሉ ውስጥ እጅግ ጎልተው የሚታዩት ግን የመፃህፍት መደርደሪያዎች ነበሩ፡፡

ከእቃዎች አቀማመጥ ጀምሮ በእንግዳ ቤቱ ውስጥ ለአይን የሚያስቀይም አንዳችም ነገር አይታይም፡፡ ሁሉም ነገር አይን የሚስብና የሚያስደስት የመንፈስ እረፍትንና ፀጥታ፥ የሚያረጋጋ ስሜት የሚሰጥ ነበር - እንደስዋ፡፡

ከጉዋዳ ብቅ እስክትል ጠበቃትና፥ ‹‹ብዙ ታነቢያለሽ!›› አላት፡፡

ደስ የሚል ሽቶዋ አፍንጫውን አወደው፡፡

‹‹ተፈጥሮን ከማድነቅ ሌላ ደስ የሚለኝ ነገር መፅሀፍ ማንበብ ነው፡ ደስታ ይሰጠኛል፡፡ ስለ ማንኛውም ነገር ደግሞ ትምህርት አገኝበታለሁ›› አለችው፥ መፃህፍቶችዋ በፍቅር አይን እየቃኘች፡፡ ‹‹እና፥ ቢሮ ገብቶ በቴሌፎ

እገልዩ፣ እገሊትዬ እያሉ የባጡንና የቆጡን ሲቀባጥሩ ከመዋል መፅሀፍ ማንበብ ይሻላል›› አለች፣ ፍንጭትዋን ብልጭ አድርጋ በአይንዋ ጭምር እየሳቀች፡፡

‹‹እና፡- መፅሀፍ ሕይወት ነው፡፡ በኔ ግምት የመፅሀፍ መጥፎ የለውም፡፡ እያንዳንዱ ደራሲ ለአንባብያን ለማስተላለፍ የሚፈልገው ከህይወት ያገኘው ልምድ አለው›› ብላ ተነሳችና፣ ከሻይ ጠረጴዛ ላይ ያለውን አበባ አስተካከለች፡፡

‹‹እና፡- ማንበብ ብቻ ሳይሆን እኔም አንድ ቀን አንድ መፅሀፍ ለመድረስ ተስፋ አለኝ›› እንዳለች፣ ወጣት ቤት ገረድ ሻይና ትኩስ የዶሮ ወጥ ፍርፍር በትሪ ይዛ መጥታ ከፍኖት ፊት አስቀመጠችውና ወጣች፡፡

ገረዲትዋ የጣት ውሀ ይዛ ተመለሰች፡፡ ደርቤ እጁን እየታጠቡ ‹‹የመፃሀፍት ማንበብ ፍቅር እንዴት አደረብሽ?›› ብሎ ጠየቃት፡፡

ፍኖት ስለ ራስዋ መናገር አትወድም፡፡ ደስ የሚላት ስለ ሌሎች ሰዎች ህይወትና ልምድ ማወቅ ነበር፡፡ ስለ ሌሎች ሰዎች ህይወትና ልማድ ማዳመጥ አይሰለቻትም፡፡ ደርቤ ስለ ራሱ እንዲናገር ለመገፋፋት ስትል ስለ ራስዋ መናገር እንዳለባት አሰበችና፣ ‹‹ታሪኩ ረጅም ነው›› ብላ ጀመረች፡፡

‹‹የመፅሀፍ ማንበብ ፍቅር ያደረብኝ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ነው፡፡ በህፃንነቴ የመፅሀፍ ማንበብ እድል አልነበረኝም፡፡ የሚያበረታታኝም አልነበረም፡፡ ከድሀ ቤተሰብ ነው የወጣሁት፡፡ በድሀ ቤተሰብ ውስጥ መፅሀፍ ማንበብ ቅንጦት ነው፡፡ ዋናው ቁም ነገር የእለት ጉርስ ማባረር ነው. . .

‹‹መፅሀፍ ማንበብ ቀርቶ ትምህርቴንም አቅዋርጬ ቀሎ ስራ እንድይዝ ወላጆቼ ይገፋፉኝ ነበር፡፡ ጥርሴን ነክሼ እንደ ምንም ንግድ ትምህርት ቤት ገባሁ፡፡ እንደ ጉዋደኞቼ ልብስም ጫማም አልነበረኝም፡፡ ያኔ፣ እንደ ጉዋደኞቼ አጊጬ በሞትኩ እያልኩ እመኝ ነበር. . .

‹‹ከጉዋደኞቼ በታች ሆኜ ስታይ ስቃይ ይሰማኝ ነበር፡፡ ስቃዩ ስለ በዛብኝ ትምህርቴን አቁዋርጬ ስራ ለመያዝ ቆረጥኩና እንደ ገና ሳስብበት ለምን? ብዬ ራሴን ጠየኩ፡፡ ስንትዋ የድሀ ልጅ እያጌጠች ትማር የለም! ከየት ነው ገንዘቡን የሚያመጡት? ከእናቶቻቸው የቆሎ ወይስ የጠላ ንግድ ትርፍ ነው?

አብዛኛዎቹ ጉዋደኞቼ ጌጥ የሚቀያይሩበትን ገንዘብ ከየት እንደሚያገኙ ለማወቅ ጊዜ አልፈጀብኝም. . .

‹‹በዚያ ስርአት ውስጥ እኔም ገባሁበት›› ብላ፥ ደርቤ ምግቡን ትቶ ዝም ብሎ የሚያዳምጣት መሆኑን በማየትዋ፥ ‹‹ብላ እንጂ›› አለችው።

ደርቤ ፍርፍሩን እፉን ሞልቶ ጎረሰ። ሻይውንም ተጎነጨ። ‹‹በሞቴ›› ብላ አጎረሰችው። ለራስዋም ጎረሰችና፥ ‹‹ታዲያ ይሄውልህ አንድ ሽማግሌ ነጋዴ አጋጠመኝ። ዘጠኝ ልጆች ነበሩት። ልጆቹ በእድሜ ከኔ ይበልጣሉ። እስቀያሚ ነበር። ግን ደግነቱ አይጣል ነው። ርህሩህ ነው። እንደ አባት ያፅናናኛል። የፈለኩትን ይገዛልኛ። ተወኝ። ስራዬ መሽቀርቀር ብቻ ሆነ።

‹‹ሽማግሌው ያለወጣት ሴቶች ሌላ እንደማይሄድና ከብዙ ኮረዳዎች አንድዋ እንደሆንኩ ያወኩ ከጊዜ በሁዋላ ነበር። አንድ ቀን፥ ለምን የልጅ ልጆችዎ ከሚሆኑ ሴቶች ጋር ይወጣሉ? ብዬ ጠየቅሁት። ‹‹የናንተ ወጣቶች ትኩስ ህይወት ያለመልመኝ እንደሆን በማለት ነዋ! የህይወት እፍታዎች ናችሁ። በናንተ ትንፋሽ መታደስ አለብኝ። ለዚህ ነው›› አለኝ. . .

‹‹ክብረ ንፅህናዬን የሸጥኩት በመታለል ነበር። በህይወቴ እንደዚያን ቀን አልቅሼ አላውቅም። ራሴንም ለመግደል አስቤ ነበር። ድህነት የማያሰራው ነገር የለም ብዬ ዝም አልኩ። እናቴ ታማ ሆስፒታል ተኝታ ነበር። ሶስት መቶ ብር ከፍዬ ከሆስፒታል ሳወጣት፥ ‹‹ገንዘቡን ከየት አመጣሽ?›› ብላ አልጠየቀችኝም። እኔም አልነገርኳትም። ከሆስፒታል ስትወጣ ትኩር ብላ ተመልክታኝ ስታበቃ እንባዋን አፍስሳ ዝም አለችኝ. . .

‹‹ሽማግሌው እንደኔው በገንዘብ ከገዛት ልጃገረድ ጋር ሲታገል ልቡ ቆሞ መሞቱን ሰማሁ። ህይወቴን ያድስልኛል ብሎ ያሰበው ነገር ሲገድለው አዘንኩለት። ግን፥ ለጥልቅ ሀዘን ጊዜ አልነበረኝም። ከአንድ የባንክ ባለስልጣን ጋር ፍቅር ይዞኝ ነበር።

‹‹ቆንጆ ነው። ወጣት ነው። ሚስትና ልጆችም አሉት። ከሱ ጋር ስንወጣ ውስጤ ሁሉ እንደ ፅጌረዳ አበባ እየፈካ ይፈነዳ ነበር። ከሱ ጋር ስሆን ራሴን መቆጣጠር አልችልም ነበር። ከሱ ጋር ተጋብተን ስንኖር እየታየኝ ስለ

ወደፊት ህይወታችን ፕላን አወጣ ነበር። እሱም እንደዚሁ፣ «አንድ ቀን አብረን እንኖራለን» እያለ ተስፋ ይሰጠኝ ነበር. . .

«ከዚዜ በሁዋላ አብረን በወጣን ቁጥር ከወንዶች ጋር ስላለኝ ግንኙነት አጥብቆ ይጠይቀኝ ጀመር። «ክብርናሽን ማን ነው የወሰደው? ማን ነው የመጀመሪያው ፍቅርሽ? እንዴት ነበር የምትሆኑት? ትወጂው ነበር ወይ? ለምንድር ነበር የምትወጂው?» እያለ ይወተውተኝ ጀመር. . .

«ዝም ስለው ያኮርፋል። እንዳያኮርፈኝ ደግም አብሬያቸው ስለ ወጣሁት አንዳንድ ወንዶች ስነግረው ይናደዳል። ሲመታኝም ይቃጣዋል።

«ስንተኛ ደግሞ ከማን ጋር ውጥተሽ ነበር። እያለ አውሬ ይሆንብኛል።

«ከዚያ በሁዋላ ተፀፅቶ ማልቀስ ይጀምርና፣ «ሁለተኛ አይለምደኝም» ብሎ ይቅርታ ይለምነኛል። ግን ሌላ ቀን ስንገናኝ ተመልሶ ያው ነው። ንዝንዙን አልቻልኩም። እርግፍ አድርጌ ተውኩት።

«በዚህን ጊዜ ትምህርቴን ጨርሼ ነበር። ዲፕሎማ ማግኘቴ ለውዬውን አስረሳኝ። ከእንግዲህ ምን አለብኝ! ስራ ይገኘ ራሴንና እናቴን እረዳለሁ ብዬ በማሰብ አዲስ ተስፋ አደረብኝ። ግን፣ ስራ የማግኘቱ ጉዳይ እንዳሰብኩት ቀላል ሆኖ አላገኘሁትም።

ዝዲቱ መጥታ ትሪውን አነሳች።

«ስራ የጠየኩት አለቃ ሁሉ መጀመሪያ የሚያቀርብልኝ፣ «መቼ ይመችሻል?» የሚል ጥያቄ ነበር። አይመችኝም ብዬ መልስ የሰጠሁት አለቃ ሁለተኛ አያየኝም። ከኔ ሁዋላ መጥተው ስራ የሚያገኙ ሴቶች እያየሁ በእድሌ አዝኜ ዝም እላለሁ። ተስፋ የሰጠሁትም አለቃ አብሬው እስከምወጣ ድረስ፣ ጫማዬ እስኪያልቅ «ታዲያስ?» እያለ ያመላልሰኛል. . .

ዝዲቱ መጥታ እጃቸውን አስታጥባ ወጣች።

«ስራ ማግኘት ነበረብኝ። እና «ታዲያስ?» ከሚሉኝ የቢሮ አለቆች ጋር ከመውጣት ሌላ ምርጫ አልነበረኝም። አንዳንዶቹ እልም ያሉ አታላዮች ነበር።

ሳይደብቅ ይነግረኛል። እንዲህ አይነቱ ሀቅ በስንት ባልና ሚስት መካከል ያለ ይመስልሃል? በኢትዮጵያውያን መካከል ያለው ፍቅር ተሸፋፍኖ ኑሮ ነው።

‹‹በፊት በፊት ምናባቱ! እያልኩ እቀና ነበር። አሁን ግን ምንም ቢነግረኝ አልቀናም። የሱም ሆነ የኔ ስሜት ይገባኛል። ዋናው ነገር በመካከላችን ያለው ፍቅር ነው። እስከ ህይወቴ ፍፃሜ ድረስ እጠብቀዋለሁ›› አለችና፥ ፍቅሩ ያሞቃት ይመስል ፊትዋ በፈገግታዋ ብርሃን ተሞላ።

ደርቤ ሊገባው አልቻለም። በአሳቡ ምን አይነት ፍቅር ነው? ብሎ ዝም አለ። በምትወደው ወንድ የማትቀና፥ በሚወዳት ሴት የማይቀና - ቅናት የሌለበት ፍቅር፥ ፍቅር ሳይሆን በሽታ ነው ብሎ አሰበ። በፍኖትና በእምእላፍ መካከል ያለው ፍቅር ትርጉም ፈፅሞ ሊገባው ስላልቻለ፥ ራሱን ነቅንቆ፥ እነሱ ናቸው እብዶች ወይስ እኔ ነኝ ደንቆሮ? ብሎ አሰበ።

ፍኖትም በበኩልዋ ስለ ራስዋና በተለይም ከእምእላፍ ጋር ስላላት ግንኙነት ለማንም ተናግራ ስለማታውቅ፥ ደርቤ ሳይጠይቃት በውስጥዋ አምቃ ያኖረችውን ምስጢር ዝክዝክ አድርጋ በማውጣትዋ ‹‹ምን ነካኝ?›› በማለት ራስዋን ወደ መታዘብ አድልታ ነበር። የደርቤን ምስጢር ለማወቅ ያላት ጉጉት የራስዋን ምስጢር አውጥታ እንድትናገር የገፋፋት መሆኑን በተገነዘበች ጊዜ በሰው ተፈጥሮ ከመገረም አልፋ በመፀፀት አልተቆጨችም ወይም በራስዋ አልተናደደችም። እፍ ያለች ሸርሙጣ ነች ብሎ ይገምተኝ ይሆናል፥ ግን ምን ቸገረኝ፥ ስለኔ የፈለገውን ቢያስብ፥ እኔነቴን እንደሆን የሚለውጥ ነገር የለም ብላ ዝም አለች።

‹‹በጣም ግልጽ ነሽ›› አላት።

‹‹አመሰግናለሁ ማለት ይገባኝ እንደሆን አላውቅም። ግልፅ መሆን ብሄራዊ ጠባያችን አይደለም። በልማዳችን ግልፅነት ከወራዳነትና ከእብደት ጋር የተያያዘ ጠባይ ነው። ለኔ ግን ግልፅ መሆን የአስተሳሰብ ነፃነት ምልክት ነው። ስድ አደግ ወይም እብድ ትለኝ ይሆናል፥ አላውቅም። ላንዱ እንደ ስኳር የሚጣፍጠው ሌላውን እንደ እሬት ሊመረው ይችላል። ግን ህይወቱ ነው›› አለችው።

‹‹ግልፅ ነሽ ስልሽ ለማመስገን ነው›› አላት።

«አንተም እንደኔ ግልፅ ከሆንክ ያንን አምባር ለማን እንደ ገዛህ እስቲ እውነቱን ንገረኝ» አለችው።

ሊዋሻት አልቻለም። ለምን ሊዋሻት እንዳልቻለ አልገባውም። «ብቻ እንዳልኩሽ ለእህቴ አልነበረም። አምባሩን የገዛሁት ለምወዳት ልጅ ነበር» አላት።

«ወደደችው? ምን አለች?» ብላ ጠየቀችው፡

«ምንም አላለችም» አላት፥ ብስጭት ብሎ።

«ለዚህ ነዋ ሰሞኑን የተለወጥከው! ማን ትባላለች—በሞቴ?» አለችው፥ ስሜትዋን ለመቆጣጠር እስከሚያቅታት ድረስ ለወሬ ጉዋጉታ።

«ሂሩት ትባላለች» አላት፥ ስምዋን መጥራት የሚሰጠው ስሜት ልቡን እያቀለጠው።

«እሺ!» አለችና ፍኖት፥ ወሬ ለመስማት ከወንበርዋ ላይ ተመቻችታ ተቀመጠች። ጥሩ መፅሀፍ ያገኘች ይመስል ልብዋ ቆሞ ነበር።

«ስምዋ መጥራት እንኳዋን ደስታ ይሰጠኛል» ካለ በሁዋላ፥ ራቅ ባለ ድምፁ፥ «ግን ሂሩት ለኔ የተከለከለች ፍሬ ናት» አላት።

«የተከለከለች ፍሬ» ብሎ የተናገረው ቃል ደስ ብሎአት በጭንቅላትዋ ውስጥ ቀረፀችውና፥ «ለምን የተከለከለች ፍሬ ሆነችብህ ልጄ?» ብላ ጠየቀችው። በፍጥነት አሳቡን በሙሉ አንብባ ለመጨረስ አሰፍስፋ።

«ቤተሰቦችዋ ያሳደጉኝ ባሽከርነት ነው። ግን፥ ጥሉብኝ ከህፃንነቴ ጀምሬ አመልካት ነበር» ብሎ ጀመረ።

«የቤት አሽከሮች ሁለታችንንም እያያያዙ ሲያሳስሙን ትዝ ይለኛል። ከስዋ በእድሜ ትንሽ የምበልጥ ብሆንም አብረን አፈር ፈጭተን ነው ያደግነው. . .

«ቤተሰቦችዋ ለሽርሽር ይዘዋት ሲወጡ እስኪመለሱ ድረስ በር ላይ ቆሜ ነበር የምጠብቃቸው። ከስዋ መለየት አይሆንልኝም ነበር። ትምህርት

ለዚህ አብዮት መታገል አትጀምርም? ስቃይ፣ ግፍ፣ ፍቅር፣ ርሀራሄ፣ ትህትና ምን እንደሆነ የምታውቅ ይመስለኛል:: እና ጥሩ አስተዋፅኦ ልታደርግ ትችላለህ:: አይመስልህም?›› ብላ በአይኖችዋም ጭምር መሳቅ ጀመረች::

ተገርሞ፣ ‹‹ምን ያደርግልኛል ብለሽ ነው? አላት::

‹‹አሳብክን ወደ ሌላ ነገር ሊመራ ይችል እንደሆን ብዬ ነው::››

‹‹ሂሩትን ሊያስረሳኝ ይችላል ብለሽ ነው? ትቀልጃለሽ መሰለኝ. . .››

‹‹ቀልዴን አይደለም:: ያብዮትና ያገር ፍቅር ከማንኛውም ፍቅር ይበልጥ ጠንካራ ነው:: እና፣ አንድ አብዮተኛ ሊኖረው የሚገባው ጠባይ ያለህ ይመስለኛል:: ጊዜህን በከንቱ አታጥፋ:: የቀይ ኮከብ ጥሪን ተቀበል:: አንድ ቀን ሰው ስትሆን ሂሩት ወዳንተ ትመጣ ይሆናል›› አለችውና፣ በአይንዋ ጭምር እየሳቀች ፍንጭትዋን አሳየችው::

አንብባ ከጨረሰች በሁዋላ እንደ ዘጋችው መፅሀፍ አድርጋ አልቆጠረችውም:: እንዲያውም የሚቀጥለው ታሪክ አካልና ደራሲ እንደሆነች ያህል ነበር የተሰማት:: የመጀመርያዬ መፅሀፍ ብላ አሰበች:: ታሪኩ እየተዘረጋ ሲሄድ በአይነ ህሊናዋ ታያትና ፈገግ አለች:: ስሜትዋን ለመቆጣጠር አልቻለችም:: ተጠመጠመችበትና ሳመችው::

ያን ሌሊት ደርቤ እንቅልፍ አልወሰደውም:: ህይወቱ አንድ ወሳኝ ምእራፍ ላይ የደረሰ መሆኑ ቢሰማውም፣ ምን አቅጣጫ እንደሚይዝ ወይም ወዴት እንደሚያመራ ቁልጭ ብሎ አልታይ ስላለው ነበር እንቅልፍ እምቢ ያለው::

ስለ ሂሩት ባሰበ ቁጥር ስቃዩ ሆዱ ውስጥ እየተገላበጠ፣ የእምአእላፍ ቲአትር መሪ ተዋናይ ራሱን ሲሰቅል በታየው ቁጥር እየተናደደና ሰው እሆናለሁ ብሎ ‹‹የሽፎ›› መሳሪያ በመሆን በፈፀመው ሁሉ ራሱን መልሶ እየታዘበና በአድራጎቱ እያፈረ፣ በሌላ በኩል ደግሞ ከፍኖት ጋር ያሳለፈውን ጊዜ በማስታወስ ‹‹ምን አይነት ውብ ፍጡር ናት! ለካ በሰዎች መሃከል እንዲህ አይነት ፍቅርም አለ!›› በማለት እየተደሰተና ቃላትዋን ሁሉ በማስታወስ እያመነዠካቸው፣ ‹‹ለምን ለዚህ አብዮት መታገል አትጀምርም?. .

. ያብዮትና ያገር ፍቅር ከሁሉም ያብልጥ ጠንካራ ነው። ያለቸው ጭንቅላ
ውስጥ እንደ መረዋ እየደወለ፣ ቀይ ኮከብ እየታየው፣ ሰማዩ በቀይ ኮከብ አጊጦ
እየታየው፣ እንዲሁ ሲገላበጥ ነበር ያነጋው።

ጎህ ቀዶ ወፎች ዝማሬአቸውን ሲጀምሩ፣ እውነት ለምን አብዮቱን
አላገለግልም? እንዳለ፣ አባቱ ወንበዴ ተብሎ ከተሰቀለበት ገመድ ተንጠልጥሎ
ሳይሆን፣ በፍኖተ ዕጊረዳ አበባ ተክሎች መሃል ቆሞ ሲስቅ ታየው። ከየት
ይሆን የምጀምረው? ብሎ እንደ ጉልቻ የጋለውን ጭንቅላቱን ይዞ ሲያስ
ቆየ። የሰፈሩ ቀበሌ ታየው።

ጭልጥ ያለ እንቅልፍ ይዞት ሄደ።

‹‹እንደ ፍየል ጭራ ገበና ከማይደብቁ አለቆችም ጋር መስራት አልችልም፤ በጥፋታቸው የቀጣሁአቸው ሰራተኞች በየውይይት ክበቡ አድሃሪ ቢሮክራት እያሉ ሲጨፍሩብኝ ዞር ብሎ ከእነርሱ ጋር ከሚያቆከቁክ አለቃ ጋር መስራት አልፈልግም። በሬ ካራጁ ጋር ይውላል ይባላል። ከፍየል ጭራ ጋር. . . ጭራውን ከሚቆላ አለቃ ጋር ለመስራት አልፈልግም። ገባሽ ቲጊ?. . .››

‹‹ገብቶኛል፥ እኔስ መቼ አጣሁት አለቃህን። ያህያ ውሀ ጠጪ ነው። በጥርሱ ቢስቅም ልቡ የሚገኝ ሰው አይደለም. . .››

‹‹ልብ ስለሌለው ነው።››

‹‹እኔ አሁንም ጠዋት ተነስተህ ሥራ ግባ ነው የምለው። ለምቀኞች በገዛ እጅህ ዱላ ማቀበል ደግ አይደለም። ያጠፉሃል ብዬ ነው የምሰጋው. . .››

‹‹ምቀኝነትንና የግል ፍላጎትን ከመደብ ትግል ጋር እያስታከኩ ለማወናበድ የሚሞክሩ በዝተዋል። እኔ. . .እኔ ግን አልፈራም፥ አላጎነብስም. . . ለማንም. . . ደግሞ አድሃሪ አይደለሁም። ስርአትና ዲስፕሊን ይከበር ማለት አድሃሪ አያሰኝም። እኔ አድሃሪ ነኝ እንዴ ቲጊ? አድሃሪ እመስላለሁ?››

‹‹ለምን እልህ ትገባለህ?›› አለችው።

ቂመኛ መሆኑን ታውቃለች። ስልጣኑን በመጋፋት ክብሩን ከነኩበት እጅግ አድርጎ የሚቆረቆርለትን ክብሩን ከነኩበት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ. . .ጊዜና ሁኔታን ጠብቆ ባለው ስልጣን በመጠቀም ሳይኮረኩም ወይም አፈር ድሜ ሳያገባ አይመለስም ነበር። በክብሩ በመጣ ጉዳይ እንኳን የለየላቸው ጠላቶቹን ቀርቶ ጉዋደኞችንና ወዳጆቹንም አይምርም ነበር። ስለሆነም፥ ከመወደድ ይልቅ፥ መከበርንና መፈራትን ስለሚመርጥ፥ ከጠላቶቹ ይበልጥ ወዳጆቹን የመጉዳት ዝንባሌ ነበረው፤ ቁንጥጫው የደረሳቸው ወዳጆቹ ሁሉ፤ ‹‹ከጌታቸው የተጠጋ ወዳጅ፥ ከአጋም እንደተጠጋ ቁልቋል ሲያለቅስ ይኖራል›› ይሉት ነበር።

ውስኪውን አንስቶ ባንድ ትንፋሽ ጭልጥ አድርጎ ያስ ልማዱ። ውስኪ ሲጠጣ በርጋታ ቀስ ብሎ እያንዳንድዋን ብርጭቆ እየተንከባከበ ነበ

የሚጠጣው፣ ‹‹እኔ በእነማእ ኮሙኒዝም አላምንም - በውይይት ክበቦች ባራክ ኮሙኒዝም›› እለ፣ የጨለጠው ውስኪ እየተናነቀው።

‹‹ጌቱ አንተ ምናገባህ? ብትተወው ምናለበት? ዝም ብለህ ስራህን በትስራ. . .››

‹‹ሰምኑን ደግሞ አብዮት ያሳበደው ማንን መሰለሽ? ያ እኔ ስራ የስገባሁት. . . የእህቴ አሽከር የነበረው. . . ደርቤ። አብዶአል። ምናለኝ መሰለሽ? ልመክረው ፈልጌ ባስጠራው፣ ‹‹የቢሮክራቶች ዘመን እያከተመ ነው. . ይልቅ፣ ጋሼ. . . ከውይይት ክበቦች ጋር ቢተባበሩ ይሻላል›› ብሎኝ ወጣ።

‹‹እውነቱን ነው።››

‹‹እንቺንም ቀበሌ አነቃሽ መሰለኝ? ልክ አገባዋለሁ. . . ሁሉንም ልክ ገባቸዋለሁ. . . ስራና ዲስፕሊን መቅደም አለበት። አብዮት አትከባበሩ ይልም። እኔ የማዝነው ሀላፊዎች አድርገው አስቀምጠውን፣ ማንም ያዋርደን፣ አብዮት ነው እያሉ ዝም ብለው በሚመለከቱን ባለስልጣኖች ነው። ንደ ፍየል ጭራ ገበና የማይሸፍኑ የምላቸው ለዚህ ነው. . .ይገባሻል?››

‹‹እልህ ነው እኮ የሚያጠፋህ።››

‹‹ሲነኩኝ አልወድም። ታውቂ የለም። አትንኩኝ ነው የምለው። ይደለም?›› አላት እየተጨነቀ፣ የጠጣው ውስኪ እየተናነቀው። ያንን ደፋር ቡን እንደ ልማዱ በግራ እጁ መታ መታ እያደረገ፦ ቲጊ፣ እኔ እኮ ሚያመኝ ውስኪ አይደለም። ይህ እውር ደንቆሮ አለም ነው ሚያቅለሸልሸኝ፤ እውር ደንቆሮ አለም። ታውቂኝ የለም ቲጊ? ሲነኩኝ ንደማልወድ?››

‹‹አውቃለሁ።››

‹‹እኔ ምንድን ነኝ-ድንች ወይስ ድንጋይ?

‹‹አንተ ምን ቸገረህ?››

‹‹እኔ ከማን እንሳለሁ? እኔ!›› ብሎ ልቡን መታ መታ አደረገና፣ ‹‹በሀይለ ሴ ጊዜ፣ ኮሙኒስት ነው እየተባልኩ የማንም ደንቆሮ ሽርሙጣ መጫወቻ

‹‹እንዘነት አድርገን! ለገንዘብ የማይጉዋጉዋ ማን አለ? ዋ እቴ! ክርስቶስም የተሸጠው ለገንዘብ ነው፡፡ ባለፈው ሰሞን መጥቶ እንደምንም አጠራቅሜ መኪና መግዛት አለብኝ ሲል ነበር፡፡ መቼም ልቡ ካቀመ በላይ ይንጠራራል፡፡››

‹‹በጣም እንጂ፥ ራሱን ከፍ ለማድረግ ያለው ጉጉት አይጣል ነው. . .››

‹‹ለመኪና መግዣ ብለን. . . ካንገራገረ ማለቴ ነው. . . ትንሽ ካጎረሰነው አፉን ይዘጋል፡፡ ደሞም አትርሺ፥ በማስታወቂያ ሚኒስቴር ውስጥ ሰርቶ የመኖር እድሉም በኛው እጅ ነው፡፡››

አቶ ጉልላት ራሳቸውን በአሉታ ነቀነቁ፡፡ ‹‹አዪ፥ ያንን ወንድምሽን እንደሆን የምታስቢው ከአይንሽ ጉድፍ እፍ ብሎ አያወጣልሽም!››

‹‹አይ፥ ለዚህ እንኩዋን እምቢ አይለኝም፡፡ ጥቃት ስለማይወድ ላመነበት ወደ ሁዋላ አይልም፡፡ ወሰኔን መስለህ እንዴ? ያንበሳ ልብ ነው ኮ ያለው፡፡ ሆኖም እሱም እምቢ ቢል የአለቃ ተክሌ ልጅ. . . ያ እንክስ እንክስ የሚለው . . አዎን መሀሪ፥ እሱ አለልኝ አንጀት የሚያደርስ፡፡››

‹‹መሀሪ ለኛ ሲል ነው እንጂ በዚያን ሰሞን መጥቶ ስለ ደብ ብጠይቀው፥ በፊት ጥሩ ልጅ ነበር. . . አሁን ግን በውይይት ክበብ ውስጥ ቀንደኛ ቀስቃሽ እየሆነ አስቸግሮአል ብሎኝ ነበር፡፡››

‹‹አሳልኩሽም? ይህ አብዮት የሚሉት ጣጣ ያልለወጠውና ያላሳበደው ማን አለ?››

ኩዋ! ኩዋ! ኩዋ! . . . የሽጉጥ ተኩስ፡፡

ድዋ! ድዋ! ድዋ! . . . የዲሞትፎር ተኩስ፡፡

አቶ ጉልላት ከተቀመጡበት ደንግጠው ተነስተው፥ ‹‹የመላኩ ያለ ያደሩበት አንሶአቸው ደሞ ሲውሉበት ነው እንዴ?›› አሉ፥ በር በ እየተመለከቱ፡፡

ወይዘሮ አምሳለ ወደ መስኮቱ እየሮጡ፥ ‹‹ደርቤ! ስሙን ቁስ ይጥለው እቴ! ማን ነሽ አንቺ!›› ብለው ተጣሩ፡፡

ተኩሱ የተከፈተው ከቤታቸው አጠገብ ስለ ነበረ ሰው ሁሉ ሲሩዋሩዋጥ ይስማቸዋል፡፡ ሁለት ሴቶች እየተቀባበሉ ጩኸታቸውን ያቀልጣሉ፡፡ የቤቱ አጥር ግንብ፥ መዝጊያው የብረት በመሆኑ ከአውራው መንገድ ላይ ይካሄድ የነበረውን ትርኢት ከቤት ውስጥ ሆኖ በመስኮት ለማየት አይቻልም ነበር፡፡

‹‹ብርሃኔ! ብርሃኔ!›› እያሉ ቢጮሁ፥ ገረድ የሚሉዋት ከቦታውም ስላልነበረች ‹‹ኧረ ልጆቼ የት ይሆኑ? ከትናንት ጀምሮ አላየሁዋቸውም፡፡ ወይኔ ልጆቼን! ልጆቼን!›› እያሉ ደረታቸውን ጥለው በር ከፍተው ወጡ - ወይዘሮ አምሳለ፡፡ አቶ ጉልላትም ተደናግጠው ተከትለዋቸው ወጡ፡፡

ህዝብ መንገዱን ሞልቶ እንደ ጉንዳን ይተራመሳል፥ ‹‹አዬ ጉድ! ጉድ እኮ ነው!›› እያለ ከንፈሩን እየመጠጠ - ሁሉም፡፡

አንዱ ድምፁን ከፍ አድርጎ ፥ ‹‹በዚያ በኩል ነው የሮጡት ቁልቁለቱን - በመንደር ውስጥ›› አለ፥ የሄዱበትን አቅጣጫ በጣቱ እያመለከተ፡፡ ባመለከተው አቅጣጫ የዲሞትፎርና የሽጉጥ ተኩስ ከሩቅ ይሰማል፡፡

‹‹ልጄን! ልጄን! ልጄን! ለኔ ባደረገው! ለኔ ባደረገው!›› እያሉ ጠጉራቸውን ይነጫሉ - እናት!

‹‹ወንድሜን! ወንድሜን! ወንድሜን! እኔ ልደፋልህ! እኔ ልደፋልህ! እኔ ልደፋልህ!›› እያለች ደረትዋን ትደቃለች - እህት!

‹‹ሸበላዬ! ሸበላዬ! ለማን አደራ አልከን? ለማን አደራ አልከን?›› እያለች ፊትዋን ትነጫለች፥ አንዲት ህፃን ልጅ ያዘለች ወጣት ሴት - ሚስት!

‹‹አምቡላንስ ጥሩ! ትንፋሹ አለች፡፡ አምቡላንስ ጥሩ!›› እያለ አንድ ረጅም ቀይ ሰው እንደ ዮሀንስ መጥምቁ በምድረ በዳ ይጮሀል - የሚሰማው አጥቶ፡ አንዱ በሌላው ላይ እየተንጠራራ ወሬ ለማየት ወደ ፊት ይጋፋል፡፡

ወይዘሮ አምሳለ፥ አጭር ቁመናቸው ምንም ለማየት ስላላስቻላቸውና ከተራው ህዝብም መካከል ገብተው መጋፋት ስላስፀየፋቸው፥ ከዳር ቆመው፥ ‹‹ምንድን ነው እሱ? ማን ነው የተመታው?›› እያሉ ለወሬ ቸኩለው ከአጠገባቸው ያሉትን ሰዎች ይጠይቃሉ፡፡

ደርቤ በሽማግሌው አንጋገር ልቡ ስለተነካና ሀቀኛም መስለው ስለታዩት ለመሳሪያቸው ደረሰኝ ሰጥቶ ሊሸኛቸው ቆርጦ ትእዛዝ ለመስጠት ሲል «ጣሊያንን ያርበደበድነው በተደበቀ መሳሪያ ነው›› የሚል ቃል ከጆሮዎቹ ውስጥ እንደ መረዋ ደውሎ ጥርጣሬ ስለቀሰቀሰበት፣ ‹‹አባቴ፣ መሬት ወይም ትርፍ ቤት ተወርሰዋል? ብሎ ጠየቃቸው፣ ሳያስበው ፈገግታውን አጨልሞ ድምፁን ከፍ አድርጎ።

‹‹የሞተላት ቀርቶ የገደላት በላ ሲሉ አልሰማህም ልጄ? መሬትም ቤትም የለኝም። ያለኝ ትዝታ ብቻ ነው›› አሉት።

‹‹የታሰረ ወይም አብዮታዊ እርምጃ የተወሰደበት ዘመድስ?››

‹‹ዘመድ?››

‹‹አዎን ዘመድ. . .ልጅ?››

‹‹ያጣ የነጣ ሰው በዚህ አለም ምን ዘመድ አለው ብለህ ነው። ልጅ የለኝም፤ መሆን ነኝ። ዘመዶቼም ልጆቼም እነዚህ መሳሪያዎቼ ነበሩ። ግን ጠላቶች አሉኝ›› አሉት፣ ፍርጥም ብለው።

‹‹ማን ናቸው እነርሱ?›› ብሎ በመገረም ጠየቃቸው።

‹‹ጠላቶቼ? ሆዴና ትዝታዬ ናቸው!››

‹‹ብሉ አባቴ፣ ትንሽ ቢታገሱኝ ከጓዶች ጋር ተመካክሬ መ እሰጥዎታለሁ›› ከማለቱ፣ ሲታገለውና ሲያስጨንቀው በቆየው ሃሳብ ህሊናው ቆራጥ አቋም ሲወስድ ተሰማው።

ሽማግሌውን አንዱ የአብዮት ጥበቃ ጉዋድ ይዞአቸው ሲወጣ ፈጠን እያለ ሲናገረው ሌላው አባል ወደ ሁዋላ ቀርቶ ‹‹ምን ሆነሃል?›› ደርቤን ጠየቀው።

‹‹ምን ሆኛለሁ?››

‹‹እኔ እንጃ! ግር ይልሃል - ከማታ ጀምሮ። አንድ ነገር የሚያስጨንቅህ ትመስላለህ። ሁላችንም የምንጠያየቀው ምን ሆኖአል? ምን ነካው? ነው።››

የቀይ ኮከብ ጥሪ

ስሜቱ አብረውት አልቆዩም። የወይዘሮ አምሳለን ጥሪ ሂሩትን እንዳስታወሰ ፊቱ ላይ እየፈካ ይሄድ የነበረው ፈገግታው ተመልሶ መጨለም ሲጀምር፥ ፍኖት በሩን አንኳኩታ ገባች። ደርቤ ፍኖትን በማየቱ ተደስቶ ከመቀመጫው ዘሎ በመነሳት ሮጦ ሂዶ ሲጨብጣት እጁን ዘረጋ። ጠጋ ብላ ጉንጩን ሳመችው። ‹‹ጓታክልቴ ውስጥ የቀጠፍኩት ናት ብላ እምቡጥ ያልፈነዳ ፅጌ ረዳ አበባ ሰጠችውና፥ ‹‹የቀይ ኮከብ ጥሪ ስለ ደረሰህ እንኳዋን ደስ አለህ። መመረጥክን ቤት ደውለው ነው የነገሩኝ›› አለችው።

ሳቂታ ፊትዋ ጨልሞአል። ብሩህ ፈገግታዋ ጠፍቶአል።

‹‹የመመረጤ ወሬ ከመቼው ተነዛ?›› አላት። ምን እንደ ሆነች ባይገባውም የተለወጠች መሆንዋ ሳይሰማው አልቀረም።

‹‹አዲስ አበባ ካቅምዋ በላይ የሰፋች መንደር ናት። የተደረገ ነገር ቀርቶ የተተነፈሰም ነገር ሰው ጆሮ ሳይገባ ውሎ አያድርም›› አለችው።

ድምፅዋም እንደ ፊትዋ ህይወት አልነበረውም። ከጥቂት ጊዜ በሁዋላ ነበር ከላይ እስከ ታች ጥቁር መልበስዋ የታየውና፥ ‹‹ምንነው ጥቁር ለበሽ?›› ብሎ የጠየቃት።

ለጥቂት ሴኮንድ ያህል አመነታችና፥ ‹‹እምአእላፍ ሞቶ ነው›› አለችው? የራስዋ በሆነ የቀዘቀዘ ድምፅ።

ደርቤ ደንግጦ ራሱን ያዘ። የሚያደርገው ነገር ጠፍቶት ህይወት አልባ ሆኖ ደንዝዞ ቆሞ ቀርቶ ነበር።

‹‹ምንም አይደል። የፈለገው ነገር ነው። ስሜቱ ይገባኛል›› አለችው።

ፍኖት ባትናገር ኖሮ እንደ ደነዘዘ ይቀር ነበር። ‹‹ምን ሆኖ ነው የሞተው?›› አላት፥ እምአእላፍን መሞት ማመን እያቃተው።

‹‹ራሱን ነው የገደለው››

‹‹እንዴት?››

‹‹ተሰቅሎ።››

‹‹ፈፅሞ አላምንም። እምአእላፍ ሞቶአል ብዬ አላምንም...››

‹‹እኔም እንደሱ ነው የሚሰማኝ። የምንወደው ሰው ሲሞት ሙቶአል ብሎ ለማመን ያስቸግራል። እኔ አለ ነው የምለው። ምክንያቱም ካላቤ አይጠፋም። ግን ትዝታው ብቻ ነው የቀረው›› አለችውና፣ መሀረም አውጥታ አይኖችዋን ጠረገች።

‹‹ግን ለምን? ለምን?›› አላት በደረቀ ጉሮሮ፣ እንደ ህፃን ፈገግታ ብልጭ ሲል ደስ ይል የነበረውን የእምአእላፍን ፈገግታ፣ ለዛና ቁም ነገር የተመላበት ቀልዱን፣ ለህይወትና ለሰው ልጅ የነበረውን የጋለ ፍቅር እያስታወሰ።

‹‹ያንን ቲአትር ካሳየ ወዲህ ደስ ብሎት አያውቅም። ውስጥ ውስጡን የሚበላው ነገር ነበር›› አለችና፣ አይኖችዋንና አፍንጫዋን በመሀረም አደረቀች።

‹‹ከፍቶት አላየሁትም። ሁልጊዜ ሲስቅና ሲቀልድ ነው የማየው። ጫቱን በልቶ ‹‹ምርቅን›› ሲሰማው የሚያየው አስቂኝ የሆነውን የሰው ልጅ ጎን ነበር›› አላት።

‹‹አዎን፣ ግን እምአእላፍ ደስታውን ነው እንጂ ከሰው ጋር የሚካፈለው፣ ሀዘኑንና ብስጭቱን ከራሱ አሳልፎ ለማንም አይገልፅም ነበር።

‹‹ቢገልጽም የሚያስቅ መንገድ ፈልጎ ነበር። እያንዳንዳችን ሀዘናችን በጉያችን፣ ደስታችንን በጋራ፣ በዚች አሳዛኝ አለም ላይ ሀዘን መጨመር ምን ያደርጋል፣ ሁሉም በልቡ በቂ ሀዘን የተሸከመ ስለሆነ፣ አንዱ ከሌላው የሚፈልገው ደስታን ብቻ ነው፤ መሆንም አለበት። ይህችን አጭር ህይወት በደስታ ማሳለፍ ከፈለግን ይህችን ማርና እሬት የሆነች ህይወት›› ይል ነበር፣ ‹‹እና፣ የሚፅፈው ለሰው ልጅ ደስታን ለመፍጠር ነበር›› ብላ፣ ‹‹ነበር እንዲህ ቅርብ ኖሮአል እሱ እቴጌ ጣይቱ›› አለችና፣ ተክዛ አንገትዋን ደፋች።

የደርቤ እንባ ኮለል ብሎ ወረደ። አይኔን የከፈተልኝን ወንድም አጣሁ ብሎ በማሰብ ሀዘኑ አጥንቱ ድረስ ዘልቆ ተሰማው። እንባውን በዝምታ እያወረደ፣ የእምአእላፍን ብሩህ ያለ ገፅታ በእንባው ውስጥ አሻግሮ እያየ፣ ለምን ራሱን ይገድላል? ዝና ፈልጎ ነው? ወይስ መፃፍ አቅቶት? እያለ ሲያስብ ከቆየ

በሁዋላ፣ እምአእላፍ አንድ ቀን፣ ‹‹መፃፍ ያቃተው ደራሲና ጥይት የሌለው መሳሪያ አንድ ናቸው›› ያው ትገዘ አለውና፣ ‹‹እንደሱ ያለ ሰው ለምንድን ነው ራሱን የሚገድለው? ለሰው ልጅ ፍፁም ፍቅር ያው ሰው እንዴት ራሱን ይጠላል? ተፈጥሮን የሚወድ. . . እ. . . እንዴት ሕይወትን ይከዳል?›› አላት፣ ብስጭት ብሎ። ከቦርሳዋ አንድ ደብዳቤ አውጥታ ሰጠችው። ደርቤ አይኖቹን ጠራርጎ ደብዳቤውን ከፈተ። ደብዳቤው፣ ‹‹ፍኖትዬ - የኔ ፍቅር›› ብሎ ነበር የሚጀምረው።

‹‹መቼም ይቅርታ አታደርጊልኝም። ይቅርታ ታደርጊልናለሽ ብዬ አልጠብቅም። አድራጎቴ ከይቅርታ በላይ ነው። ህይወትን ያህል ውብ ነገር በገዛ ፈቃዱ ደህና ሁኚ ብሎ ለዘለአለም የሚሰናበት ሰው ይቅርታ ሊጠይቅም፣ ይቅርታ ሊደረግለትም አይችልም።

‹‹ግን ሲኦል የተሻለ ቦታ ሳይሆን ይቀራል ብለሽ ነው! እስከማየው ድረስ ቸኩያለሁ። መቼም ፈልጌ መንግስት ለማያት አልሄድም። ከጥቂት ጊዜ በሁዋላ የሚሰለቸኝ ይመስለኛል. . .

ደርቤ ከደብዳቤው ላይ ቀና ብሎ ፈገግ አለ። በራሱ ላይ ሞት ፈርዶ መልሶ በራሱ የሚስቅ ሰው ይገርማል ብሎ አሰበና፣ ደብዳቤውን ማንበብ ቀጠለ።

‹‹ለማንኛውም ነገር ዘለአለማዊ ደስታ የሚሉት ነገር ያ አይመስለኝም። የፈጠራ ህልም ነው።

‹‹ቸኩያለሁ። የምንጠለጠልበት ገመድ ተዘጋጅቶ ይጠብቀናል። ሽምቀቆው አፉን ከፍቶ ይታየኛል።

‹‹ፍኖትዬ፣ ለመኖር አልቻልኩም። ያለ ድርሰት ሌላ ህይወት የለኝም። ምኞቴ በድርሰት ለሰው ልጅ ደስታን ለማስገኘት ነበር። ግን ለሰው ልጅ ደስታ ለመስጠት አልቻልኩም። ራሴን አታልዬ፣ ሌሎችንም ማታለል ምን ፋይዳ አለው! በኔ ግምት በድርሰት ምንደኛ ወይም አድርባይ መሆን የሚቻል አይመስለኝም። ለስሜቱ ሀቀኛ ያልሆነ ደራሲ ለራሱም ሆነ ለሌላው ደስታ ሊሰጥ አይችልም።

‹‹ኢትዮጵያን በሚገባ የሚያውቅ ኢትዮጵያዊ፣ ኢትዮጵያ የሚወድ ኢትዮጵያን አብዮተኛ መሆን አለበት! ምክንያቱም ኢትዮጵያ አብዮት ያስፈልጋታል፣ ተሀድሶ ያስፈልጋታል፣ ያለኝ ትዝ ይለኛል አለች።

‹‹አብዮትም እንደ ድርሰት ንፁህ ስሜታችንንና ሙሉ ጊዜያችንን፣ የመፍጠር ችሎታችንን ይጠይቃል›› አላት፣ ስሜት እየተናነቀው።

ፍኖት ትኩር ብላ እያየችው፣ ድንገት ፍንጭትዋን ብልጭ አድርጋ ምላስዋ በማሾል ጥርስዋን ላሰች። ከንፈሮችዋ ረጠቡ። በውስጥዋ መፈንደቅ የጀመረውን ስሜት በግድ ገታችና፣ ‹‹አብዮተኞችን ከዚህ አንፃር ለማየት ሞክሬ አላውቅም። ግሩም ነው›› አለችው።

‹‹መቼም መፅሀፍሽ ውስጥ እኔ አለሁበት አይደለም?››

‹‹ማን አለህ?››

‹‹እንዲሁ ይገባኛል። ሁሉጊዜ የምትጠይቂኝ ጥያቄዎች ይነግሩኛል። ጠያቂ፣ ጆሮና አይን ብቻ ሆነሻል።››

አባባሉ አስገርሞአት ፈገግ አለች። ፈገግታዋ ተጋባበት። ደስ አለው። የሚሰማኝን ሁሉ ዝክዝክ አድርጌ ልነግራት ብችል ምን ነበረበት ብሎ ተመኘ። መፅሀፍዋ ትዝ አለውና ድንገተኛ ቅናት አደረበት። ምን ነው ባለቀላትና በተገላገለችው አለ። ለምን ያስቃያታል! የሚል አሳብ መጣበትና፣ እናቱን! አለ በልቡ።

‹‹ለምን እንዲህ ታየኛለህ?››

ጥያቄዋ አስፈራውና አይኑን ሰበረ።

‹‹ለምን ያስቃያታል እያልኩ በልቤ ስራገም ነበር።››

‹‹ማን?››

‹‹መፅሀፍሽ››

‹‹ለምን?››

‹‹ብቻ አለ አይደል። ቅናት አሳደረብኝ።››

‹‹ለምን?››

‹‹መካከላችን የገባ ሰው መስሎ ስለታየኝ። እና ስለሚያስቃይሽ።››

ውስጥዋ ይፈነድቅ የነበረው ስሜት ገንፍሎ ስለ ወጣ ዘላ ግንባሩን ሳመችው። ጉንጭዋን ሳማት። ላንዳፍታ አይኖቻቸው በቅርብ ተጋጩ። የእሳት ብልጭታ ተፈጠረ። እሱ ቀይ ኮከብ ታየው። እስዋ አዲስ ምእራፍ ታያት።

እየፈነደቀች፥ በጥርስዋም በአይንዋም ሳቀችና፥ ‹‹እምአእላፍ ሞተ። አዲስ ምእራፍ ተወለደ። እምቢ ብሎኝ የነበረውን አሳብ ፈታህልኝ›› አለችውና፥ ‹‹ቆይ እንጂ። እንደ ገና ግንባሩን ስማ እየሮጠች ስትወጣ ተከትሎ ደረሰባትና፥ ‹‹ቆይ እንጂ። ምን ነካሽ ቀብሩ መቼ ነው?›› አላት።

‹‹ውይ በሞትኩት! የመጣሁበትን ጉዳይ ረስቼው! አሁን ነው›› አለች፥ ባላየችው ሁኔታ እንደማፈር ብላ።

‹‹አብሬሽ እመጣለሁ። ግን ሞቶአል ብዬ አላምንም።››

‹‹ደራሲ ይሞታል፥ ድርሰቱ ግን አይሞትም›› ብላ፤

‹‹ሌላም የምጠይቅህ ነገር ነበረኝ›› አለች።

‹‹ምን?››

‹‹ስለ ሂሩት።››

‹‹ጀመርሽ እንግዲህ!››

‹‹ምን?››

‹‹ያን መከረኛ ጥያቄሽን።››

ከት ብላ ሳቀች።

‹‹ሌላ ጊዜ ስለ እስዋ አጫውትሻለሁ። ለስዋ ያለኝ ፍቅርና ለቀይ ኮከብ ያለኝ ፍቅር እየተወሳሰበብኝ፥ እየተገመደብኝ ሄዶአል›› አላትና ‹‹እንጂ ቆይኝ›› ብሎአት ወደ ቢሮው ገባ።

የቀይ ኮከብ ጥሪ

ኮቱን ይዞ ሽጉጡን ጎኑ እየሻጠ ተመልሶ መጣና፣ ‹‹እምአእላፍን መሸኘት አለብኝ›› አላት።

‹‹ይኖራል። ከመቃብር በላይ ይኖራል። ለዘለአለም!›› ብላው ፊታቸውን ወደ መንገዱ መለሱ። እርስዋን ‹‹ማርና ሬት›› እየጠራት፣ እርሱን ቀይ ኮከብ እየጠራው. .

## ምእራፍ ፲

ከማስታወቂያና መርሀ ብሄር ሚኒስቴር ሊጋለጡና ሊመቱ ይገባቸዋል በማለት የመስሪያ ቤቱን የአብዛኛዎቹን የመምሪያ ሀላፊዎች፥ የአንዳንዶቹን የጋዜጣና የራዲዮ ፕሮግራም ዋና አዘጋጆች እንዲሁም የአንዳንድ የጠቅላላ አገልግሎት ሀላፊዎችንና የፔርሶኔል ሹሞችን ስም ዝርዝር ይዘው የመጡት አራት ጋዜጠኞች ከደርቤ ቢሮ ወጥተው በቀጥታ ወደ ስራቸው አልተመለሱም። ተያይዘው በቀጥታ ያመሩት ወደ ሌላ ቀበሌ ነበር።

እግረ መንገዳቸውን ላንዳፍታ ቆም ያሉበት ጊዜ ቢኖር፥ አዲስ ዘመን ጋዜጣ ለመግዛት ብቻ ነበር።

ጋዜጣውን ብዙ ህዝብ ይሻማ ስለነበረ በስንት ልመናና ግፊያ ለዚያው በሃያ አምስት ሳንቲም ከአንድ ጋዜጣ በላይ ለመግዛት አልቻሉም። የፈለጉት ዜና በመጀመሪያው ገፅ በሶስት አምድ፥ በ፵፮ ኮር ፊደል፥ ‹‹የተጋለጡ አናርኪቶች በተራማጅ ሀይሎች ቁጥጥር ስር ዋሉ›› በሚል አርእስት ስር ተፅፎ በማየታቸው ተደስተው ፈገግታ በመለዋወጥ መንገዳቸውን ቀጠሉ።

በአርእስቱ ስር የሰፈረው ፅሁፍ ይዘት፥ በተራማጅ ሀይሎች ቁጥጥር ስር የዋሉት ዘጠኝ አናርኪስቶች፥ ሶስት ሴቶችና ስድስት ወንዶች፥ ትናንት ጠዋት ከረፋዱ ላይ በቁጥጥር ስር ለማዋል የበቁት፥ የመስሪያ ቤታቸው ሰፊ ሰራተኛ ከሀቀኛ ታጋዮች ጋር በመተባበር ስላጋለጣቸው ነው የሚል ነበር. . .

ዘጠኙም ሰዎች በዋስይሁንና ግበረ አበሮቹ እጅ መራራ ፅዋቸውን ቀምሰው እንደ ውሻ ጥምብ ከወንዝ ውስጥ ማታውኑ ተጥለዋል። ‹‹ዋስይሁን ትንሽ ጊዜ ቢያገኝ ኖሮ እኛንም ከስንት የኢ.ዲ.ሀ. አባሎች፥ አናርኮ ፋሺስቶችና ተገንጣይ ቡድኖች ቅፅበታዊ በሆነ ፍጥነቱና ቆራጥነቱ በገላገለን ነበር›› በማለት አራቱም ጋዜጠኞች በመያዙ እየተቆጩና በደርቤ አቅዋምም እየተገረሙ ከቀበሌው ፅህፈት ቤት ደረሱ።

ከአዲስ አበባ ቀበሌዎች ሁሉ በቅድሚያ የታጠቀና አብዮቱ ከተከላካይነት ወደ አጥቂነት በተሸጋገረበት ወቅት የመጀመርያውን ጥይት በመተኮስ የህዝባዊ የቀይ ሽብርን ክስተት ያበሰረ፥ ስሙ ከሩቅ የሚያስፈራ ዝነኛ ቀበሌ

ሌለ ርምጃ መውሰድ ያስፈልጋል። አዝማሚያው አደገኛ ነው›› አለ፥ ፍርጥም ብሎ።

ኮፍያውን አይኑ ድረስ ደፍቶ ሲጃራ እያከታተለ የሚያጨሰው የአብዮት ጥበቃ ሊቀ መንበር ለመጀመርያ ጊዜ እንደ ምንም አፉን አላቆ እያንዳንዱዋን ቃል እየቆጠረ፥ ‹‹እዎን. . .እዚያ. . .እንትን. . . እንትን. . . ቀበሌ ውስጥ የኛም እንትን ጉዋዶች አሉ። እንትን. . . ዘዴ ፈልገን. . . እንትን. . . እንትን. . . እንትን. . . እንዲጋለጥ. . . እንትን. . . እንትን. . . ለማድረግ ይቻላል›› አለ። ነገሩን እንትን. . . እያለ በመጎተት ትእግስታቸውን አስጨረሰ። በጣም አይነ አፋር ስለነበረና ለመናገርም ሲፈልግ ቃላት ስለማይያዙለት በርከት ያሉ ሰዎች ባሉበት መናገር አይወድም። በህፃንነቱ የወደቀ ቦምብ አግኝቶ ሲቀጠቅጥ ፈንድቶበት ነው ይባላል፥ ግራ እጁ ቆራጣ ነበር። በአንድ እጁ የተኮሳት ጥይት መሬት ጠብ ስለማትልና ርህራሄ የሚሉትን ነገር እስከነቃሉም ስለማያውቅ ከሩቅ የማይፈራው ሰው አልነበረም። መናገር ከመጥላቱ የተነሳ ብዙ ሰዎች ካሉበት ቦታ መገኘት ደስ አይለውም ነበር። በሰዎች መካከል ሲሆን ሰውነቱ ሁሉ ይወጣጠርና የሚያደርገው ነገር መላቅጡ ይጠፋዋል።

የቀበሌው ሊቀ መንበር ፊቱ የነበረውን ወረቀት በአይኑ ጨረፍ አደረገና፥ ‹‹ለማጋለጥ እንኳዋን ለጊዜው አመች ሁኔታ ያለ አይመስለኝም። በሪፖርቱ ላይ እንደ ተመለከተው በብዙ ድምፅ ነው የተመረጠው›› አለ።

ታደሰ እንደ መበሳጨት አለና፥ ‹‹ሌላውስ አማራጭ?›› ብሎ ጠየቀው።

‹‹ከላይ ድጋፍ ያለው ይመስለኛል። ባይኖረው መቼ ይደፍር ነበር?. . .››

‹‹ድጋፍ ቢኖረው ታዲያ ምን ይሁን! አንተ ደሞ ትገርመኛለህ! የኛ ጥይት ቦታ አለው አሉህ? ብሎ አመናጨቀው። ሶስቱም ተያዩና ፈገግ አሉ. .

‹‹ማን አስወሰደና?››

‹‹እኔው ነኝ የፈረደብኝ!››

‹‹ታዲያስ?››

‹‹በፈጠረሽ አምላክ ተይኝ! የባሰ ውርደት፤ ከውርደትም ግርፋትና ሞትም ሊከተል ይችላል. . .››

‹‹እኔ የሸዋሉል ልጅ!››

‹‹አዎን፥ በስልክ አክብሮ ዛሬ አይመቸኝም ያለሽ ሰው፥ ሊያስረንም የሚችል መሆኑን ዘነጋሽ መሰለኝ. . .››

‹‹ይሄው አይደል የቀረው? ምን ነው ሞቴን ባቀረበው! እንደዚያ በትህትና ስጠይቀው. . . ኤጭ!. . . ምን ነው ምላሴን በቆረጠው ኖሮ!. . .››

‹‹አይደለም። አሁንም የሚያዋጣው ትህትና ነው። ደግ አድርገሻል። አሁንም የሚያዋጣው ትህትናና ዘዴ ነው።››

‹‹ትንሽ ሰው መቼም ከፍ ላድርግህ፥ ላክብርህ ሲሉት፥ ከራስ ላይ ይወጣል።››

‹‹ግድ የለሽም አይወጣም። በዘዴ የተያዘ ማንኛውም ነገር ከልኩ አያልፍም።

ወይዘሮ አምሳለ በባላቸው አስተያየት ያልተስማሙ መሆናቸውን ለመግለፅ ራሳቸውን እየነቀነቁ፥ ‹‹ከልኩ አያልፍም ሲባል ራስ ላይ እየወጣ ሊዶአል እቴ!›› ከማለታቸው፥ ልጃቸው ተሰማ በረጅም ቁመናው እየተንገላወደ ው ብሎ ገባ። ወይዘሮ አምሳለ ነገራቸውን አቋረጡና ተሰማን በትላልቅ ይኖቻቸው ከላይ ወደ ታች፥ ከታች ወደ ላይ ከቃኙ በሁዋላ፥ ‹‹ ምን ነው ንዲህ ከሰውነት ወጣህ ልጄ? አመድ የነፋብህ መስለሃል። ይህን ጢምህን ግሞ ብትላጨው ምን አለበት ልጄ? የምን ማስቀየም ነው እሱ!›› አሉት፥ ጢሙ አለ ቅጥ ማደግ እንደ አዲስ ነገር ተበሳጭተው።

አቶ ጉልላት ግን በተሰማ መጎሳቆልና ከሰውነት መውጣት፣ እንዲሁም ካለ እድሜው በድንገት መገርጀፍ ቢገረሙም፣ ጭንቅላታቸውን የመታቸው ወይዘሮ አምሳለ ያሳጤኑት ሌላ ነገር ነበር።

‹‹የደነገጥክ ትመስላለህ። ምን ሆነሃል?›› ብለው ጠየቁት።

‹‹ ሂሩቴ ደህና አይደለችም እንዴ?›› አሉ ወይዘሮ አምሳለ።

‹‹ደህና ናት›› አላቸው።

‹‹እኮ ምን ሆነሃል?›› ብለው እንደ ገና ጠየቁት፣ የተሰማን መንፈስ መሸበር እያጤኑ።

ተሰማ የሰውነትም ሆነ የመንፈስ እርጋታ አይታይበትም ነበር። እጁም እግሩም እረፍት አጥተው ይወራጫሉ። አልፎ አልፎ እንደመደንገጥ ያደርገውና ሰውነቱ ሽምቅቅ ይላል።

ወይዘሮ አምሳለ፣ ጢሙን በጥላቻ አይን እየተመለከቱ፣ ‹‹ተናገር። ምን ይዘጋሃል?›› አሉት።

ተሰማ ሁለቱንም በአይን ጨረፍታ ተመለከተና አቀርቅሮ፣ ‹‹ስለ ደርቤ ጠዋት ደውዬ ነበር. . .›› አለ።

ወይዘሮ አምሳለ፣ የደርቤ ስም እንደ ገና በመነሳቱ በአንድ ፊት እየተንገፈገፉ፣ በሌላ በኩል ደግሞ ተሰማ ሊናገር ያሰበውን ለመስማት እየቸኮሉ፣ ‹‹አዎን፣ ምን ተፈጠረ ታዲያ?›› ብለው አጣደፉት። እንዳቀረቀረ ቀርቶ፣ በጫማው ወለሉን እየፈተገ፣ ‹‹በሂሩት በእኔና በደርቤ መካከል አደገኛ ሁኔታ ተፈጥሮአል›› አላቸውና፣ ከባድ ሸክም ከትከሻው ላይ እንዳወረደ ሰው ቁና ተነፈሰ።

‹‹እንዴት ያለ አደጋ በል?›› አሉ አባትየው።

አሁንም እንዳቀረቀረ ወለሉን በጫማው በሀይል እየፈተገ፣ ‹‹እዚህ. . .ኤ. . .ኢ. . .ህ. . .አ. . .ፓ መሆናችንን ያውቃል›› አለ።

‹‹ኢ.ህ.አ.ፓ.? እናንተ? የኔ ልጆች? ይህንኑ ነበር የፈራሁት!›› አሉ አቶ ጉልላት:: ቀጠሉና፣ ‹‹ምን ቆርጦአችሁ ነው እዚያ ውስጥ የገባችሁት? አዬ ዘንድሮ! አዬ ዘንድሮ! ›› ብለው ራሳቸውን ይዘው አቀረቀሩ::

ወይዘሮ አምሳለ ከተቀመጡበት ተነስተው በሁለቱም እጆቻቸው ራሳቸውን ይዘው እየተንጎራደዱ፣ ‹‹ወይ ጉዴ! ወይ ጉዴ! ወይ ጉዴ!›› እያሉ ቅልጥ ያለ ሙሾ ማውረድ ጀመሩ::

አቶ ጉልላት የራሳቸውን ሀዘን፣ ብስጭትና ንዴት ትተው ተዪ እንጂ! ምን ነካሽ?›› እያሉ ግልግል ገቡ::

‹‹ጉልላቴ ተወኝ! ተወኝ! ተወኝ! ሂሩት፣ ሂሩቴ ልጄ! ይሄኔ በመንገድ ዳር ደፍተዋት ይሆናል፣ ደፍተዋት ይሆናል. . .››

‹‹የመላኩ ያለህ! አታሙዋርቺባት! ተይ ነው የምልሽ. . .››

‹‹እኔን. . . እኔን ያስቀድመኝ ልጄ! እናትሽ ትደፋልሽ ልጄ!›› አሉና፣ ወደ ተሰማ መለስ ብለው፣ ‹‹ምን በደልኩዋችሁ? ምን በደልኩዋችሁ?›› እያሉ ራሳቸውን ይዘው ጮሁበት::

ተሰማ በእናቱ ጩኸት ተሸማቅቆ የባሰውን አቀረቀረ:: አንድ ወንድና አንዲት ሴት የቤት ሰራተኞች በወይዘሮ አምሳለ ጩኸት ተደናግጠው መጥተው ከበር ላይ ቆመው ነበር::

ነገሩ ባይገባቸውም በእሜቴ ልቅሶ ሆዳቸው ባብቶ አይኖቻቸው እንባ አቅርረው ነበር:: አቶ ጉልላት በአንድ ፊት ባለቤታቸውን እያፅናኑ፣ ሰራተኞቹን፣ ‹‹ኧረ ምንም የለም:: ደህና ነው:: ብለው ወደ ስራቸው እንዲመለሱ አዘዙአቸው::

ሰራተኞቹ መሄዳቸውን ካረጋገጡ በሁዋላ ወደ ተሰማ ተመልሰው፣ ‹‹ለመሆኑ ሂሩቴ የት ናት?›› ብለው ጠየቁት::

‹‹ሱቅ ናት:: እዚያ ትቼአት ነው የመጣሁት›› አላቸው፣ ቀና ብሎ::

ወይዘሮ አምሳለ ወዲያውኑ ስልክ ደወሉ። ከብዙ ጊዜ በሁዋላ ሱቁ ውስጥ የሚሰራው አሸከር ስልኩን አነሳ። ሂሩት አሁን በቅርቡ የወጣች መሆንዋን ነገራቸው።

‹‹ጉዋደኞችዋ ዘንድ ሄዳ እንደሆን?›› አሉ። ወይዘሮ አምሳለ እያከታተሉ ስልክ መደወል ጀመሩ። ዘመድ ቤት - የሂሩት ጉዋደኞች ቤት - አንድም አልቀራቸው። ሂሩት ያለችበትን ግን የሚያውቅ አልነበረም።

‹‹ጉልላቴ ዝም ትለኛለህ? ልጄን አጣሁዋት ኮ. . .›› አሉ ተስፋ ቆርጠው።

‹‹ምን ሆንሺብኝ?››

‹‹እንፈልጋት እንጂ!››

‹‹የት ብለን? አዲስ አበባ ሰፊ ነው. . .››

‹‹ሬሳ ወድቆአል በተባለበት ሁሉ. . .››

‹‹አታሙዋርቺባት ነው የምልሽ አንቺ ሴት! ዛሬ በቀኝ ጎንሽም አልተነሳሽም? ወቸ ጉድ!››

ተሰማ ከተቀመጠበት እየተነሳ፥ ‹‹ባይሆን እኔ ዞር ዞር ብዬ ልፈልጋት›› ሲል አሳብ አቀረበ።

አቶ ጉልላት ተቆጥተው፥ ‹‹አርፈህ ተቀመጥ! ከዛሬ ጀምሮ እግርህ ከዚህ ቤት ዝር እንዳይል! ዋ! ገብቶሃል? አደብ ግዛ። ከእንግዲህ ልጅነት የለም። እምቢ ያልክ እንደሆነ ካንተ ወይም ከኔ ይለይልናል። ልባርግ!›› አሉት።

አባቱ እንደዚያ ምርር ብለው ተናግረውት ስለማያውቁ ተሰማ ደነገጠ። እናቱም ለልጆቻቸው እንደዚያ ሲጨነቁና ሲያለቅሱ በማየቱ በአንድ ፊት ልቡ ተነክቶ ነበር። ስለሆነም፥ ፈቃዳቸውን ከመፈፀም ሌላ አማራጭ እንደሌለው ታወቀው። ይሁን እጂ እህቱን ካለችበት ፈልጎ የማግኘቱ ጉዳይ ምን ያህል አስቸኳይ እንደሆነና ማምሻዋን ምን ለማድረግ እንዳቀደች ሊነግራቸው ፈልጎ ነበር። የወላጆቹን አሳዛኝ ሁኔታ በማየትና የተናገርኩ እንደ ሆን የባሰውኑ ተደናግጠው አንድ ነገር ይሆናሉ፥ ወይም ሊፈልጉዋት ወዲህና ወዲያ ሲሉ

ፍፁም እንግዳ የሆነ የጭካኔ መልክ ስለታያቸው ተጨንቀው፥ ‹‹ከጠዋቱ የተለየ ሌላ ምን አስበሻል?›› ብለው ጠየቁአቸው፡፡

‹‹ምንም፡፡››

ሁለቱም በዝምታ ተዋጡ፡፡

አቶ ጉልላት የሚስታቸውን አሳብ ዘልቀው ለማወቅ አእምሮአቸውን ሲቡዋጥጡ ከቆዩ በሁዋላ፥ ‹‹ተይ አይሆንም ንገሪኝ፡፡ ብንመካከርበት ይሻላል፡፡

‹‹ምንድን ነው የምነግርህ? እኔም አላውቀውም›› አሉአቸውና ከት ብለው ሳቁ፡፡

አቶ ጉልላት በሚስታቸው ሁኔታ አንድ አይነት ፍርሃት አደረባቸው፡፡ ወይዘሮ አምሳለ ደገሙና፥ ‹‹እኔም አላውቀውም›› ብለው በሳቅ ተንከተከቱ፡፡

ደርቤ ሲመጣ. . . ትእግስት. . . ትእግስት. . .ነገም ይሁን ከነገ ወዲያ ሲመጣ. . . መቼም ገንዘብ የማይስበው የለም. . . መኪና ሲገዛ!. . . የጨዋ ልጅ ተዋርዶ መናጢ ድሀ በመኪና ሲኮፈስ. . . ሲመጣ በጥሩ እንጀራና ወጥ ጠቅልሎ የሚጎርሰው መርዝ ታያቸው፡፡

እንደ ገና ከት ብለው ሳቁ፡፡

‹‹ምን ሊሆን ይችላል ትያለሽ? ማታ ሲናገር የነበረውን አልሰማሽም? የደርግ ባንዳ ሆኖአል፡፡ መክዳቱ ነው፡፡ ባይከዳ ኖሮ ሹልክ ብሎ አይጠፋም ነበር፡፡››

ሂሩት ትላልቅ አይኖችዋን እንደ ጡዋፍ እያንቦገቦገች ዘንፋላ ጠጉሩዋን ከፊትዋ ላይ ለማራቅ ጭንቅላትዋን ወደ ቀኝ መታ እያደረገች፥ ‹‹ቢከዳ አይገርመኝም፡፡ ግን አንተ እንዳልከው በአቅዋም የተነሳ አይመስለኝም›› አለችው፡፡

‹‹ፈርቶ ይሆናል!›› አላት፡፡

‹‹ቢፈራም አይገርመኝም፡፡ ለህይወቱ የማይፈራ ማን አለ? ህይወት ውድ ናት፡፡ መኖር ራሱ ደስታ ነው፡፡

‹‹ግን እኛ አለን፥ አልፈረጠጥንም!›› አላት፡፡

‹‹እፉ! ተወኝ እባክህ! ህይወቱን የማይወድ የለም፡፡››

‹‹አንቺ በተለይ. . .››

‹‹አዎን፥ እኔ በተለይ! ህይወትን እወዳለሁ፡፡ መኖር ራሱ ልዩ ደስታ ይሰጠኛል፡፡ እያንዳንዱ ቀን ልዩ ጣእመ ዜማ ነው የሚያበስርልኝ፡፡ ሙዚቃ ነው፥ የማይጠገብ የህይወት ሙዚቃ ነው፥ የማይጠገብ የህይወት ሙዚቃ! ለዚህ ይሆናል አደጋ የሚባል ነገር መኖሩ የማይታወቀኝ፡፡ ግን አደገኛ ጨዋታ ላይ ነው ያለነው፡፡››

‹‹እንከኩዋን ሄደ ነው የምትይው?››

‹‹እፉ! አላልኩም!››

‹‹ታዲያ ምንድን ነው የምትይው? ሊገባኝ አልቻለም›› አላት ተበሳጭቶ፡፡

‹‹እኔ የምለው፥ ምንድን ነው የምለው? አዎን፥ ከአደጋ ጋር ድብብቆሽ መጫወት ደስ ይላል፡፡ ደስ አይልም?›› ብላ ጠየቀችው፡፡

ተፈጥሮዋ ሆኖ ከአንድ ቦታ እንኩዋን ረግታ መቀመጥ አትወድም። እጆዋንም፥ እግሮዋንም፥ ሰውነትዋንም ማንቀሳቀስ ታዘወትራለች። ህይወትዋ በእንቅስቃሴ ስልት ላይ የተመሰረተ ይመስል ነበር። በአንድ አሳብም አትረጋም። አዲስ አሳብ ይስባታል፤ አዲስ ነገር ይማርካታል። ታዲያ ተፈራ ደስ አይለውም። ሁኔታዋ ሁሉ የመንፈስ እረፍት ይነሳዋል። ግን፥ ከአይኑ ሊለያት አይችልም። ሳይወድ ቀናተኛ አድርጋዋለች።

‹‹እኔ ደስ አይለኝም›› አላት።

‹‹እንግዲያውስ አንተም እንደ ወንድሜ ድንች ነህ! የልብ ትርታን ከፍ የማያደርግ ህይወት መኖር ትርጉሙ ምንድን ነው? ትርጉም የለውም። ስሜት የሌለበት ህይወት፥ ህይወት አይደለም። የልብ ትርታን ከፍ የሚያደርግ ስሜት ግን የህይወት ቅመም ነው›› አለችው፥ ጥፍሮችዋን ቀይ ቀለም እየቀባች። ቀጠለችና፥ ‹‹ከአደጋ ጋር ድብብቆሽ እየተጫወትን የምናደርገው ነገር ሁሉ፥ ወረቀት መበተኑ፥ አርማ መስቀሉ፥ መንገዶችና ግድግዳዎች ላይ መፃፍ የልብ ትርታን ከፍ ያደርጋል። እና ደስ ይላል!›› አለችው።

‹‹በፖለቲካ እሳት መጫወት!›› አላት ተገርሞ።

‹‹እሱም ህይወት ነው! በአደጋው መጠን የልብ ትርታ ከፍ ይላል። እና ለህይወት የበለጠ ውበትና ትርጉም ይሰጣል!››

‹‹ዋዛ መስሎሽ››

‹‹እኔ የማየው አደገኛነቱን ሳይሆን የሚያስከትለውን የልብ ትርታ ነው። ስሜት የማይሰጡ ተመሳሳይ ሰአቶች እግር በእግር እየተተኩ ቀኑ መሽቶ ሲነጋ ምን ህይወት ነው?››

ተናደደና፥ ‹‹ለብዙሀኑ እግር በእግር የሚተካ ተመሳሳይ ሰአት የሚባል ነገር የለም›› አላት። ‹‹እያንዳንዷ ደቂቃ ያለ ከፍተኛ የልብ ትርታ አታልፍም። የእለት ጉርስ ማግኘት ከፍተኛ ትርታን ይጠይቃል። ረሀብ ፋታ አይሰጥም። ለብዙሀኑ እያንዳንድዋ ደቂቃ ትርጉም አላት፤ የሞትና ሽረት ጉዳይ ናትና። ከሞት ጋር ነው እነርሱ ድብብቆሽ የሚጫወቱት። አንቺ ግን

የቡርኸዋ ኑሮ መኖር ስልችቶሽ ነው ከአደጋ ጋር የድብብቆሽ ጨዋታ የምትፈልገው።

ቁም ሳጥን ላይ ወዳለው ትልቅ መስተዋት ጠጋ ብላ ሁኔታዋን ከላይ እስከ ታች ድረስ በረጋ መንፈስ ተመለከተች። የለበሰችው ጥቁር ሸሚዝና ሱሪ የሰውነትዋን ቅርፅ አጉልቶ ያሳያል። እየተዘናፈለ ከከብ ትከሻዋ ላይ የወደቀውን ጠጉርዋን ሰብስባ በቀይ ሻሽ ሸብ አደረገችው። ቀይ የከንፈር ቀለም ከቦርሳዋ አውጥታ በጥንቃቄ ተቀባች። ፈገግ አለች። ወደ ተፈራ መለስ ብላ፣

«እንግዲያውስ፣ ከብዙሀነ አንድዋ ብሆን ምንኛ ደስ ባለኝ!» አለችው።

«አይመስለኝም! ከብዙሀነ አንድዋ ብትሆኚ የተወለድሽበትን ቀን በየደቂቃው ትረግሚ ነበር!» አላት።

«የልብ ትርታዬን የሚጨምር ከሆነ ለምን እረግማለሁ» አለችው።

«ታዲያ የብዙሀነ የኑሮ ውጣ ውረድ የልብ ትርታሽን እንደሚጨምር እያወቅሽ፣ ከእድገር በህብረት ዘመቻ ለምን ቀረሽ?»

«አንተስ ለምን ቀረህ?» አለች፣ ተቆጥታ።

«አንቺ ስለቀረሽ። አሁንም እዚህ እሳት ውስጥ የገባሁት ባንቺ ምክንያት ነው. . .»

«በኔ አታሳብብ!»

«ስራም ስላጣሁ ነው። መኖር አለብኝ፣ አይደለም? አላት አዝኖ።

«እንደሱ በላ! ለምን በኔ ታሳብባለህ» አለችው፣ ረጅም አንገትዋን እንደ እስክስታ ወራጅ እንክት አድርጋ።

ያባቱ መታሰር የንብረታቸው መወረስ፣ ስራ የማጣቱ በየመስሪያ ቤቱ ማመልከቻ ባገባ ቁጥር ያባቱን ስም ሲያዩ የፊታውራሪ ልጅ ነህ እንዴ! ወደ ፊት እናሳውቅሃለን ብለው ተስቦ የያዘው ይመስል እንዳይጋባባቸው ቶሎ ከቢሮአቸው እንዲወጣላቸው የሚጣደፉት ቢሮክራቶች ትዝ አሉት። እንጠራሃለን። እናሳውቅሃለን። አትመላለስ። ጠብቅ። ግን የሚራኝ ቁምጥና ወይስ ለምፅ የሚያሳውቀኝ የለም፣ ተስፋ የማያልቅ ተስፋ ብቻ!

አለብኝ? ያባቴን ስም ስጠራ አቤት ሲፈሩ! ውሾች! ወኔ–ቢስ ቢሮክራቶች! ስሜን ጠርቼ ያባቴን ስም ላልደግም! ይገርማል። በፊት ያባቴ ስም ለማንኛውም ቦታና ጊዜ የሚያገለግል የይለፍ ወረቀት ነበር። አሁን ግን ያደጋ ምልክት ነው። ቀይ መብራት-የጥፋት ደወል - እያለ ሲያስብ ቆየና፥ ‹‹ልጅ ባባቱ ሀጢአት ይቀጣል? ማን ያወጣው ሕግ ነው?›› አለት።

‹‹ልጅ ያባቱን ሀብት ይወርስ የለ!›› አለችው፥ ፀጉርዋን እያስተካከለች።

‹‹ምን ማለትሽ ነው?››

‹‹አትጩህ! የውርስ ጉዳይ ቢሆን ሽንጥህን ገትረህ ትከራከር ነበር። ባባት ስም ስንነግድ ከኖርን ለምን ባባት ሀጢአት አንቀጣም፥ እ?›› አይደለም? ዲቃላም ብትሆን ያባቴ ልጅ ነኝ ብለህ ምስክር ትፈልግ ነበር - ለመውረስ። አሁን ያባትህ ስም እንቅፋት ስለሆነብህ ያባቴ ልጅ አይደለሁም ብለህ ልትክድ ትፈልጋለህ። እና፥ ልጅ ባባቱ ሀጢአት ለምን ይቀጣል ትላለህ።

‹‹ተሳስተሻል። ፍፁም ተሳስተሻል››

‹‹ኡፉ! እሱን ተወውና ይልቅ ስለ ተሰማ ለላእከ ምን ብዬ እንደማስረዳ ንገረኝ።››

‹‹ተሳስተሻል. . .››

‹‹ኡፉ! ምን ብዬ እንደማስረዳ ንገረኝ ነው ያልኩህ!››

‹‹ምን ምክንያት እንደምትሰጪ እኔ አላውቅም!››

‹‹ተቆጣህ እንዴ? አትቆጣ። ማታ ከፍተኛ ስራ ይጠብቀናል። ሰፈራችንን ቀይ በቀይ ነው የምናደርገው. . .››

‹‹ምኑም ደስ አላለኝም።››

‹‹እኔ ግን ከደስታዬ ብዛት የልቤ ትርታ ጨምሮአል። ነገ ጠዋት የስራችንን ውጤት ስንመለከት ደግሞ የበለጠ ደስ ይለናል። ይልቅ ወደ ሀገ እንሂድ። እንቅስቃሴ የህይወት ቅመም ነው›› ብላው ተያይዘው ወጡ።

መበሳጨቱ ስለገባት እጁን ፈልጋ ያዘችው። መለስ ብሎ ተመለከታት። አይኖቻቸው ተገናኙ። ፈገግታ ተለዋወጡ። እጅዋን ጠበቅ አድርጎ ያዘ።

ወደ ጆሮዋ ጠጋ ብሎ፥ ግሩም ጠረንዋ ህይወት ይሰጠው ዘንድ ወደ ውስጥ እየተነፈሰ፥ ‹‹ጊዜያዊ ደስታ. . . እ. . . ከጊዜያዊ የልብ ትርታ የላቀ አላማ በኖረሽና የዘላለም ባርያሽ ሆኜ በቀረሁ፥ ከማለቱ የተሳፈሩበት መኪና በመንገድ ቆመ። ባለ ሰይቼንቶው በድንገት ፍሬን በመያዙ ፊት ለፊታቸው ካለው ወንበር ጋር ሊላተሙ ምንም አልቀራቸውም ነበር። ከፈለጉበት ስፍራ ደርሰው ስለነበረ ተያይዘው ወረዱ። ገበያው በመቀዝቀዙ ሰይቼንቶ ነጂው አሳቡ የባከነ ይመስላል። ከመንገድ ሌላ ህይወቲ የሌለው ይመስል ደግሞ፥ አይኑ ከመንገድ ለሌላ አይመለከትም። ሂሩት ብሽቅ ብላ ሳንቲሞቹን አፍንጫው ላይ ወረወችለት።

ከአውራ መንገድ እምብዛም ርቀው አልሄዱም። ኮረኮንች መንገድ ተከትለው በእግር ትንሽ እንደተጉዋዙ፥ ሂሩት ወደ አንድ ተራ መሳይ ኪዮስክ ጠጋ ብላ፥ ‹‹ቅርንፉድ አለ?›› ብላ ጠየቀች።

‹‹ለምን የሚሆን?›› አላት ባለ ሱቁ።

‹‹ለጉትቻ›› አለችው።

ጠጉሩን ተላጭቶ የራስ ቅሉ የሚያብለጨልጨው ወጣት ባለ ኪዮስክ ወደ ተፈራ መለስ ብሎ፥ ‹‹ምን ልታዘዝ?›› አለው።

‹‹ክብረ ሰማይ›› ብሎ መለሰለት።

‹‹ክብረ ሰማይ ለምን?››

‹‹ለቂጥኝ››

ባለ ኪዮስኩ ማንነታቸውን በማወቁ ፈገግ ብሎ ግራና ቀኝ በመመልከት በአካባቢው ሰው አለመኖሩን ካረጋገጠ በሁዋላ፥ ከመስኮቱ ስር ያለችውን ትንሽ ስውር በር ቶሎ ከፍቶላቸው ሹልክ ሹልክ እያሉ ገቡ። ቡቱቶ የለበሱ ሶስት ጭቅቅታም ሰዎች በጀበና ሻይ ጥደው፥ ቁጭ ብለው ጫት ይቅማሉ። ቡቱቶውና ጭቅቅቱ የምድር ጎስቋዋላ ቢያስመስላቸውም ቅሉ፥ የሰውነታቸውን

ሳይቀር፥ ክፍሉ ውስጥ በሚታየው መግነጢሳዊ እቅስቃሴ ልቡ ከመሳብ አላመለጠም። ሂሩትም በበኩልዋ የልብዋ ትርታ እየጨመረ ሲያስፈነድቃት ምንም አልቀረውም ነበር።

ላእከ ከጠረጴዛው ላይ ቀና ብሎ ተንጠራራና፥ ‹‹አ! እንቁጣጣሽ!›› አላት። እንቁጣጣሽ የሂሩት የኮድ ስም ነበር። ትኩር ብሎ በአድናቆት እየተመለከታት፥ ‹‹ውበትሽ በየቀኑ እየፈካ ይሄዳል›› አላት። ሲናገር ድምፁ እንደ ነጎድጓዋድ ያስተጋባል።

‹‹አመሰግናለሁ። የልቤ ትርታ እየጨመረ ስለሚሄድ ይሆናል የምፈካው!›› አለች ሂሩት፥ ፈገግ ብላ።

‹‹እንደ ምሽት ፅጌረዳ!›› አላትና፥ ኩበት የመሰለውን ለምቦጩን በምላሱ ልሶ አረጠበ።

ላእከ ለሂሩት ውበት ያለውን አድናቆት ተፈራ አልወደደም። ባባበው እጁ ላእከ ይባስ ብሎ እንደ ሂሩት ጥጓ ጎፈሬውን አከክ አከክ አድርጎ ዝም አለ። ላእከ ይባስ ብሎ እንደ ሂሩት ጥሏ ያህል ቀጥሮት ምንም ግምት ወይም ትኩረት ሳይሰጠው በመቅረቱ ውስጡ በግኖ ነበር።

ላእከ አንድ ነገር ለማለት እንደ ፈለገ ያስታውቃል። ግን የሀሺሽ ጢስ በሰውነቱ ውስጥ እስካለ ድረስ አሳበ ብኩን በመሆኑ፥ ለማለት የፈለገው ነገር ቶሎ አይጨበጥለትም። ወዛም ጠይም ፊቱን አጨማዶ ሲያስብ ከቆየ በሁዋላ ‹‹አ! ላጺሶ በጠዋት ለጥብስ ደርሶአል። ከኛም ወገን አንድ የመከላከያ ጉዋድ ቆስሎ ሊያዝ ነበር። ራሱን ገደለ። ይህንን ነው እኔ ዲሲፕሊን የምለው። ራሱን የገደለው እኛ እንድንኖር ነው። እና፥ እንኖራለን። መሞት ብቻ አይደለም። ለመኖር መግደልም አለ። ላጺሶ ባይሞት ኖሮ ይህ ህዋስ እስካሁን አይኖርም ነበር። ደግነቱ ላጺሶ ከያዘው ምስጢር ጋር ወደ መቃብሩ ወርዶአል›› አለና፥ ለመጨመር የፈለገው አሳብ ስለ ጠፋው ፊቱን በትልቅ እጁ ማሻሸት ጀመረ።

የለበሰው ነጭ ሸሚዝ እጀ ጉርድ ስለነበረ፥ ፊቱን ሲያሻሽ ጡንቻው እንደ አሎሎ ሲንከባለል ይታያል። ሁኔታው ሁሉ በልቡ ፍርሃት ስለሚለቅበት፥ ተፈራ የባሰውን ጠላው። ሂሩት በላእከ ጡንቻና ቆራጥነት፥ ባለው ስልጣንና

በሚታይበት ኩራት ተማርካ አፏዋን ከፍታ ስለምትመለከተው፣ ተፈራ፣ ቅናትም አድሮበት፣ ጥርሱን ይነክስ ነበር።

ሂሩት ጡንቸኛ ወንድ ስታይ ያምራታል። ቀጭን ወንድ ስታይ ያምራታል። ጠይም ወንድ ስታይ ያምራታል። ጥቁር ስታይ ያምራታል። ቀይ ወንድ ስታይ ያምራታል። ወንድ ሲባል እስዋን ለማስደሰት ብቻ የተፈጠረ ይመስላታል እና፣ በወንድ ገላ ትደሰታለች። ከተደሰተችበት በሁዋላ አትወደውም ትንቀዋለች።

‹‹ኦ! በነገራችን ላይ›› አለ ላእከ ‹‹ጥቆማችሁ ጥሩ ነበር። ለትግል ትክክለኛ ጥቆማ በጣም አስፈላጊ ነው። ሳልረሳ. . . ሳልረሳ. . . መሳሪያዎቹና ገንዘቡ ደርሶአችሁአል?›› ብሎ ጠየቀና እፀ ፋርሱን ወደ ውስጥ ማገ።

ተፈራ፣ ‹‹አዎን ደርሶናል›› ብሎ መለሰለት።

‹‹ምን ሆነሃል? ያዘንክ ወይም እኔ እንጃ፣ አንድ ነገር የምታስብ ትመስላለህ›› አለው።

‹‹አላዘንኩም፣ አሳብም የለብኝም!››

‹‹አዎን፣ በአብዮት ጊዜ ሀዘን የለም። ማኦ፣ አብዮት የጭቁኖች በአል ነው ሲል ጨርሶታል። ማሰብም ካንተ አይጠበቅም። ድርጅትህ የማሰቡን ተግባር ያከናውንልሃል። ካንተ የሚጠበቀው ድርጊት. . . ድርጊት. . . ድርጊት! ብቻ ነው›› አለውና፣ ቀጥሎ፣ ‹‹ታወላውላለህ መሰለኝ?›› ሲል ጠየቀው።

‹‹የመደቤ ልጉዋም እየሳበኝ ይሆናል›› አለው።

ላእከ ፈገግ ብሎ ወተት የመሰሉ ትላልቅ ጥርሶቹን እያሳየው፣ ‹‹አዎን፣ ማኦ እንዳለው፣ ከመደብ ውጭ ባህርይ ወይም ተፈጥሮ የሚሉት ነገር የለም። የሰው ተፈጥሮ እንደ ማንኛውም ነገር የሚመራው በዲያሌክቲካዊ ህግ ነው። የሰው ተፈጥሮ እንደ ማንኛውም የሰው ተፈጥሮ አንድ ቦታ ረግቶ የሚቀር ኩሬ አይደለም። እንደ ማንኛውም ነገር እየተለወጠ እያደገ የሚሄድ ነው። ንቃት፣ ዲሲፕሊን፣ ድርጊት - ከዚያ በሁዋላ ማወላወል የለም። ኦ! አሁን ትዝ አለኝ። ወንድምሽ የት አለ?›› ብሎ ሂሩትን ጠየቃት።

የተዘጋጀችበት ጥያቄ ነበርና፣ «በድንገት አሞት ተኝቶአል» ብላ ፍንክች ሳትል መለሰችለት።

«ይህ ድርጅት ለበሽተኞች ቦታና ጊዜ የለውም!» ብሎ በነጎድጉዋዳዊ ድምፅ በመጮህ ጠረጴዛውን መደሻ በሚመስለው እጁ አንዴ ሲመታ፣ ክፍሉ ውስጥ የነበሩት ሁሉ ዞር ብለው ይመለከቱት ጀመር።

ሁሉም፣ ምን ይከተል ይሆን? በማለት ጆሮአቸውን አቁመውና አይናቸውን አፍጠው ይመለከቱት ስለነበረ፣ በተፈጠረው ሁኔታ ተጠቅሞ መልእክት ለማስተላለፍ በመፈለግ፣ «እኔ ለበሽተኞች፣ ለደካሞችና ለተሸናፊዎች ደንታ የለኝም!» አላቸው። «የምናካሂደው የድኩማን ድርጅት አይደለም። ተጋድመን ህመማችንን የምናዳምጥበት ጊዜ ላይ አይደለም ያለነው! ያሮጊቶች ስሞታ አልፈልግም! ነፃ ርምጃ በተቃጣብን ባሁን ጊዜ፣ እያቃሰትን ከመታገል ሌላ ምርጫ የለንም። ይህ ለሁላችንም ግልፅ መሆን አለበት።»

ነጎድጉዋዳዊ ድምፁ አጉዋርቶ ዝም ሲል፣ ክፍሉ ፀጥ እረጭ ብሎ ቀረ። ከጥቂት ጊዜ በሁዋላ ነበር ሁሉም ወደየስራው ተመልሶ ጎንበስ ቀና ማለት የጀመረው።

«እንዲነሳ እንነግረዋለን» አለ ተፈራ የሂሩትን ውሸት ደግፎ።

«ንገሩት! መነሳት አለበት። እንዲያውም አሁን ትዝ አለኝ። ዛሬ ማታ ስራ አላችሁ አይደለም እንዴ?»

«አዎን፣ ተዘጋጅተናል» አለች ሂሩት።

«ታዲያ ምናባቱ ሆኖ ነው የሚጋደመው? ወይስ ፈርቶ ነው? ለመሆኑ ስሙ ማን ነበር? የሰው ስም አይያዝልኝም! እና፣ ለፈሪ ሰው ደም አክብሮት ሆነ ርህራሄ የለኝም!» አለና፣ አሁንም እፀ ፋርሱን ወደ ውስጥ ማገ።

ተፈራ፣ አዎን፣ ከእንቁጣጣሽ ሌላ ስም አይያዝልህም! ብሎ በልቡ ረገመው።

‹‹በነገራችን ላይ፥ ማን ነው የምትሉት? እፋ! ይሄ የቀበሌያችሁ የአብዮት ጥበቃ ሊቀ መንበር ሆኖ የተመረጠው? ስሙን አምጡልኝ!››

‹‹ደርቤ›› ብላ ነገረችው፡፡

‹‹አዎን፥ ደርቤ፡፡ ማታ ነግራችሁኝ ስሙ ጠፋብኝ፡፡ የቤት አሽከራችሁ ነበር አላላችሁኝም እንዴ?››

‹‹አዎን፥ ነበር›› አለችው፡፡

‹‹ጠባዩን፥ ደካማና ጠንካራ ጎኑን ታውቃላችሁ ማለት ነዋ! ለመሆኑ ምን አይነት ሰው ነው?››

‹‹ብጣም ጥሩ ልጅ ነበር፡፡ አሁን አላውቅም፡፡ ታታሪ ነው፡፡ በዚህ ላይ ደግሞ ራሱን ከፍ ለማድረግ ይጥራል›› አለች ሂሩት፡፡

‹‹ምን ለመሆን?›› ብሎ ጠየቃት፡፡

‹‹እኔ እንጃ!›› ብላ ክብ ትከሻዋ እንደ እስክስታ ወራጅ መታ አደረገች፡፡

‹‹ማወቅ አለብሽ፡፡ እኔ እንጃ ማለት መልስ አይደለም›› አላት፡፡

‹‹ተሰማ እንደ ነገረን ከሆነ የሂሩትን ትኩረት ለመሳብ ብሎ ነው የሚንጠራራው!›› አለው ተፈራ፡፡

‹‹ተሰማ እንደ ነገረን ከሆነ የሂሩት ትኩረት ለመሳብ ብሎ ነው የሚንጠራራው!›› አለው ተፈራ፡፡

‹‹አ! ይሄማ ጥሩ ነው፡፡››

‹‹ማ? እኔ?››

‹‹አዎን አንቺ!››

‹‹እንዴት አድርጌ?››

ላእከ ሀሺሹን ለመጨረሻ ጊዜ በረጅሙ ስቦ ጭሱን ዋጠ፥ ቆየ-ቆየ-ቆየ እና ወደ ውጭ ሲተነፍስ ትንሽ ጭስ እንኳዋን ካፉ አልወጣችም. . .

‹‹በውበትሽ ተጠቀሚ!›› አላት ሂሩትን፥ ‹‹የሴቶች ውበት ምን ጊዜም አደገኛ ወጥመድ ነው። በነገራችን ላይ፥ አንድ ጆሴ ቀርቶ ስንት ታላላቅ ሰዎችም በሴቶች ውበት ተጠምደው ጉድ ሆነዋል። የሴቶች ውበት በተለይም በኛ ህብረተሰብ ውስጥ ትልቅ የፖለቲካ መሳሪያ ሊሆን ይችላል። ግብረ ስጋ ርካሽና ጠቃሚ መሳሪያ ነው። እንዲያውም አሁን ሳስብ እንቁጣጣሽ በዚህ ረገድ ብዙ ጥቅም ልትሰጨን ትችያለሽ›› አለ ላእከ፥ በመጣለት አሳብ ተደስቶ።

ተፈራን ግን አሳቡ አቅለሽልሾት ቁዋቅ ሊለው ትንሽ ቀርቶት ነበር። በዚህ ላይ የወንድነት ወኔው ተቀስቅሶ ምንም ሳይፈራ፥ ‹‹ርካሽና ሰይጣናዊ አሳብ ነው!›› አለ፥ ድምፁን ከፍ አድርጎ። ቀጠለና እሳት ጉርሶ እሳት ለብሶ ‹‹እኔ እያለሁ ይህን አታደርግም! እንድታደርግም የሚያስገድዳት ሃይል የለም!›› አለ።

ላእከ የሚያስገድዳት ሃይል እንዳለ ሊያሳየው ፈልጎ ነበር። እንዲያውም ሂሩትን ሳብ አድርጎ ከተፈራ ፊት ሊስማት አሰበና ተወው። ግን አሳቡን ጨርሶ ከአእምሮው ውስጥ አላወጣም። ለጊዜው በአሳቡ ውስጥ ቅድሚያን የያዘው የፖለቲካ ሁኔታ፥ ማምሻውን የሚፈፅሙት ከፍተኛ ግምት የተሰጠው የቅስቀሳ ተግባር ስለነበረ፥ ቆይ ሌላ ጊዜ እሰራልሃለሁ በማለት እልኩን ውጦ በልዝብ አንደበት፥ ‹‹ትወዳታለህ መሰለኝ?›› አለው።

‹‹የግል ጉዳዬ ነው!›› ብሎ መለሰለት።

የላእከ ስሮች ተገታተሩ። ሆኖም፥ ንዴቱን እንደ ምንም ውጦ፥ ‹‹ለከፍተኛ አላማ የተፈጥሮን ውበት መጠቀም ነውር አይደለም! ወይስ በአላማችን አታምንም ማለት ነው?›› አለው።

ላእከ ወዴት ሊመራው እንደ ፈለገ ስለ ገባው ተፈራ ዝም ብሎ ቀረ።

‹‹አልመለስክልኝም እኮ!››

‹‹እኔ ያልኩት፥ እኔ. . .የምለው. . .እወዳታለሁ. . .እና።››

‹‹አዎን የምትለው ገብቶኛል። እኔም ትሽርሙጥ አላልኩም።›› በውበትዋ ተጠቅማ. . . ማን ነው ስሙ? አዎን፥ ደርቤን ታግባባውና ወደኛ ትሳበው ነው ያልኩት. . .››

‹‹ለምን አይደመስስም?›› አለው ተፈራ፡፡

‹‹ከሞተ በህይወት ያለ ሰው ይጠቅማል ብዬ ነው፡፡ ልንጠቀምበት እንችላለን. . .››

‹‹ግን መስመራችንን ያውቃል እኮ!›› አለች ሂሩት፡፡

‹‹ውበት የማያሸንፈው ልብ የለም! ተፈራም እንቦሳ የሆነው በውበትሽ ተማርኮ ነው፡፡ ፈገግ በይና እንኩዋን የደርቤን ልብ ሰራዊት ትፈቺያለሽ፡፡ ዘዴ ፈልገሽ ቅረቢው፡፡ ሳታውቂው ምርኮኛሽ ይሆናል፡፡ ቀላል ነው! አላት፡፡

ላእከ በደርቤ አሳቦ ስለ ራሱ ልብ መማረክ ነበር የሚናገረው፡፡ ከነገ ጀምሮ፥ ሂሩት ከአጠገቡ ሳትለይ እንድትሰራ ለማድረግ የቆረጠው የጀመረውን አረፍተ ነገር ከመጨረሱ በፊት ነበር፡፡ ስለተፈራ እንደ ሆነ ገሃነም አፉን ከፍቶ ሊጠብቀው ይችላል ብሎ በአሳቡ ቆረጠ፡፡

ተፈራም በበኩሉ ከዚህ ሁሉ ጣጣ ለመውጣት በልቡ ቆርጦ፥ እግሩ ካለበት ክፍል ውስጥ የሚወጣበትን ደቂቃ ነበር የሚጠብቀው፡፡ እርግጠኛ ያልሆነበት ነገር ቢኖር የሂሩትን አቅዋም ነበር፡፡ ሂሩት ግን፥ ልብዋ ቆሞ የምታሰላስለው ደርቤን የምታጠምድበትን መንገድ ነበር፡፡

‹‹ቀላል ነው›› ብላ ፈገግ አለች፡፡

የሱካር፥ የጉበትና የኩላሊት መድሀኒት፥ «ግሩም የሆነ መድሀኒት አግኝቻለሁ። አንድ አርመን ነው የሰጠኝ። እስቲ ሞክረው» ሲል አንዱ፥ ሌላው ደግሞ፥ «የለም ጃል ምን ነካህ? ያለ ፋርማሲስት የሰጠን መድሀኒት ይሻላል» እየተባባሉ ኪኒኖችን እንደ ቆዛ ሲውጡ ላንዳፍታ ታዩት። እንደ ሀበሻ መድኃኒት እንደ ከረሜላ እየተቀባበለ የሚቅም ህዝብ ይኖር ይሆን? በማለት ሲገረም፥ ኤ. ቢ. ዋይልድ የተባለ ፈረንጅ እ.ኤ.አ. በ1880 ኢትዮጵያን በጎበኘበት ጊዜ፥ እንደ ኢትዮጵያውያን መድሀኒት የሚወድ ህዝብ አላየሁም. . .» በማለት በትዝብት ያሰፈረው ፅሁፍ ወለል ብሎ ታየው።

ዋይልድ ከመቃብሩ ተነስቶ ኢትዮጵያውያን መድሀኒት እንደ ከረሜላ እየተለዋወጡ ሲቅሙ ቢመለከት ምን ይል ይሆን? በማለት ረጂም የአሳብ ጉዞ ለመጀመር ሲያዘግም፥ መልካሙ አቋረጠውና፥ «ጋሼ ጌታቸው፥ ብር ሊወድቅብዎት ነው» ብሎ በጣቱ ጠቆመው። ብር ሳይሆን የሎተሪ ቲኬት ነበር።

«ስድሳ ሽህ ብር ልጥል ነበር ጃል!» አለው።

«ዛሬ ነው እኮ የሚወጣው» ሲለው፥ ጌታቸው የቲኬቱን ቁጥርና ሎተሪው የሚወጣበትን ቀን አገላብጦ ተመለከተና፥ «ልክ ነህ። የስድሳ ሽህ ብር ጌታ መሆን ነው ዛሬ!» አለው።

መልካሙ ጢጋ ብሎ በስንት መከራ ካዳመጠው በሁዋላ፥ «ከትናንት ጀምሮ እጄን ይበላኛል» አለና መዳፉን እከክ እከክ አድርጎ ሳመ።

«እከክ እንዳይሆን?»

«የለም እከክ አይደለም። ገንዘብ ላገኝ ስል ነው እጄን የሚበላኝ» አለና፥ ትናንሽ አይኖቹ በተስፋ አበሩ፥ «እኔም ለገብርኤል ተስዬ በእርሱ ስም አንድ ቲኬት ገዝቻለሁ» አለው።

ወዲያውኑ የቀበሌ ዲሞትፎር ተኩስ ሶስት ጊዜ አጉዋራ። ጌታቸው፥ «በለው!» አለና፥ «ለምን በራስህ ስም አልገዛህም?» ብሎ ጠየቀው።

መልካሙ በተኩሱ ደንግጦ አልሰማውም።

‹‹ምን አሉ?››

‹‹ለምን በገብርኤል ስም ገዛህ? ነው ያልኩህ፡፡››

‹‹ገብርኤል ያውቃል ብዬ ነዋ! መቶዋን ብር ለሱ ተስያለሁ፡፡››

‹‹አላሳነስክበትም? ከፍ ያለ ብር ለተሳለለት ሰው እድልህን አሳልፎ የሰጠብህስ እንደሆን?

‹‹ይድረሰኝ እንጂ ምን ከፍቶኝ፡፡ ጃንጥላም እጨምራለሁ. . .››

‹‹ስንጋም አክልበት፡፡ ገብርኤል ባነስተኛ ጨረታ አይገደድም. . .››

‹‹ሽረ በስመ አብ ይበሉ ጋሼ. . .››

‹‹በስመ አብ ብያለሁ፡፡ ግን ገብርኤል በስለት ተደልሎ አንድ ነገር ይሰጠናል ብለህ አትጠብቅ፡፡ ከንቱ ነው›› አለው፡፡

‹‹በስመ አብ ይበሉ፡፡››

‹‹ብያለሁ!›› ኢትዮጵያውያን ምድራዊ ባለስልጣኖችም ሆነ መላእክትን በጉቦ አባልገው የተመኙትን ለማግኘት ምን ያህል ጥረት እንደሚያደርጉ በአሳቡ ላንዳፍታ አጤነና ሲያበቃ፥ ውስኪውን ባንድ ትንፋሽ ጨልጦ፥ ‹‹መላእክት በጉቦ የሚደለሉ የአጥቢያ ዳኞች አይደሉም፡፡ ብትሳልም ባትሳልም የእድልህን አታጣም›› አለው፡፡

‹‹እግዜር አይሰጥም አይነሳም ነው የሚሉት?››

‹‹ላለ! አዎን›› ብሎ፥ ነገሩን እዚያው ላይ ለማቆም አስቦ ነበር፡፡

ነገር ግን፥ መልካሙ ቀጠለና፥ ‹‹ማንኛውም ነገር እግዜር ካልተጨመረበት አይሆንም›› አለና፥ ነገሩን በይበልጥ ለማብራራት አስቦ፥ ‹‹እይ ጋሼ ጌታቸው፥ አባቴና ጉዋደኛው፥ ፊታውራሪ ጉልላት ይባላሉ፥ አሁን እንኩዋን አቶ በሉኝ ብለዋል አሉ›› አለውና፥ ትዝ ብሎት፥ ‹‹ያውቋቸው የለም እንዴ? የጢቾ እንደራሴ በነበሩበት ጊዜ ከዚህ አይታጡም ነበር›› አለው፡፡

‹‹አዎን አውቀዋለሁ፡፡ ከማወቅም የእህቴ ባል ነው. . .››

የከፈቱት፣ ሁዋላ ቀር የሆነውን ህዝብ መፅሀፍ ቅዱስ አስታቅፈው ምድሩን ትቶ ወደ ሰማይ እንዲያንጋጥጥ ለማድረግ በቻሉበት ጊዜ ነው። ስለሆነም፣ አምላክ ይህን ያደርግልኛል፣ ያህን ይሰማኛል፣ ይነሳኛል፣ ይነፍገኛል የሚል አምላክ ይህን ያደርግልኛል፣ ... ነገር ከመካድ ይቆጠራል። ጭፍን አስተሳሰብ ሰብአዊነተትን ያህል ክቡር ነገር ከመካድ ይቆጠራል።

‹‹ታዲያማ ስድሳ ሺህ ብር ከደረሰዎት ወፈር ያለ ጉርሻ አይነፍጉኝም ብዬ ነዋ! እንደሚወጣልዎት ታይቶኛል. . .››

‹‹እንዴት ታየህ?››

‹‹ቁልጭ ብሎ ነዋ የታየኝ! ቲኬትዋ ከኪስዎ ብቅ ያለችው ያለ ምክንያት አይደለም። ብቅ ሲያደርጉዋት ጊዜና ደግሞ ልቤ የደነገጠው መደንገጥ እንዲህ አይምሰልዎት! ጋሼ ጌታቸው፥ ቢደርስዎት ስንት ይሰጡኛል?››

‹‹ሺህ ብር›› አለው፥ ሳያስብ።

‹‹እኔ ደግሞ ለስላሴዎች የአስር ብር ግምጃና ጡዋፍ።

ከጥይት ቤት አካባቢ የሽጉጥና የዲሞትፎር ተኩስ አይሎ መሰማት እንደጀመረ ሀብቴ ይርጉ፥ ጉደታ ፈይሳ፥ ታቦር ይመርና ኢዮብ ገብረማርያም ተንጋግተው ገቡ። የአራት ኪሎና የአቡነ ጴጥሮስ አንጋፋ ጋዜጠኞች ነበሩ።

ጌታቸው ሁኔታቸውን ትመስላላችሁሳ!›› አላቸው።

አራቱም የሚለውን ለመስማት ጆሮአቸውን ጠጋ አድርገው ነበር።

ታቦር አሳቡንና ምላሱን አስተባብሮ ለመናገር እየተቸገረ፥ ‹‹እኛን የሚገድለን አረቄ ነው፥ ጥይት ሲያልፍም አይነካን›› አለው።

ታቦር ሰውነቱ አልቆ፥ ስለታም ጠይም ፊቱ አመዱ ወጥቶ በየቦታው የተኮረኮመች ሰይቸንቶ መስሎ ነበር።

ጉደታ ፈይሳ በጌታቸው ውስኪ እየቀና፥ ‹‹እኔ ብሞት ለቀባሪ አላስቸግርም፤ በጋዜጣ ወረቀት ጠቅልላችሁ ቅበሩኝ›› አለ፥ መልከ መልካም ቀይ ፊቱን እያብረቀረቀ።

ጉደታ ፈይሳ እድሜው ገፋ ያለ ቢሆንም፥ የወጣትነት መንፈስ ይታይበታል። ራሱን ትልቅ ጋዜጠኛ አድርጎ የሚቆጥር በመሆኑ፥ ኢዮብ ገብረማርያም ሁልጊዜ ስለሚናደድ፥ ‹‹. . .በጋዜጣ ወረቀት የሚጠቀለለው እቃ ብቻ ነው። ጋዜጠኛ አይደለም›› አለው፥ ምላሱን እየገመደ።

«ብሩን ዘግቶ የሚውል የዴስክ ጋዜጠኛ እዚህ ውስጥ ምን አገባው? ህዝባዊ ጋዜጠኞች ይናገሩ!» አለውና፣ ከት ብሎ ሳቀ። ጉደታ ራሱ ተናግሮ ራሱ ይስቃል።

«ድንቄም ህዝባዊ ጋዜጠኛ!» አለው ኢዮብ።

ታቦር አይኑን እያቁለጨለጨ፣ «የለም እኮ! እንዴ፣ እንዴ! ጉደታ እኮ ለመቃብሩ የጋዜጣን ወረቀት የመረጠው የሬሳ ሳጥን ለመግዛት ስለማይችል ነው» አለ።

«የሬሳ ሳጥን ፍጆታ በዝቶ ምርቱ ስለ ቀነሰ ዋጋውም ንሮአል!» አለ ሀብቴ፣ ደረቅ ቀልዱን አክሎ።

«እሱም የዋጋ ቁጥጥር . . . እንዲደረግበት ያስፈልጋል። አለበለዚያ. . . መኖርም መሞትም ከአቅማችን በላይ ሊሆን ነው. . .»

«ለዚህ ነው እኮ፣ በጋዜጣ ወረቀት ጠቅልላችሁ ቅበሩኝ የምለው. . .»

ሀብቴ ወደ ላይ አንጋጦ ጣራ ጣራውን እየተመለከተና ቀይ ድዱን እያሳየ፣ «አትቸገሩ!» አለ። «እኔ የሬሳ ሳጥን በርካሽ የሚሸጥበት ሱቅ አይቻለሁ። በሩ ላይ ምን ተፅፎአል መሰላችሁ? ከፍ ብሎ በትልቁ «ቀይ ሽብር እናፋፍማለን» ይልና፣ ከስሩ ደግሞ፣ «በርካሽ ዋጋ የሬሳ ሳጥን ይገኛል» ይላል። ያለንግድ ሚኒስቴር ቁጥጥር ፍጆታንና ፍላጎትን ያስተካከለ ቤት. . . ለማንኛውም ነገር አዳው ገብስ ነው» ብሎ ወደ መልካሙ ዞረና፣ «ያንን መርዜን አቀብለኝ» አለው።

መልካሙ ቢራ አውርዶ ሰጠው።

ጉደታና ታቦር ተያዩ። ታቦር ወደ ኢዮብ እየተመለከተ፣ «ዛሬ የተወለድኩበት ቀን ነው አላልከንም ነበር እንዴ? አንተን ተማምነን ነው እኮ የመጣነው» አለው።

ደርግ ባወጣው መግለጫ የፍራንክ ቅጭልጭል በሚሰማበት ቦታ ሁሉ እየዞሩ በወሬ የሚነግዱትን ጋዜጠኞች በጥብቅ ካወገዘ ወዲህ፣ ታቦርና ጉደታ የሚተማመኑት በገዛ ኪሳቸው ሳይሆን በሌሎች ሰዎች ኪስ ሆኖአል። በፊት

ባለቤቱ ከእርሱም አልፋ በየውድቅቱ ከቤት እምጥተው በድኑን ጥለውላት የሚሄዱትንም የአረቄ ጉደኞቹን ጭምር፣ ‹‹እናንተ ናችሁ እንዲህ የምታደርጉት፣ አጫራሾች! የምትጠጡት የልጆቼንና የኔን ደም ነው!›› እያለች፣ አኩርፋና ገላምጣ በስድብ ስለምትሸኛቸው፣ ምላስዋን በመፍራት ወደ ኢዮብ ቤት ብቅ ማለት ከተወ ዘመን የለወም። እና፣ ይሄም እያበሳጨው ያስጠጣው ነበር - ጠዋት ማታ. . .

የቤተሰቡ ብዛት እየጨመረ ሲሄድ፣ መጀመሪያ ሁለት መኝታ ክፍል ያለው ቤት፣ ቀጥሎ ሶስት መኝታ ክፍል ያለው ቤት ሳይወድ በግድ እያስፈለገው፣ በፍላጎቱ መጠን የቤት ኪራይ እየጨመረበት፣ ኑሮው እየቆረቆዙ፣ ችግር ኪሱንና ጉዋዳውን እየዳበሰ፣ ችግሩ በልጆቹ ሰውነትና አለባበስ ላይ ከፉኛ እያንፀባረቀ፣ ደመወዙ በሞዴል ስድስት በቅድሚያ ተወስዶ እያለቀ፣ እድሉ በየወሩ መጨረሻ ላይ ደመወዝ መውሰድ ቀርቶ የደመወዝ መዝገብ መፈረም ብቻ እየሆነ፣ የጎረቤት ኪዮስክ ዱቤ እየተጫነው. . . በየእለቱ የሚፅፈውን ፅሁፍ በቤት ኪራይ ውድነትና በቤት አከራዮች ጭካኔ ላይ መመስረት ጀመረ። እንጨት ቆም ቆም - ማእዘን ሰካ ሰካ - ማገር መታ መታ - ጭቃ ለጠፍ ለጠፍ - ቀለም ቀባ ቀባ አድርገው ከሁለት መቶ እስከ ሁለት መቶ ሃምሳ ብር የወር ኪራይ መጠየቅ በወገን ላይ ይቅርታ የሌለው በደል መፈፀም ነው፣ እያለ ነጋ ጠባ ቢፅፍም ሰሚ አላገኘም። የቤት ኪራይ እየተወደደ ኢዮብም ርካሽ ቤት ፍለጋ ከተማ ዳር እየወጣ - በደብረ ዘይት መንገድ - በነፋስ ስልክ - በአስመራ መንገድ ኮላም በረት - በጉጃም መንገድ ከመርሀ ቤቴ ሆቴል አልፎ በመከራየት እየተንከራተተ ኑሮው እያዘቀጠ እንደ መሄዱ መጠን፣ በየጊዜው የሚፅፋቸውም ፅሁፎች በቁጭትና በንዴት፣ ተስፋ በመቁረጥና በብስጭት እየተሞሉ ሄዱ። በዚህን ጊዜ ነበር በጊዜው የነበሩት ባለስልጣኖች አደገና ኮሙኒስት ነው ብለው በማመን አላፊነት በሚጠይቅ ስራ ላይ እንዳይቀመጥ ያደረጉት።

እንዲሁም መጠጥ ቤቶች እየበዙ እንዳይሄዱ ቁጥጥር እንዲደረግ፣ መጠጥ ቤቶች ለህዝብ ክፍት የሚሆኑበት ሰአት እንዲወሰን ወጣቶች እንደ ልባቸው መጠጥ ቤት ዘው ብለው እንዳይገቡ እድሜያቸውን የሚያመለክት የመታወቂያ ካርድ እንዲይዙ ህግ እንዲወጣ፣ ከአገር ቤት ኮረዳዎችን

‹‹የምን ልጆች?››

‹‹ጥዋት ትምህርት ቤት እንደሄዱ አልተመለሱም። ወይኔ ልጆቼ! ምነው አፈር በበላሁት!››

ከጥቂት መጬዋጬዋህ በሁዋላ ነበር ጉዋደኞቼ እንደ ምንም አስታግሰዋት ሲያበቁ፥ የሚማሩበትን ትምህርት ቤት እንድትነግራቸውና ሄደው ልጆቹን ለማምጣት የተስማሙት።

ከአንድ ሰአት በሁዋላ በብርድ የተቆራመዱ፥ በረሃብ የተቆሉ፥ ከንፈሮቻቸው እንደ ከብት የደረቁ፥ በፍርሃት የተዋጡ፥ የደነገጡ፥ የሚንቀጠቀጡ፥ ህፃናት ልጆች እጅ ለእጅ ተያይዘው እንዳመሹት ሁሉ፥ እጅ ለእጅ ተያይዘው የገቡት። ከፍርሃታቸው የተነሳ እናታቸውን እስኪያዩ ድረስ አልተላቀቁም። እናትዬውም እንደዚያ በፍርሃት ተውጠውና ተርበው እጅ ለእጅ ተያይዘው በተመለከተቻቸው ጊዜ እንባዋ ባንዳፍታ ደረቀ። ‹‹ምትን እናት ሆንኩት? አፈር ይብላኝ። የማርያም ልጅ የተሰቀለው በሰው እጅ በመሆኑ እናቱ አልሸሸችም። መስቀሉ ስር ተንበርክካ አለቀሰች። እኔ ግን እያየሁ በገዛ እጄ ልጆቼን ከችግር መስቀል ላይ አልሰቅላቸውም። እኔ ብሰቀል ይሻላል ብላ እንደ ወትሮዋ ሳትስማቸው ውልቅ አለች። ጭለማ ከንፉን ዘርግቶ ጋረዳት. . .

የኢዮብ የስራ ጉዋደኞች በስካሩ እየተገረሙና እንደ ጥፐ ቦጭቀው እያሙት፥ ብርዱን እያማረሩ፥ ልጆቹን ከትምህርት ቤት - ከዘበኛ ቤት ውስጥ - አውጥተው ቤት ለማድረስ ስላጠፉት ጊዜ እየተቆጩ ወደ አቅራቢያው መጠጥ ቤት ተመለሱ። ከኢዮብ የባሱ ጠጪዎችና ሃላፊነት የማይሰማቸው ከመሃከላቸው ጠፍተው - እህቶቻቸው - ወንድሞቻቸው - እናቶቻቸው - ዘመድም ባይኖር ገረዶቻቸው ዘወትር እንቅልፍ አጥተው እየባነኑ የሚጠብቁዋቸው ይገኙ ነበር። አንዳንዶቹ፥ በተለይም እየሰከሩ ገብተው ሚስቶቻቸውን በመደብደብና በመሳሪያ በማስፈራራት ከቤት ያስወጡና ወጥተውም ስራ እንዳይዙ በማስፈራራት ከአገር ያባረሩ፥ ሌሎች ደግሞ ሰክረው ገብተው ሲጃራ አቀጣጥለው በመተኛት ተከራይተው የሚኖሩባቸውን ቤቶች በእሳት በማጋየት እዳ የሚገፈግፉ፥ ሌላው ደግሞ ከስካሩ የተነሳ ሁለት

አዳዲስ መኪናዎች ፈፅሞ ከጥቅም ውጭ ያደረገና ዳግመኛ መሪ ላለመጨበጥ እርም ብሎ የተወ - በያይነቱ ነበሩባቸው. . .

ጉዋደኞቹ አስተኝተውት ከሄዱ በግምት ከሁለት ሰአት በሁዋላ ኢዮብ ነቃ። ቤቱ ባዶ ነበር። እረጭ ብሎአል። በቀሉት አይኖቹ ክፍሉን አማተረ። ልጆቹ እጅ ለእጅ እንደ ተያያዙ ከሶፋው ላይ ኩርምት ብለው ተኝተዋል። አስታወሰ. . .

ክፍሎቹን ሁሉ አዳረሰ። ማንም አልነበረም። አወቀ። ወደ ጉዋዳ ዘው ብሎ ቢላዋ አነሳ። ወደ መኝታ ቤት ሄደ። ወደ ውስጥ በረጂሙ ተንፍሶ አይኖቹን ከደነ፣ ‹‹እማምዬ ራበኝ!›› የመጨረሻ ልጁ ድምፅ ነበር። ቢላዋውን ጣለው። እና ዳግመኛ ላለመጠጣት ማለ. . .

ኢዮብ በአሳብ ጭልጥ ብሎ መሄዱን አጤነና፣ ‹‹ምን ሆነሃል?›› ብሎ ጠየቀው ጌታቸው።

ኢዮብ እንደ መባነን ብሎ፣ ‹‹ሆሆሆ . . . ስላሳለፍኩት ከንቱ ሃምሳ አመት ነበር የማስበው። ህይወት አጭር መሆንዋን ብዙ ከመኖር የተረዳሁ መሰለኝ›› አለው።

‹‹እዎን፣ በተለይ ህይወት በዚህ ሰሞን አጭር እየሆነች ሄዳለች!›› አለው ጌታቸው፣ ውጭ የሚጠፋውን ተኩስ እያዳመጠ።

‹‹ላጭር ህይወት!›› አለና፣ ኢዮብ ሻይውን አነሳ። ቀጠለና፣ ‹‹የተወለድኩበትን ከንቱ ቀን ለማክበር ነው የመጣሁ›› አለው።

ጌታቸው ሲያስብ ቆየና፣ ‹‹የከንቱም ከንቱ። የኛ ህይወት በየእለቱ እንደምናዘጋጀው ዜና ነው። ሲያልፍ ወዲያውኑ ይረሳል - እንደ ትናንቱ ዜና›› አለና፣ ወደ ሀብቱ መለስ ብሎ፣ ‹‹ዛሬ ምን ወሬ አለ?›› ብሎ ጠየቀው።

‹‹ሰው ውሻ አልነከሰም። ከብርሃንና ሰላም ፎቅ ተወርውሮ ራሱን የገደለ ካቡኑ ጴጥሮስ ሀውልት ጋር የተጋጨ፣ የልጃገረድ ክብር በግድ የደፈረ የለም። የወሬ ድርቅ ሆኖአል!›› አለው፣ ወደ ላይ አንጋጦ ቀይ ድዱን እያሳየ።

‹‹አይ የቡርዥዋ ጋዜጠኛ አመለካከት! ይኽ ሁሉ የቀበሌ ተኩስ፥ ተልባ ሲቆላ ነው በለኛ! በምስራቅ፥ በደቡብ፥ በሰሜን የሚካሄደውስ ጦርነት?›› አለው።

‹‹ኦ. . . እሱ የመደብ ጦርነት ነው. . .››

ሀብቴ፥ ይርጉ የሚቀልድ መሆኑን ቢያውቅም፥ ‹‹የመደብ ጦርነት ወሬ አይሆንም ያለህ ማነው?›› አለው።

‹‹የለም፥ መራራ ትግል ነው ማለቴ ነው። መራራ ትግል ፕሮፓጋንዳና ቅስቀሳ ነው የሚያስፈልገው። ትግል ነው የሚያስፈልገው፥ ወሬ አይደለም። ገባህ? በቃ፥ ፖለቲካ አታናግረኝ፤ እኔ እኮ የምትከተለውን መስመር አላውቅም!›› ብሎ፥ ለመዝፈን እየቃጣው፥ ‹‹ባሉባልታ ወሬ መነገድ. . . በውሸት ተነስቶ መቀደድ፥ እንደ ጣቃ መቀርደድ፥ በሰፊው ህዝብ መቀለድ፥ ወሬውን ወዛ ወዛ ቀባ ቀባ ማድረግ፥ በጋዜጣ ላይ መባለግ፥ በቲቪ መረግረግ - አክትሞአል!›› አለ።

ጉደታ፥ በሀብቴ ደረቅ ቀልድ እንደ መብሸቅ ብሎ፥ ‹‹ቁም ነገሩ ያለው አመለካከታችንን ከመለወጥ ላይ ነው›› አለ። ‹‹ህዝባዊ ጋዜጠኞች ብንሆን ኖሮ ይህ ሁሉ የመደብ ትግል እየጦፈ ስለወሬ ድርቅ አናወራም ነበር! የህዝቡን አስተሳሰብ መምራት ሲኖርብን ጅራት ሆነን ቀርተናል!››

‹‹ማን ከለከለህ ታዲያ!›› አለው ጌታቸው፥ ብሽቅ ብሎ።

ታቦር ነፃ ውስኪውን ጨለጠና፥ ‹‹እንዴ፥ እንዴ፥ የመደብ ልጓም እየሳበው ነው!›› አለ።

‹‹. . . አመለካከት. . . ምናምን. . . እንደ ሸሚዝ የሚለውጥ አይደለም። . . አመለካከት ከእምነት ተነጥሎ ሲታይ አይችልም። እኔ የሚገርመኝ የብዙ ሰዎች እምነት እንደ ላስቲክ ለመሳብና ለማጠር መቻሉ ነው። አድርባይነት በዝቶአል!›› አለ ኢዮብ፥ ወደ ጉደታ እየተመለከተ።

‹‹የጊዜው በሽታ ነው!›› አለ ጌታቸው፥ ባሳቡ የደርቤን በድንገት መለወጥ አስታውሶ።

ሀብተ ወልድ፥ ከራጉኤል ደብተራዎች ሌላ ጋዜጠኛ የለም ብለው የሚያምኑ ቢሆኑም፥ ጌታቸው ባጭር ጊዜ ውስጥ ስራውን ተለማምዶ ባሳየው ችሎታና ብልህነት በመገረም፥ ጋዜጠኛንና ሰላይን ለይተው አይመለከቱም ነበርና፥ ለሁለቱም ስራ ያስጠጉት ጀመር። መኮንን ሀብተ ወልድን የሚያህል፥ አድራጊ ፈጣሪ፥ ፈላጭ ቆራጭ ባለኝው ሚኒስቴር መስሪያ ቤት ገብቶ የሚያዝ ሰው መጠጋቱ ባልከፋም ነበር። ግን፥ ለምን ሊያስጠጉት እንደ ፈለጉ በትክክል ባወቀ ጊዜ ነበር አዘውትሮ የመለኪያ አንገት መጨበጥ የጀመረው። እንደ እድል ሆኖ ብዙም አልቆየም። ነፃ የትምህርት እድል አግኝቶ ወደ አሜሪካ ሄደ። ሆኖም፥ ከመኮንን ሀብተ ወልድ ቢገላገልም፥ በእሳቸውና በእህቱ ምክንያት የተጠናወተው የጋዜጠኛነት ሙያ እንደዛር አድርቦት ቀረ።

«አቶ ጌታቸው ያልከው እውነት ነው። አሁንም ቢሆን የራሳችን ጠላት እኛው ራሳችን ነን» አለ ታቦር። አሳቡ ከምላሱ ስለሚቀድም አፉን መክፈት አቅቶት ሲጨነቅ ሌላውንም ያስጨንቃል።

«እንዴት?»

«አዎን፥ ማለቴ፥መደብ ከልጉዋም ይስባል ይባል የለ? የንኡስ ከበርቴ ባህርያችን ነው ጠላታችን።»

«ምን ለማለት ፈልገህ ነው?» አለው ጌታቸው፥ ቆጣ ብሎ።

«እኔ የምለው፥ አዎን፥ የማይቋዋቋዋሙትን ሃይል ከመጋፈጥ አብሮ መሰለፍ ይሻላል ለማለት ነው. . . ማለቴ፥ ዛሬ አንድ ወሬ ሰምቻለሁ።»

ታቦር ወሬ እንደማያመልጠው ያውቃልና ጉደታ ተጣድፎ፥ «ምን ወሬ ሰማህ?» ብሎ ጠየቀው።

«ከማስታወቂያ ሚኒስቴር አርባ ሰዎች ሊጋለጡ ነው እየተባለ በሰፊው ይወራል። እንደ ሰማሁት ከሆነ ሁላችንም አለንበት። ቅድም እንዳልኩ የራሳችን ጠላት እኛው ራሳችን ነን። ንቀቱን ትተን ከሰፊው ሰራተኛ ጋር በውይይት ክበቦች ውስጥ ብንካፈል ኖሮ ይህ ሁሉ አይደርስብንም ነበር። ከሰፊው ሰራተኛ ጋር ሆድና ጀርባ ሆነን የቀረነው በገዛ እጃችን ነው. . . ለራሳችንም ባይሆን፥ ብንካፈል እኮ ሰፊው ሰራተኛ በአንዳንድ ጥቅም አሳዳጅ

ትንፋሽ ጨለጠና፥ ‹‹ይሄ ደርቤ የሚሉት ሰው እኮ አብዮአል፤ ዳሩ ይህ አብዮት ያላሳበደው የመስሪያ ቤታችን ሰው ማን አለና›› ብሎ፥ ሌላ ውስኪ አዘዘ። በደርቤ መለወጥ እየተገረመ የአባቱን ሞት ሊበቀል ይሆናል፥ በቂም በቀል የሚያምን ሰው አደገኛ ነው ብሎ አሰበ።

መልካሙ መዳፉን አከከና ሳም ሳም አድርጎ ሌላ ውስኪ ቀዳለት። ለተቀሩትም ደገመ።

ጌታቸው ቀጠለና፥ ‹‹ውይይት ክበብ መግባት በግድ መሆን የለበትም። እኔ አልንበረከክም። እነዚህን እናጋልጣለን ብለው የተነሱትን አፈ ጮሌዎች አንድ በአንድ ነው የምሰራላቸው፤ አይነጋ መስሎአት በቁዋት አራች ነው!›› አላቸው።

‹‹ለአለቆቻችን ሁሉ ያንተን ልብ ቢሰጣቸው ምን ነበረበት!›› አለው ጉደታ።

‹‹ልብ የላቸውም!›› አለና ጌታቸው፥ ‹‹ያዙኝ ልቀቁኝ የሚለው ሁሉ ለአብዮቱ ሲል አይምሰልህ። ለጥቅሙ ሲል ነው። ዛሬ በአብዮት ስም ተጠቅልሎ የማይቀርብ የመርዝ አይነት የለም። ድዱን ሲመቱት ሹልክ ብሎ መጥቶ እግር ላይ ይወድቃል! አይምሰላችሁ!›› አለ ጌታቸው፥ ልቡን መታ መታ እያደረገ።

ሀብቴ ቀይ ድዱን እያሳየ፥ ‹‹እኔ የለሁበትም። ስልጣን ለሰፊው ህዝብ! አውሎ ንፋስ ሲመጣ ብልሃቱ ማጎንበስ ነው›› አለ።

‹‹አይ አቶ ጌታቸው! አንተ ኮ እልኸኛ ነህ። ድባቅ ሳትመታ አትመለስም!›› አለው ጉደታ።

ጉደታ መቼም ጥሉበት ሰውን መሸንገል ይወዳል። ከተመቸውም ሌላውን መሳሪያ ከማድረግ ወደ ሁዋላ አይልም። ጌታቸውም በበኩሉ ሽንገላ አይጠላም። ስለሆነም፥ አሜን፥ አሜን የሚሉትን ሲያስጠጋ፥ አሳቡን የሚቃወሙትን ደግሞ ተከታትሎ ከማጥፋት ወደ ሁዋላ የማይል ቂመኛ ነበር። ሆኖም፥ ለሚያስጠጋቸውም ሰዎች የሚያሳየው ፍቅርና አክብሮት ዘላቂ አልነበረም። እንደ ትኩስ ድንች ነበር ሰዎችን አንስቶ የሚጥላቸው። ታዲያ፥

ጉደታ የያንዳንዱን ሰው ድክመት የማወቅ ተሰጥዎ ነበረውና፥ ጌታቸውን ባገኘው ቁጥር ሳይሸነግለው አያልፍም።

ጌታቸው ሲያስብ ቆየና፥ ‹‹አንተምኮ ሪፖርተሮች ቤታቸው ከመሄዳቸው በፊት እጅ ነስተውኝ ካልወጡ እያልክ ትቆጣ ነበር›› አለው ጉደታን።

‹‹ዛሬ አያበላም›› አለ ሀብቴ።

‹‹እሱ. . . ሆሆሆ. . . በሰላም ጡረታ እንዳይወጣ. . .›› አለ ኢዮብ። ‹‹መምሪያ ሃላፊዎቻችን. . እገሌ አድሃሪ ነው፥ ሰካራም ነው፥ ስራ አይገባም. ማይ ፉት. . ዘ ፓት ኮሊንግ ዘ ኬትል ብላክ. . . እያሉ ጡረታ ሊያወጡን ነው ሲሉ ሰማሁ። በስንት በኩል እንጠቃ? እኔ ግን አብዮቱ ለኛም ጭምር የመጣ መስሎኝ ነበር።››

‹‹አብዮቱ የመጣው ለጭቁኖች ነው!›› አለ ሀብቴ።

‹‹እኛ ምንድን ነን?››

‹‹ምንም አይደለንም። መደብ እንኳን የለንም። አቅዋምም የለንም›› አለው ሀብቴ።

‹‹ጌታቸው ነገሩ ከነከነውና፥ ‹‹አቅዋም ካልተወሰደ አገር መኖር አይቻልም ያለህ ማን ነው?›› አለ። ‹‹አየህ፥ የሰፊውን ህዝብ ጥቅም አምኖ መቀበል አንዱ ራሱን የቻለ አቅዋም ነው። ነገር ግን ባንድ አዳር ሁሉም ኮሙኒስት መሆን አይችልም። የኮሙኒስት ፓርቲ ደግሞ በጥራት ነው እንጂ በብዛት አያምንም። እኔ የማዝነው ትናንት እልም ያሉ ነፍጠኛ፥ የዘርና የሃይማኖት ትምክህተኛ የነበሩ አንዳንድ ግለሰቦች ዛሬ ኮሙኒስት ነን እያሉ ሲደነፉ ሳይ ነው። ይህን ሳይ ኢትዮጵያዊነቴ ያስጠላኛል፥ ያመኛል፥ ያቅለሸልሸኛል።››

‹‹አየህ፥ አቅዋም የዝምድናና የጉዋደኛነት ሀረግ ስቦ እንዲሁ በቀላሉ የሚወሰድ ጉዳይ አይደለም። የማሌ ድርጅት አባል ለመሆን አስቀድሞ ሀቀኛ ኮሙኒስት መሆን ያስፈልጋል። ኮሙኒስት ለመሆን ደግሞ ከቁስ አካላዊ ርእዮተ አለም ውጭ ያለውን እምነት ሁሉ እንደ እርጌ ቁና አውጥቶ መጣል የመጀመሪያ ተግባር ነው። መፅሀፍ ቅዱን ስይጣንም ሊጠቅስ ይችላል። የማርክስና የሌኒን መፅሀፍ የጠቀሰ ሁሉ ኮሙኒስት አይደለም። ለማንኛውም

ነገር አወናባጅ ሁሉ እርቃኑን ወጥቶ የሚታይበት ጊዜ ሩቅ አይደለም። እኛ በውዥንብር ውስጥ እንጠፋ ይሆናል። ግን ጊዜው ይደርሳል።ምናለ በሉኝ!››

ከስላሴ አካባቢ የተኩስ ዶፍ ሲወርድ ይሰማ ነበር።

‹‹ተኩሱ እየቀረበ መጣ. . . እንሂድ መሰለኝ›› አለ ኢዮብ።

መሄዱን ወዶ አልነበረም እንሂድ ያለው። ከቤቱ የበለጠ የሚጠላው ነገር አልነበረም። ለምሳና ለእራት የተጎሳቆሉ ህጻናት ፊት ማየት አስጠልቶታል። ለመሄድ የቸኮለው ጉደታና ታቦር በሱ ኪሳራ መጠጥ መደጋገማቸውን በማየቱ ነበር።

‹‹እኔስ እቆያለሁ። ከጥይቱ ይልቅ እኔን የሚያስፈራኝ ያ አፉን ከፍቶ የሚጠብቀኝ ባዶ ቤቱ ነው›› አለ ሀብቴ።

ጌታቸው፥ ‹‹አዎን፥ ሞት ቦታ መርጦ አይመጣም። የመስኪያ ወገብ እንደ ጨበጡ፥ ወይም በመንገድ እየሄዱ በድንገት መሞት ይሻላል?›› ከማለቱ፥ እሜቴ - የቡና ቤቱ ባለቤት - ነጠላቸውን ከትከሻቸው ላይ ጣል አድርገው ደብረክ ደብረክ እያሉ ገቡ።

‹‹አዬ ጉድ፥ ከደንበኞቼ ሁሉ እናንተው ብቻ ቀራችሁ?›› አሉ፥ ማን ገንዘብ ከፍሎ ማን በዱቤ ለመጠጣት እንደ መጣ በልባቸው እያሰቡ።

‹‹አይዞሽ፥ ሞት ነው የሚለየን›› አላቸው፥ ጌታቸው።

‹‹ጠላትህ ይሙት!›› አሉትና፥ ወደ ሀብቴ ዘወር ብለው፥ ‹‹ማታ በህልሜ ጥጥ የመሰለ ጮማ እየቆረጥኩ ሳጎርስህ አየሁ ልጄ። ህልሜ መሬት ጠብ አይልም። ሲሳይ ነው።፡››

እየተንገፈገፈ፥ ‹‹ዋጥኩት ታዲያ?›› አለ። የምግብ ነገር ሲነሳ ያንገፈግፈዋል። ሲበላ ያልበዋል። ምግብ የሚጋብዘውን ሰው እንደጠላቱ ነበር የሚቆጥረው።

‹‹እንክት አድርገህ!›› አሉትና፥ ወደ ታቦር መለስ ብለው፥ ‹‹ዛሬ ፊትህ ፈካ ብሎአል›› አሉት።

እሜቴ የሁሉንም ቲኬት ተመለከቱና፣ «እኔ ህልም ያየሁት ለሀብቴ ነው። ያገኘ እንደሆን እንድረዋለን» አሉ።

የእህል ስም ሲያነሱበት ላብ ላብ እንደሚለው ሁሉ፣ የሚስት ነገርም ሲያነሱበት አይወድም። ሴቶችን የሚፈራው ከሩቅ ነበር። ሴቶች ሲጠጉት የሚያደርገውና የሚናገረው ነገር ስለሚጠፋው ይርበተበታል። ሆኖም በደረሰበት ሁሉ ሚስት ፈልጉልኝ እያለ የወጣትነት እድሜውን ወደ መጨረሱ ገደማ ነበር።

ጉደታ፣ «እሱ'ኮ ያ ነገር አይሰራለትም» አለና፣ ከት ብሎ ሳቀ።

እሜቴ፣ «እኔ ለሀብቴ ነው ህልም ያየሁት» ሲሉ ሰምቶ ፊቱ ልውጥ አለ። የልጃገረድ ሳዱላ የመሰለችውን ከሁዋላ ያለችውን መላጣውን እከክ እያደረገ፣ «የእኔ እድል ሁልጊዜ ለምን ለሀብቴ ይሆናል?» አለ በአሳቡ. .

. . . ከጥቂት ዓመታት በፊት እርሱ ተፃፅፎ ባገኘው የነፃ ትምህርት እድል እንዲጠቀም የተደረገው ሀብቴ ይርጉ ነበር። መቼም ለባለስልጣኖች ማጎብጎብና ማጎንበስ አይሆንለትምና ታቦር እንባውን አፍስሶ ዝም አለ። እንባው በከንቱ ፈስሶ አልቀረም። ከጥቂት ጊዜ በሁዋላ ሌላ ነፃ ትምህርት እድል አግኝቶ ወደ አሜሪካ ሄደ። ሁለቱም የጋዜጠኛነት ትምህርታቸውን ፈፅመው ሲመለሱ ለአንድ ጋዜጣ አዘጋጅነት የተመረጠው ሀብቴ ስለነበረ ለጥቂት ወራት አለቃና ጭፍራ ሆነው ሰሩ። ያኔ ነበር ታቦር ወሽመጡ የተቆረጠው። ያኔ ነበር በጊዜ ከስራ ገበታው ላይ መገኘቱን ትቶ በግድ የለሽነት መተኛት ያመጣው። ያኔ ነበር ከወደ ውሃው ጨመር እያደረገ መወሳሰድ የጀመረው። የደረሰበትን የብስጭት ስሜት የተረዳለት ግን አልነበረም። ሃላፊነትን መሸከም አይችልም፣ ጠጪ ነው፣ የበላዮቹን ትእዛዝ ሆነ ምክር አይቀበልም፣ በሚል ሰበብ ይባስ ብሎ እድገት እየታለፈው ሄደ፣ እርሱም በሃይል እየተበሳጨ፦

«እና፣ ህልምሽ ቅዠት ነው» አላቸው፣ እሜቴን።

እሜቴ፣ «የኔ ህልም ከመሬት ጠብ አይልም» እንዳሉ፣ ሁለት ሰዎች ተከታትለው ገቡ። ሁለቱም ሞቅ ብሎአቸዋል። ለቤቱ እንግዳ አልነበሩም። የእሜቴ ቡና ቤት ደንበኞች ነበሩ።

አለመግባባትና በግል በሚያካሂደው ድርጅት ላይ በየጊዜው እየደረሰ የሚሄደው ኪሳራ ነበር። ደምሮ፥ ቀንሶ፥ ብቻውን ከራሱ ጋር አውርቶ ሲያበቃ ቀጥሎ የሚናገረውን ጋዜጠኞቹ አስቀድመው ስለሚያውቁት ተያይተው ይጠብቁት ነበር።

‹‹እዩ የኛ ጋዜጠኞች›› አለ። ‹‹ድንቄም ጋዜጠኛ! ትርኪ ምርኪውን ከምታወሩ ስለ ስራ ዲሲፕሊን ለምን አታስተምሩም? ሰውን ሰው ያደረገው ስራ ነው ሲባል አልሰማችሁም? ዳሩ የት ታውቁትና!››

‹‹እንጂኔር፥ ምን ጎደለ ነው የምትለው!›› አለው ጉደታ።

‹‹ምን አሙዋልታችሁ ስርታችሁ ታውቃላችሁና? ወዛደሩ ንቃት እያለ ስራ ሲፈታ - ዝም! በስድስት ወር ውስጥ መጠናቀቅ ያለበት ስራ ሁለት አመት ሲፈጅ - ዝም! ስራው በተፈለገው ጊዜ ሳይጠናቀቅ ቀርቶ ተቁዋራጭ አሻጥር ፈፀመ ተብሎ ሲወነጀል– ዝም! የናንተ ድንፋታ የመለኪያ አንገት ስትጨብጡ ብቻ ነው!

‹‹እኔስ ግድ የለኝም። ስራዬን ዘግቼ አርፈዋለሁ። እርፍ! በቃ! ምን አዳረቀኝ! ከሙብት ሌላ ግዴታ ምን መሆኑን ከማያውቅ ሰራተኛ ጋር ለምን አዳረቃለሁ? ቆሽቴ ለምን ይድበን? ታዲያ እናንተ ጋዜጠኞች ናችሁ ለዚህ ሁሉ ተጠያቂዎች. . .

‹‹እህህ!›› አሉ፥ ባሻ ትርፌ።

በቦታው የሉም - ባሻ ትርፌ። በህልም አለም ውስጥ የሚንሳፈፉ ይመስላሉ። ያሉበት ሁኔታ መጥፎ ቀልድ ነበር መስሎ የሚታያቸው። ለእሳቸው ሁኔታው ሁሉ ደብዛው የጠፋ አሉባልታ ሆኖ ነበር የሚታያቸው። በቦታው የሉም. .

እንጂኔር ረታ ቀጠለ፦

‹‹ወዛደሩ ሙብትና ግዴታን ለይቶ እንዲያውቅ አታስተምሩም። ሙብት! ሙብት! ሙብት ብቻ። ሙብት ያለ ግዴታ ትርጉም የለውም። እናንተ ጋዜጠኞች ናችሁ አገር ያጠፋችሁት። ድራሻችሁ ይጥፋና! ዳሩ ከናንተ ምን

ይጠበቃል! ሙያችሁ የሚጠይቀው ምግባር ምን እንደሆነ፣ በእጃችሁ ያለው መሳሪያ ምን ሃይል እንዳለው የማታውቁ የእብድ ገላጋዮች ናችሁ. . .

‹‹እህህ!›› አሉ ባሻ ትርፌ፡፡

እንጂኔር ረታ ቀጠለ፡-

‹‹እኔስ ግድ የለኝም፡፡ ስራዬን ዘግቼ አርፌዋለሁ፡፡ ቆሽቴ እንደ ደበነ አይቀርም፡፡ እኩልነት ሲባል ሁሉንም ዜሮ ማድረግ ነው እንዴ? አይደለም! እኩልነት መልክ መልክ አለው፡፡ ‹‹የተካበተ ስራ›› የሚለውን የማርክስን እኩልነት መልክ መልክ አለው፡፡ ‹‹የተካበተ ስራ›› የሚለውን የማርክስን ቲዎሪ ታውቃላችሁ? አይመስለኝም፡፡ እያችሁ፣ ትምህርት፣ ልዩ ሙያ፣ ቲዎሪ ታውቃላችሁ? አይመስለኝም፡፡ አያችሁ፣ ትምህርት፣ ልዩ ሙያ፣ የተካበተ ስራ ስለ ሆነ፣ ትምህርትና ልዩ ሙያ ያላቸው ሰዎች የተሻለ ደመወዝ ይከፈላሉ፡፡ የሶሻሊዝም አላማ በእኩልነት ስም ሁሉንም ዜሮ ማድረግ ሳይሆን፣ ከእያንዳንዱ እንደ ችሎታው ለእያንዳንዱ እንደ ስራው በሚል መርህ መሠረት፣ የህዝቡን ኑሮ ከፍ ማድረግ ነው፡፡ አይ የኛ ጋዜጠኞች! ይህን ይህን ብታስተምሩ ታውቁትና!. . .

‹‹እህህ›› አሉ፣ ባሻ ትርፌ፡፡

ጌታቸው አቀማመጡን ለወጠ፡፡ ጋዜጠኞቹ ተጠቃቀሱ፡፡

‹‹ዲስኩሩን አቁመህ ውስኪ ብትጋብዘን ጥሩ ነበር›› አለ፣ ጉደታ፡፡

እንጂኔር ረታ ቀጠለ፡-

‹‹ለምን አፈር አትጠጡም፡፡ የምትፅፉት ጋዜጣ አረቄ አረቄ ነው የሚሸተው፡፡ ‹‹ውዥንብር›› የሚሉት ቃል ጥሩ ቃል ነው፡፡ እናንተ የውዥንብር ኤክስፐርቶች ናችሁ፡፡ ለማንኛውም ነገር፣ ይቅርታ አድርጉልኝ፡፡ መናገር አልነበረብኝም፡፡ መናገር ምን ያደርጋል? ስራዬን ዘግቼ እርፍ! ቢቃ! ብሎ ለስራ አስኪያጆች፡፡ ሃላፊነትን አሸክሞ ዲሲፕሊን ማስከበር ለማይችለው ስራ አስኪያጅ ይብላኝልን! መጥኔውን ይስጣቸው›› አለና፣ መጠጡን እንደቶ ጨለጠ፡፡››

‹‹በጊዜያችን፥ ትግል የህይወታችን ዋነኛው ጉዳይ ነው። መለማመድ ያለብን አይመስልህም? አለም አንድ ቦታ የቆመች አይደለችም። ለውጥ የተፈጥሮ ህግ ነው። ችግሩ የኛ አሳብ አለመለወጥ ነው›› አለው፥ ጌታቸው።

‹‹ተወው እባክህ! በኛ ላይ የማይበረታ የለም!›› አለ ታቦር።

‹‹የወዛደሩ ትርፍ ንቃት ነው። አንተ የምታስበው ብርሀን ብቻ ነው። ወዛደሩ ያሸንፋል!›› አለ ሀብቴ።

‹‹አይ ጉድ! ከስሬ ስዘጋ ንቃት የት እንደሚያደርስ እናያለና!›› ከማለቱ፥ ተከዘው ‹‹እህህ›› ሲሉ የቆዩት ባሻ ትርፌ ከተቀመጡበት በድንገት ብድግ ብለው፥ የተለመደውን ሙሾአቸውን ማውረድ ጀመሩ።

‹‹ዋይ - ዋይ - ባላባት ዋይ - ዋይ! . . . ተቀበሉኝ እንጂ!›› ብለው፥ እሜቴን ነጠላ ነጥቀው ካሸረጡ በሁዋላ ‹‹በሞቴ ተቀበሉኝ!›› ብለው ‹‹ዋይ - ዪ ባላባት ዋይ -›› ደረታቸውን መደለቅ ጀመሩ።

‹‹ከእንግዲህ ቀረ ሳይሰሩ መብላት!››

‹‹ዋይ - ዋይ!››

‹‹የኪራይ ቤት።››

‹‹ዋይ - ወይ!››

‹‹ይህች አለም።››

‹‹ዋይ - ዋይ!››

‹‹አዱኛ።››

‹‹ዋይ - ዋይ!››

‹‹ወላዋይ።››

‹‹ዋይ - ዋይ!››

‹‹ዋዬ! ዋዬ! ዋዬ! ዋዬ!›› ብለው ሙሾውን በማቆም፥ ‹‹እህህ›› ካሉ ኋ፥ ስቅስቅ ብለው ማልቀስ ጀመሩ - እንደ ልማዳቸው።

የሎተሪውን ወሬ ለመስማት መልካሙ ቸኩሎ ሬዲዮ ከፍቶ ነበር፤ የምሽቱ ዜና መተላለፍ ጀመረ፡፡ ሁሉም ጆሮአቸውን ከሬዲዮው ላይ ተክለው ያዳምጡ ጀመር፡፡ መግለጫ ወይም አዋጅ፣ የተያዙ፣ የሞቱ፣ የቆሰሉ. . . የሚማርክ ምንም ወሬ አልነበረም፡፡

የሬዲዮ አንባቢ በመጨረሻ ‹‹የሎተሪ እጣ›› ሲል ሁሉም በደብልጥ ጆሮአቸውን አነቁ፡፡ እጣ ያላቸውን ቲኬቶች ቁጥሮች ሁለት ሁለት ጊዜ እየደጋገመ አነበበ፡፡ በመጀመሪያ ቲኬቱን ቀዶ ከወለሉ ላይ የጣለው ጌታቸው ነበር፡፡ ሌሎችም እርሱን ተከትለው አንድ በአንድ እየቀደዱ ጣሉ፡፡

‹‹ማስተዛዘኛ እንኳዋን የለም?››

‹‹ማስተዛዘኛው ቆርጦ አቅዋም መውሰድ ነው›› አለ ሀብቱ፣ ወደ ላይ አንጋጦ ቀይ ድዱን እያሳየ፡፡

ሁሉም ቀዳደው የጣሉትን የሎተሪ ወረቀት በበር የሚገባው ሃይለኛ ነፋስ ከወለሉ ላይ እያተራመሰ ይበትን ነበር፡፡ ሁሉም በዝምታ ተውጠው፣ እያንዳንዳቸው በአሳብ እየተጉዋዙ፣ የተቀዳደዱትን የሎተሪ ቲኬቶች በአይናቸው ሲከተሉ እንደ ቆዩ፣ መልካሙም የሎተሪ ቲኬቱን ቀዶ ጣለ፡፡ ነፋሱ ይዞት ሄደ፡፡

ባሻ ትርፌ፣ ‹‹ምኞች! የጨዋ ልጅ እድል ካከተመ ቆይቶአል!›› አሉ እየተነፋነፉ፡፡

ጌታቸው ወደ መልካሙ ዞሮ፣ ‹‹ገብርኤልና ስላሴዎች ከኛ የተሻለ ጉቦ የሰጣቸው አገኙ መሰለኝ! በጨረታው አልተገደዱም›› አለና፣ የውስኪ ብርጭቆውን አንስቶ፣ ‹‹ለወደፊቱ ህይወታችን! ወይስ የወደፊት ህይወት የሚባል ነገር የለም? ብሎ ቆመ፡፡

‹‹የነገው ህይወታችን በደርቤ እጅ ነው!›› አለ ታቦር፡፡

ጌታቸው፣ ‹‹እንግዲያውስ ለደርቤ ጤንነት!›› አለና፣ ውስኪውን ጨለጠ - እስከ መጨረሻዋ ጠብታ. . .

# ምእራፍ ፲፫

"ለወይዘሮ አምሳለ ምሳለና ለአቶ ጉልላት ቀኑ ቀውጢ ሆኖባቸው ነበር። ስለ ቀበሩት መሳሪያና ስለ ደርቤ ማሰብ አቁመዋል። መነታረኩና መወነጃጀሉም ትተዋል። ስለ ራሳቸው ህልውናም ሆነ ስለ ችግራቸው ረስተዋል። ሁለቱም የተጨነቁበት ጉዳይ በሂሩት መጥፋት ነበር።

ሂሩትን ፍለጋ ስልክ ያልደወሉበት የዘመድ ቤት አልነበረም። ከሂሩት የቅርብና የሩቅ ጉደኞችም መሃከል ስልክ ያልተደወለለት አልነበረም። ተያይዘው ያልደረሱበትም ሰፈር አልነበረም። ሬሳ ወድቆበታል የተባለ ሰፈር አንድም አልቀራቸውም። ከተማውን ከዳር እስከ ዳር አዳርሰውታል።

በደጀ ሰላሙ ላለፉት ታቦት ሁሉ - ገብርኤል - በአታ - ስላሴ - ቅድስት ማርያም - መድሀኔ አለም - የካ ሚካኤል - ጨርቆስ - እስጢፋኖስ - ልደታ - ተክለሃይማኖት - ራጉኤል - ቅዱስ ዮሐንስ - ቅዱስ ጊዮርጊስ፥ ‹‹ሂሩትን ከዚህ መአት የሰወርክልኝ እንደሆን፥ ምንም ሳይነካት ያስገኘህልኝ እንደሆን›› በማለት፥ ሰንጋ - ሙክት - ጃንጥላ - ገንዘብ - ወርቅ - የጆሮአቸውን ጉትቻ - የጣታቸውን ቀለበት - የአንገታቸውን ወርቅ - እጣን - ከርቤ - መጋረጃ - ግምጃ - ጡዋፍ - ያልተሳሉት ነገር አልነበረም።

ወይዘሮ አምሳለ በየደረሱበት የወደቀ ሬሳ ገና ከሩቅ ባዩ ቁጥር፥ ‹‹እኔ ወይዘሮ አምሳለ! እኔ አያይም! የኔ ፅጌ ረዳ ናት የተቀጠፈችው! አመለ ቅብጥብጥዋ! አላይም! አይኔ አያይም! የኔ ፅጌ ረዳ ናት የተቀጠፈችው! አመለ ቅብጥብጥዋ! ቁንጥንጥዋ እመቤት!›› እያሉ፥ ደረት ጥለው በመጮህ አገር ሲያስቸግሩ ነበር የዋሉት።

አቶ ጉልላትና ወይዘሮ አምሳለ በክንቱ ሲማስኑ ውለውና በከባድ ሃዘን ተውጠው ሲመለሱ፥ ጎረቤታቸው ይቀልጥ የነበረው የሰርግ ዘፈን፥ ይደለቅ የነበረው ከበሮ፥ ያስተጋባ የነበረው እልልታ፥ አንዱ ሲሰቅ ሌላው ያስቅሳል እንዲሉ፥ የህይወት ሁለት ገፅታ ሳይከሰትላቸው አልቀረም። የሰርጉ ዘፈን ምሬታቸውን በማባባሱ ሁለቱም በዝምታ ስቅስቅ ብለው ያለቅሱ ስለነበረ፥ ሁለቱም፥ የድሃ ከቤታቸው ደጃፍ የተደረደረውን የመኪና ብዛት አላጤኑትም። ሁለቱም፥ የድሃ ሰርግ መሆኑን ዘንግተው፥ መኪናዎቹ ሰርጉ ቤት የተጠሩ እንግዶች ሳይሆኑ አይቀሩም በማለት በግምገማሽ ልብ አስበው ነበር።

ለአደጋ ተጋልጦ ሳለ የሚያደርገው ነገር ጠፍቶት ዝም ብሎ በአሳብ መጨነቁ ነበር በይበልጥ ያስጨነቀው።

«ከአደጋ ጋር ድብብቆሽ መጫወት!» የሂሩት አባባል ትዝ ባለው ቁጥር «ጅል!» እያለ ይሳደባል። ውስጥ ውስጡን እንደ መጋዝ ይዞ የሚገዘግዘው ግን ሌላ ነገር ነበር። «ብቃ ፈሪ ነኝ!» ብሎ ራሱን ለመታዘብ ይቃጣውና፥ «የለም ራሴንና እህቴን ከዚህ አደጋ ለማውጣት መሞከር ፈሪ አያሰኘኝም!» ቢልም፥ ራሱን በራሱ ለማሳመን እያቃተው ከራሱ ጋር ይጣላል።

በአሳብ ሲጨነቅ ከዋለ በሁዋላ፥ የእናቱና የቤተዘመዱ ዋይታ ህሊናውን ስላስጨነቀው፥ አንድ ነገር ለማድረግ ቆረጠ። ድንገተኛ አሳብ መጣለት።ደርቤ መጥቶ ከፊቱ ተደቀነ።

ደርቤ ከነጋ እፎይ ብሎ የሚተነፍስበት የአንድ ደቂቃ ጊዜ እንኳዋን አላገኘም። በቀበሌው ቁጥጥር ስር የዋሉን ግለሰቦች ማህደር አንድ በአንድ መርምሮ ውሳኔ መስጠት፥ ጥቆማ የተደረገባቸውን ግለሰቦች ተከታትሎ ሁኔታቸውን በተጨባጭ ማጣራት፥ የቀበሌው ጥበቃ የሚጠናከርበትን መንገድ ባስቸኳዋይ መሻት፥ እነዚህና እነዚህን የመሳሰሉ ስራዎች ከፊቱ ተደቅነው፥ መስራት ያለበት ስራ ብዙ፥ የተሰራው ጥቂት እንዲሉ፥ የሚይዘውና የሚጨብጠው ነገር ጠፍቶት ይንደፋደፍ ነበር። በዚያ ላይ፥ እግር በእግር የሚተኩ ስብሰባዎች መሳተፍ፥ የማያቋርጡ አቤቱታዎችን መስማትና በየደቂቃው የሚመጡትን የስልክ ጥሪዎች መቀበል ነበረበት። ስለሆነም፥ ከስራ ብዛት የተነሳ ስለ ደረሰበት የህሊና ጭንቀት ለማስታወስ ጊዜ አላገኘም። ሆኖም ከአእምሮው በስተጀርባ አንድ ነገር ሳያቋርጥ እንደሚጎተጉተው ይሰማው ነበር።

በተለይም ከጥዋት ጀምሮ እስከ ስምንት ሰአት ድረስ ያለውን እንደ አይኑ ብሌን የሚሳሳለትን ጊዜ ያሳለፈው በላዲሶ ቀብር ዝግጅትና በቀብሩ ስነ ስርአት ላይ ስለነበረ፥ ፋታ አላገኘም። ከቀብር ሲመለስ ከድካሙ ብዛት ሰውነቱ ዝሎ ነበር።

ሌላውን ሊያሳምን አይችልም›› ካለ በሁዋላ፥ ‹‹ከነጋ እህል አልቀመስኩም! በጣም ርቦኛል›› አለው።

‹‹ወንድሜን!›› አለና፥ እፍኝ የሽንብራ ቆሎ ከኪሱ አውጥቶ ሰጠው።

‹‹ዘዴኛ ነህ ጃል! ስንቅህን ይዘህ ትዞራለህ!›› ብሎት፥ ቆሎውን እየቆረጠመ፥ ‹‹ሲርበኝ የህፃንነት ዘመኔ ትዝ ይለኝና ሆዴን ባር ባር ይለዋል። እናቴም ትዝ ትለኛለች። አንጀት ጠብ የሚል እህል እያማራት ነው ጥላኝ የሞተችው። ጠኔ በያዘኝ ቁጥር የምታደርገው ነገር ሲጠፋት፥ እቅፍ አድርጋ እንቅልፍ እስኪወስደኝ ድረስ ታባብለኝ ነበር። እንባ የሚያቀሩት አይኖችዋ ትዝ ይሉኛል። አንዳንዴ ጠኔው ብሶብኝ ሳስቸግራት እያለቀሰች ትመታኝ ነበር። እኔ ደግሞ ማልቀሴን አላቆምም። ታዲያ እብድ ሆና ከቤት ብር ብላ ትወጣለች። እኔ ደሞ ደጅ ቁጭ ብዬ እጠብቃታለሁ። በህይወት የማልቆያት ስለሚመስላት ነው መሰለኝ እየሮጠች ስትመጣ እኔም እየሮጥኩ ወደስዋ እሄዳለሁ። አንድ ነገር ሳትይዝልኝ አትመለስም ነበር። ያንን እየተስገበገብኩ ስበላ እንባ ባቀረሩ አይኖችዋ ትክ ብላ ታየኛለች። ህይወታችን ይሄው ነበር - በየእለቱ›› አለና፥ በረጂሙ ተንፍሶ ሲያበቃ፥ ‹‹እንዲያ እንዲያ ስንል አንድ ቀን ተስቦ ያዛት። ከተጋደመችበት ዳግመኛ አልተነሳችም። ልቅሶዬ እንኳዋን ሊቀሰቅሳት አልቻለም. . .ኦህ! ይህን ሁሉ ለምን እንደማወራህ አልገባኝም። ረሀብ የሚሉት ቃል ስሜቴን ስለሚቀሰቅስብኝ ነው መሰለኝ። ግሩም ቆሎ ነው›› አለውና የቀረውን ቃመው።

እፍኝ ቆሎ ጨመረለትና፥ ‹‹እኔም እንዳንተ በስቃይ ነው እዚህ የደረስኩ። የት ወደቅ ብሎ የሚጠይቀኝ ማንም አልነበረም። ያሳለፍኩትን ስቃይ ሳስታውስ ሰው ሁሉ ያስጠላኛል›› አለው።

ደርቤ በሰውዬው አባባል ተነክቶ ሲያስብ ቆየና፥ ‹‹እንዲህ አይነቱ አመለካከት ጥሩ አይደለም። ጥላቻ አላማ መሆን የለበትም። የኛ አላማ ፍቅር ነው - የሰው ልጅ ፍቅር። ጠላቶቻችን የወደቀው ስርአትና የዚያ ስርአት ቁንጮዎችና ደጋፊዎች ናቸው እንጂ ሰው ሁሉ አይደለም። አንድ ሀቀኛ አብዮተኛ ጥላቻንና ቂም በቀልን ምን ጊዜም ቢሆን አላማው ማድረግ

የሚያመራውን የመቆመርያውን ርምጃ ዛሬ እናንተ ወስዳችሁአል። በተላሉ የሚገመት ርምጃ አይደለም። በዚህ ቀበሌ ታሪክ ውስጥ ተገቢውን ስፍራ ይይዛል ብዬ አምናለሁ። ለመሳሪያዎቻችሁ አስፈላጊ ደረሰኝ ይሰጣችሁአል። በቅርብ ጊዜ ውስጥ መሳሪያዎቻችሁ እንዲመለሱላችሁ ተደርገው፥ የአብዮቱን ስፈር እንደምታጠናክሩባቸው አልጠራጠርም። አመሰግናለሁ›› ብሎ ንግግሩን እንደ ጨረሰ፥ ሁሉም ግርማ ሞገስ ባለው ሁኔታ በአንድነት እጅ ነሱ።

ደርቤ ከደስታው ብዛት የእያንዳንዳቸውን ጉንጭ ይዞ ለመሳም ከጅሉት ነበር። አንድ የአብዮት ጥበቃ ጉዋድ ሲሮጥ መጥቶ፥ ‹‹ስልክ ይፈልግሃል። በጣም አስቸኩዋይ ነው ትላለች። ሶስተኛ ጊዜ መደወልዋ ነው›› ብሎ ነገረው።

‹‹ማን ናት እሰዋ?። ቆይታ ልትደውል አትችልም?››

‹‹ሂሩት ነኝ ትላለች። ቆይተሽ ደውይ ብላት አሁን ካላቀረብክልኝ ሞቼ እገኛለሁ አለችኝ። ሃይለኛ ሴት ናት።››

ደርቤ ደነገጠ። ሂሩት የሚል ስም ሲሰማ ልቡ ይደነግጣል። ሂሩት የምትባል ሌላ ሴት አያውቅም - ልቡ ውስጥ ካለችው ሌላ። ሂሩት በሚል ስም የሚጠሩ ሴቶች ሲያጋጥሙት ሁልጊዜ ከፊቱ መጥታ የምትደቀነው ሂሩት ጉልላት ብቻ ነበረች። ሂሩት - ስምዋ ራሱ ለጆሮው እንደ ረቂቅ ሙዚቃ ሆኖ ነበር የሚሰማው።

የስራ ጉዋደኞቹ ለሽማግሌዎቹ ደረሰኝ ሰጥተው በክብር እንዲሸኙዋቸው አዘዘና እየተቻኮለ ወደ ቢሮው ሄደ። ቴሌፎኑን ሲያነሳ እጁ ይንቀጠቀጥ ነበር።

‹‹ሀሎ. . .››

‹‹ደርቤ ነህ?››

‹‹ነኝ. . .››

‹‹ሂሩት ነኝ።››

‹‹አውቄአለሁ››

‹‹በምን አወቅከኝ?››

‹‹በድምፅሽ፡፡ ድምፅሽ የትም አይጠፋኝም፡፡ ስንት ዘመን ስሰማው የኖርኩ ድምፅ አይደለም እንዴ? አንዳንድ ስሞችና ድምፆች ልዩ ስሜት ይሰጣሉ፡፡››

‹‹ታዲያ ምን ነው አስጠበከኝ ልጄ? የአብዮት ጥበቃ ሊቀ መንበር መሆን ያኮራል እንዴ? በነገራችን-እንኳዋን ደስ አለህ!››

‹‹ስራ ይገፍ ነው እንጂ ምኔ አንቺ ላይ ይኮራል ብለሽ ነው ሁሉጊዜም አሽከርሽ ነኝ፡፡››

‹‹ሁሉጊዜም ወንድምሽ ነኝ ብትለኝ ይሻላል፡፡››

‹‹እኔ የምመርጠው አሽከርነቱን ነው፥ እንዲህ በማለቴ ሌላ ትርጉም እንዳትሰጪው፡፡ አንቺ ሀብታም እኔ ድሃ ምን ሲሆን ወንድምና እህት እንሆናለን ማለቴ አይደለም፡፡ ምረጥ ቢሉኝ አሽከርሽ መሆንን ነው የምመርጠው፡፡ አሽከርሽ መሆን የበለጠ ደስታ የሚሰጠኝ ይመስለኛል›› አላት፡፡

ዝም ብላ ስታስብ ቆይታ፥ ‹‹ብዙ ደሞዝ ካልጠየቅኸኝ ስራ ስይዝ እቀጥርሃለሁ›› አለችውና፥ ከት ብላ ሳቀች፡፡

‹‹ደሞዝ አልጠይቅም ኧረ!››

‹‹ያለ ደሞዝማ ብዝበዛ ይሆናል!›› አለችውና፥ ‹‹እንደ ክርስቶስም በምሳሌ መናገር ጀምረሃል መሰለኝ!›› በማለት፥ በአሽሙር ነካ አደረገችው፡፡

‹‹ጠቢባን ይነጋቾዋል!›› አላትና፥ መሀረብ አውጥቶ ከፊቱ ላይ የተንቸረፈፈውን ላብ ጠረገ፡፡ እጁም ሳይቀር አልቦት ነበር፡፡

ሂሩት በሀሳብዋ፥ ‹‹እኔ ደንቆሮ ነኝ፡፡ እውነቱን ነው፡፡ ስለ ራሴ ብቻ ስለማስብ ነው መሰለኝ፥ የሰው ስሜት አይገባኝም፡፡ ግን ህይወት ተአምራዊ ነገር ናት፡፡ አይናችን እየተገለጠ ነው የሚሄደው›› ስትል ቆየችና፥ ‹‹ለብርቱ ጉዳይ ፈልጌህ ነበር›› አለችው፡፡

‹‹አሽከርሽ መሆኔን እመርጣለሁ ብዬሽ የለም? ከቃልሽ አልወጣም፤ ጉዳዩን ንገሪኝ›› አላት፡፡

‹‹በስልክ የሚነገር አይደለም፡፡ ላገኝህ እፈልጋለሁ፡፡››

‹‹መቼ?››

‹‹ከተቻለህ አሁን። ወይም በሁዋላ። ሱቃችንን ታውቀው የለም? እዚያ።››

‹‹እሜቴም ጥዋት ደውለውልኝ በጣም እፈልግሃለሁ ብለውኝ ነበር። ይገርምሻል፤ አንዲት ደቂቃ እረፍት የለኝም። ሳላስቀይማቸው አልቀረሁም። ይኸውልሽ አሁንም ላስቸኩዋይ ጉዳይ ስብሰባ መግባቴ ነው›› አለና፥ ምን እንደምትለው ለመስማት ፈልጎ ዝም አለ።

‹‹ሂሩቴ፥ ምንነው ዝም አልሽ? ተቀየምሺኝ መሰለኝ?›› አላት።

‹‹ለምን አልቀየምም? ግን ጥፋተኛዋ እኔው ነኝ›› በል ተወው ስትል፥ አቋዋረጣትና፥ ‹‹ምን አባቴ ላድርግ ትይኛለሽ? ፋታ የለኝም እውነቴን ነው. . . እንጂ ለነገሩማ እኔም ላገኛችሁ በጣም ፈልጌ ነበር. . . አንቺንና ተሰማን›› አላት።

‹‹ለምን ትፈልገናለህ?›› ብላ ጠየቀችው፥ ድምፅዋን በድንገት ከፍ አድርጋ።

‹‹የምንነጋገርበት ብርቱ ጉዳይ አለ። እሜቴንና ጌቶችንም በጣም እፈልጋቸዋለሁ። የጊዜ ጉዳይ ሆነብኝና ነው እንጂ።››

‹‹እኮ ለምን?››

የድምፅዋ መለወጥ ታወቀው። ድምፅዋ ውስጥ የመደናገጥ ወይም ግራ የመጋባት ሁኔታ ይሰማ ነበር።

‹‹ምን ሆንሽ?›› ብሎ ጠየቃት።

‹‹ምን ሆንኩ?››

‹‹ድምፅሽ ተለወጠብኝ። ድንገት ስትርቂኝም ተሰማኝ።››

‹‹መስሎህ ይሆናል።››

‹‹እሺ ማታ እንገናኝ።››

«በስንት ሰአት?»

«ሶስት ሰአት ላይ። ሱቅ ሳይሆን ቤታችሁ። ሁላችሁንም ባንድነት ላገኛችሁ እፈልጋለሁ።»

«ሶስት ሰአት ላይ አይቻለኝም. . .እ. . .» አለችና፣ ለምን እንደማይቻላት ምክንያት ስትፈልግ ቆይታ፣ «ነፃ ርምጃ በተፋፋመበት በዛሬው ጊዜ አምሽቶ መሄድ አደገኛ ነው። አይመስልህም?»

«የሚያሰጋ ነገር የለም። ለሀቀኛ አብዮተኞች ጊዜው አያሰጋም። የስጋቱ ጊዜ አልፎአል። አሁን በማጥቃት ላይ ነን።»

«አዎን ልጄ! ላንተማ ሁሉም በእጄ ሁሉም በደጄ ሆኖልሃል። ለማንኛናም ዛሬ ማታ አይመቸኝም» አለችው።

«እሺ ስብሰባውን እንደ ጨረስኩ ልደውልልሽ» አላት። እሺ ልትለው ነበር፡ አሳብዋን ለወጠችና፣ «እኔ ሲመቸኝ እደውልልሃለሁ። አትቸገር። ቻው!» ብላ፣ ለመመለስ እድል ሳትሰጠው ስልኩን ዘጋችበት።

ሂሩት ስልኩን እንደ ዘጋች ወደ ላኢከ ዞር ብላ፣ «ምን እንዳለኝ ሰምታችሁአል?» አለች።

«ምን አለሽ?» አላት ተፈራ፣ ቸኩሎ።

ቀኑን ሙሉ ከነበሩበት ኪዮስክ - ከኢ.ህ.አ.ፓ. ህዋስ - የሚወጣበትን ደቂቃ በናፍቆት ይጠባበቅ ነበር። ከጥዋት ጀምሮ በሰፈሩ ከባድ አሰሳ ይካሄድ ስለነበረ መውጣት አልቻለም። ሰፈሩ አንድ በአንድ ሲታሰስ ኪዮስክዋን ዞር ብሎ የተመለከተ አልነበረም። እንደዲያውም፣ ፀሀይ ያቃጠላቸውና ሲጃራ የጠማቸው ፈታሾች እየተመላለሱ ከሱቅዋ አምቦ ውሀና ሲጃራ ሲገዙ ነበር ሂሩት ወደ የዋሉት። ፍተሻው ጋብ ካለ በሁዋላ በተፈራ ጎትጓቶችነት ነበር ሂሩት ወደ ደርቤ የደወለችው።

«እኔን፣ ተሰማን፣ እናቴንና አባቴን - ሁላችሁንም ባንድነት በሶስት ሰአት ላይ ለማግኘት ይፈልጋል። ለምን ይሆን?» አለች።

ላእከ እየቀለደ፣ «ቤተሰቡን ሰብስቦ ጉዞ ሊጠይቅ ይሆናል፣ አጅሬ» አላት።

«እየደፈርክም ብለህ ነው? ደፋር ነው ሎ» አለው ተፈሪ።

«የለም የለም፣ አለች ሂሩት፣ «ሁላችንንም ጥንድ ወጥመድ ሊያደርግ ነው፤ ተንኮሉ ገብቶኛል።»

ላዕከ ራሱን ነቀነቀና፣ «አትቃዢ እባክሽን» አላት፣ «አንድ ማይም የቀበሌ ዘበኛ የሌለውን እውቀትና ጥበብ አለው ብለሽ አትካቢው። እንደነገራችሁን ከሆነ ሰውዬው በነ እሰራለሁ ብሎ የተነሳ ጆል ነው። ሁላችሁንም የፈለገበት ምክንያት ለኔ ግልፅ ነው። ሊያግባባችሁ ፈልጎ ይሆናል። በእድሉ መጠቀም ነበረብን። እምቢ በማለትሽ ተሳስተሻል። በገዛ ወጥመዱ ልታስገቢው ትችያለሽ። ውብ ሴት የማትረታው ወንድ የለም - በተለይም በኛ ህብረተሰብ ውስጥ እንደ ውሻ ተከትሎሽ ባይመጣ ምናለ በይኝ።»

ወዲያውኑ፣ ጠጉሩን የተላጨ አንድ ወጣት ገባና፣ «የተጠናከረ ፈታሽ ቡድን በሰፈሩ እንደ ገና ተሰማርቶአል» አላቸው።

ሁሉም ተያዩ።

ላእከ የሚያጨሰውን እፀ ፋርስ በረዥሙ ማግ አድርጎ ቁራጩን ወረወረና፣ «እነዚህ ሰዎች ዛሬ አልለቀቁንም፤ ጥቆማ ደርሶአቸው ይሆናል» አለ። ሁሉም ስራ እንዲያቆሙና መብራት አጥፍተው በተጠንቀቅ እንዲቆዩ አዘዛቸው።

ሁሉም ስራቸውን አቁመው መሳሪያቸውን መፈተሽና ማጉረስ ጀመሩ።

«እቅዳችንን ሊያስተጓጉሉብን ነው መሰለኝ» አለች ሂሩት፣ በናፍቆት የምትጠባበቀው ከአደጋ ጋር የድብብቆሽ ጨዋታ ትዝ ብሎአት።

«አትስጊ አሁን ይሄዳሉ። በቀን ያጡትን ቦታ በምሽት እንዴት ያገኙታል? ምፅአት ቢመጣ ይህን ቦታ ሊያገኙት አይችሉም፤ ከሀዲ መካከላችን ካሌለ በስተቀር!» አላትና፣ «በነገራችን ላይ ስለ ወንድምሽ የሰጠሽኝ መልስ አላጠገበኝም። ዋሽተሽኛል። ወንድምሽ የታመመ አልመሰለኝም። እኔ

‹‹የምለው ነገር ትርጉም አለው? ለምን ይህን ሁሉ እንደምለፈልፍ እኔም አልገባኝም። ለማለት የፈለግሁት. . . ምን ለማለት ነበር የፈለግሁት. . . ነበር የፈለግሁት - ባጭሩ፣ ምክንያቱም ክፉና በጎን የማይለይ ሀሊና ይዋሽ አይዋሽ አይታወቅም። የኢትዮጵያዊ ባህርይ እንቆቅልሽ ነው - ፍቺ የሌለው እንቆቅልሽ ነው። እውነቱን ንገሪኝ። የት ነው ወንድምሽ?›› አለት፥ ሂሩትን።

‹‹እውነቱን ማወቅ ትፈልጋለህ? የት እንደሆነ አላውቅም። ቤት ሂዶ ይሆናል። ግን ስልክ ደውዬ ለማረጋገጥ አልፈለኩም። ብቻ እዚህ እንደማይመለስ እርግጠኛ ነኝ›› አለችው፥ ፍርጥም ብላ፣

‹‹አሁን ገባኝ። አለተሳሳትኩም። በራሱ ላይ ፈርዶአል በይኛ!››

‹‹አልገባኝም።››

‹‹ይገባሻል›› አላትና፥ ሂዶ ለአንድ ጠረንገሉ ወጣት በጆሮው አንድ ነገር ነገረው። ወጣቱ ፊቱን በቁም ነገር አኮሳትሮ እያዳመጠ በእሺታ ራሱን ይነቀንቅ ነበር።

ሂሩት ምንም እድል ሳትሰጠው በድንገት ስልኩን ጆሮው ላይ የዘጋችበትን ምክንያት ለማሰላሰል ደርቤ ጊዜ አላገኘም። ወዲያውኑ ነበር ተጠርቶ ስብሰባ የገባው። የስብሰባው አላማ ስለ እናት አገር ጥሪ ዝግጅት ለመነጋገር ነበር። ሆኖም ስብሰባው ከተጀመረ ከጥቂት ደቂቃዎች በሁዋላ፥ ውይይቱ ፈር ለቆ ወደ ዲሞክራሲያዊ መብት ጥያቄዎች በማምራቱ፥ ስብሰባው የቡድን ስሜት ማንፀባረቂያ መድረክ ሆኖ ለገላጋይ እስከማስቸገር ደርሶ ነበር።

‹‹የዲሞክራሲያዊ ማእከላዊነት ጥያቄ የሰፊውን ህዝብ ነፃ ርምጃ ለማይናፍቅ ታቅዶ የቀረበ የቀኝ አድርባዮች ጥያቄ ስለሆነ፥ እናወግዘዋለን! ነፃ እርምጃችን በትግላችን ይቀጥላል! አድርባዮች ይጋለጣሉ!›› አሉ፥ ከዳር የተቀመጠው ባለ አንድ አይና ሰውዬ።

‹‹ዲሞክራሲያዊ ማእከላዊነት እየተባለ ከትናንት ማታ ጀምሮ እስካሁን የሚለፈፈው ነፃ እርምጃችንን ለመግታት ብቻ ሳይሆን ዲሞክራሲያዊ መብት

‹‹ለጊዜው የወዛደሩ ፓርቱ ባይኖርም፥ አብዮታዊ መንግስት የለም፥ አብዮታዊ መንግስት አለ። አብዮታዊ አመራር የለም የሚሉ ሰዎች ካሉ፥ አቋዋማቸውን ግልፅ እንዲያደርጉ እፈልጋለሁ። እኔ በበኩሌ፥ አብዮታዊ አመራር የሚሰጥ አብዮታዊ መንግስት አለ ብዬ አምናለሁ። አብዮቱ ማእከል አለው ብዬ አምናለሁ። ስለሆነም፥ ዲሞክራሲያዊ ማእከላዊነት አሰራር በተግባር እንዲተረጎምና በነፃ እርምጃ ስም የሚፈፀመው ስርአት አልበኝነት እንዲጠፋ እታገላለሁ. . .

‹‹ጉዋዶች! የወዛደሩ ፓርቲ በሌለበት ሁኔታ የዲሞክራሲያዊ ማእከላዊነት አሰራር ሊኖር አይችልም፥ የሚሉት እነማን ናቸው? በፍርሃት ተውጦ ማን እንደሆኑ፥ ለምን አላማ ተሰባስበው እንደ ተሰለፉ፥ ገሀድ ሳናወጣ ብንቀር የገዛ ህሊናችን ይፈርድብናል። እንዲህ አይነቱን ውዥንብር የሚነዙት ለስልጣን የቋዋመጡ፥ አብዮታዊውን መንግስት በሾኬ ጠልፈው በመጣል ከሰፊው ህዝብ ትከሻ ላይ ባቋዋራጭ ወጥተው ጉብ ለማለት የሚፈልጉ ንኡስ ከበርቴዎች ናቸው። ዲሞክራሲያዊ መብት ለጭቁኖች አሁን፥ የሚለው አቋዋም፥ ጊዜያዊ ህዝባዊ መንግስት አሁን፥ ከሚለው ጥያቄ በይዘትም ሆነ በአላማ የሚለይበት መንገድ አይታየኝም. . .

‹‹አብዮታዊው መንግስት ጉያ ውስጥ ተሸጉጦ ሰፊውን ህዝብ አነቃለሁ፥ አደራጃለሁ እያለ በአንዳንድ ፋብሪካዎች፥ ቀበሌዎችና መንግስት መስሪያ ቤቶች አካባቢ ራሱን ለስልጣን ሲያደራጅ የቆየው ቡድን፥ ዛሬ ድርጅታዊ እብጠት ተሰምቶት፥ ዲሞክራሲያዊ መብት ለጭቁኖች አሁን፥ በሚል ሽፋን ስልጣን ስጡኝ፥ እያለ ሲደነፋ ያስቃል። ነገሩ የልጆች ጨዋት ሆኖ ነው የሚታየኝም. . .

‹‹እኔ ምሁር አይደለሁም። ስለ ሳይንሳዊ ሶሺያሊዝም ያለኝም እውቀት በጣም አነስተኛ ነው። ግን ደደብ አይደለሁም። በድርጅት አካባቢ ግለሰቦችን አሰባስቦ ሆያ ሆዬ በማብዛት የወዛደሩን ፓርቲ ለማስገኘት እንደማይቻል ይገባኛል። የወዛደሩ ፓርቲ ስል ሳላስታችሁ አልፈልግም. . . በኢትዮጵያ የወዛደሩ መደብ የሰርቶ አደሩ ፓርቲ ብል ትክክል ይመስለኛል። አሁን ባለንበት ተጨባጭ ሁኔታ ገና እያቆጠቆጠና እያበበ በመሄድ ላይ ነው። ለማንኛውም ነገር የሰርቶ አደሩን ፓርቶ ሀልውናው የተጠናከረ አይደለም።

ሲመሰርቱ የሚችሉት በግንባር ቀደምትነት ታግለው፥ የሚያታግሉ፥ አመራራቸው በሰፊው ህዝብ ዘንደ ተቀባይነትንና ታዋቂነትን ያገኙ፥ አብዮቱንና የኢትዮጵያን አንድነት ለመጠበቅ ችሎታና አስተማማኝ ሃይል መሰረት ያላቸው ታጋዮች ናቸው እንጂ፥ የዚህ ድርጅት ወይም የዚያ ድርጅት የማእከላዊ ኮሚቴ አባል ነን በማለት፥ በር ዘግተው ሲያወኩ የሚውሉና አሜሩሪዎቻቸውን እየላኩ ምልመላ በገፍ እንዲካሄድ የሚያደርጉ ብልጣ ብልጦች አይደሉም።

‹‹ጉዋዶች! የስልጣን ጥማቸውን ለማርካት መሳሪያ ሲያደርጉን የሚፈልጉን ቡድኖች መታገል አለብን። የሀቀኛ አብዮተኞች አይነተኛ ተግባር፥ ሀቀኛ ታጋዮች የሰርቶ አደሩን ፓርቲ እንዲያስገኙ አመቺ ሁኔታዎች እንዲፈጠሩላቸው መታገል ነው እንጂ፥ በቅጥረኛነት ስሜት ለቡድኖች አምባገነንነት እርስ በርስ ሽኩቻ ማካሄድ አይደለም።

‹‹አቅዋሜን ገልጫለሁ። ቤቱ ፍርዱን እንዲሰጠኝ እጠይቃለሁ›› ብሎ ቁጭ አለ።

ቤቱ ስሜቱን በጋለ ጭብጨባ ገለጠለት። ሶስቱ ሰዎች ግን አቀርቅረው ነበር።

‹‹ሶስቱም በራሳቸው ላይ ግለ ሂስ አካሂደው ቤቱን ይቅርታ ይጠይቁ›› የሚል አሳብ ካንዱ አባል በመቅረቡ፥ ሁሉም አሳቡን በመደገፍ እጃቸውን አወጡ።

ሶስቱም ሰዎች የተመካከሩ ይመስል፥ በአንድነት ተነስተው ከስብሰባው ለመውጣት ሲሄዱ፥ በር ላይ የቆሙት ሁለት የአብዮት ጥበቃ ጉዋዶች አቆሙአቸው።

የቀበሌው ሊቀ መንበር የሚሰጠው ትእዛዝ ጠፍቶት ሲያቅማማ፥ ደርቤ ሽጉጡን ላጥ አድርጎ አቀባበለና፥ ‹‹ካሁን ጀምሮ በቁጥጥር ስር ውላችሁአል። እብሪት ለማንም አይበጅም። የሰፊው ህዝብ ዲሞክራሲያዊ መብት በተግባር እየተተረጎመ ነው። የናቃችሁትም ማእከል ፍርዳችሁን ይሰጣችሁአል›› እላቸውና፥ ትጥቃቸውን አንደ በአንድ አስፈትቶ እየነዳ ይዞአቸው ወጣ።

ሶስቱንም እየነዳ ሲሄድ በአይኑ ህሊናው ሌላ የትግል ግንባር ሲከፍት ይታየው ነበር። ዞር ሲል ተሰማ ጉልላትን ስላየ ተገረመና፣ «ተሰማ ምን ነው ደህና አይደለህም? ምን ታደርጋለህ እዚህ?» ብሎ ጠየቀው።

«አንተን ነበር የምፈልገው። ከመጣሁ ቆይቻለሁ» አለው፣ ጢሙን እየጎነተለ።

«ጠብቀኝ መጣሁ» ብሎት ሰዎቹን ተከትሎ ሄደ።

ደርቤ አልቆየም። ወዲያውኑ ነበር የተመለሰው። ተሰማ የመጣበትን ጉዳይ ለመስማት የቸኮለ መሆኑ ያስታውቃል። ተያይዘው ወደ ቢሮ ገቡ። ደርቤ እየተደናበረ ሄዶ መብራቱን አበራ። ጊዜው አልታወቀውም። ሰአቱን ተመለከተ። ከምሽቱ አንድ ሰአት ተኩል ሆኖ ነበር።

«ጊዜው እንዴት ይሮጣል!» አለ። «ጊዜ ተርፎን፣ የምናደርገውን አጥተን ሶስት ሺህ ዘመን እንዳላንቀሳቀስን ሁሉ፣ በድንገት ጊዜ ያጥረን ጀመር። ስለ ጊዜ ይገርማል! ኢትዮጵያውያን ጊዜ አጠረን ሲሉ ሰምቼ አላውቅም ነበር፣ ስለ ጊዜ ማን ደንታ ነበረው? «እሺ ነገ» ብሄራዊ ጠባያችን ሆኖ ቆይቶ ነበር። ባሁኑ ጊዜ ነገ የሚባል ነገር የለም። ህይወት ፍጥነት ጨምራለች!» አለውና፣ ትኩር ብሎ ሲመለከተው ከቆየ በሁዋላ፣ «ምን ሆነሃል? በጣም ትተክዛለህ። የፍርሃት መልክም ይታይብሃል» አለው።

ተሰማ አንገቱን ቀና አድርጎ በሚንቀጠቀጥ እጁ ጢሙን እየጎነተለ፣ «ደህና ብለሃል» አለው በጎረና ድምፅ፣ «በጣም ተክዣለሁ። ፍርሃትም አድሮብኛል። ጊዜም የለኝም። ጊዜ እየከዳኝ ነው!»

«ንገረን ምን ሆነሃል?»

ሲያቅማማ ከቆየ በሁዋላ፣ «መጀመሪያ ራሴን አጋልጬ እጄን ላንተ ልሰጥ ነው የመጣሁት» አለው።

«እንዲህ አይነቱን እርምጃ የሚወስዱ ደግኖች ናቸው። ታዲያ ለምን ፍርሃት አድሮብኛል ትላለህ?» ብሎ አበረታታው።

እንድትሆኑ ላግዛችሁ አስቤ ነበር፡፡ እንዲያስረክቡና በሰላም እንዲኖሩ ለመምከር ፈልጌ ነበር፡፡ ጌቶችም የደበቁትን መሳሪያ ለመድረስ ከፍተኛ የመንፈስ ጭንቀት አሳልፌአለሁ፡፡ ከዚህ ውሳኔ ላይ እስከሆነ ድረስ ለአብዮቱ ህልውና የማልወስደው እርምጃ የለም. . . ሆኖም፥ አብዮቱ ሀሲናዬ

‹‹እባክህን ሂሩት ያለችበትን ንገረኝ፡፡ ህይወትዋ አደጋ ላይ ነው!›› ያለው፡፡

‹‹ያለችበትን ቦታ እንዴት አድርጌ ልነግርህ እችላለሁ?››

‹‹ለምን አትችልም?››

‹‹ምክንያቱም የሰዋን ህይወት አድናለሁ ብዬ ሌሎቹን ለአደጋ ማጋለጥ ይሆናል፡፡››

‹‹አላማችን ግድያ አይደለም እያልኩህ! ደም የጠማን ሰዎች አይደለንም፡፡ የኛ ጥም ፍትህ፥ እኩልነትና ነፃነት ነው፡፡›› አለው ብስጭት ብሎ፡፡

‹‹አዎን፥ አንተ እንዲህ ትላለህ፡፡ ግን ላእከን አታውቀውም፡፡ ሰይጣን ነው፡፡››

‹‹ማን ነው ላእከ?››

‹‹ከሱ ጋር ናት፡፡ በዋዛ እጁን የሚሰጥ አይደለም፡፡ በህይወቱ የቆረጠ ሰው ነው፡፡ በህይወቱ የቆረጠ ስለሆነ፥ እኛ የምንወላውለው የህይወት ድንኮች እንፈራለን፡፡ በፍርሃት እንታዘዘዋለን፡፡ እንደሱ ብሆን ምን ነበረበት? ግን አይደለሁም፡፡ ፈሪ ነኝ፡፡››

‹‹ተሰማ! ፈሪ አይደለህም፡፡ በፍርሃት እንደ በግ መነዳትን ጠልተህ ነፃነትህን ለመሻት እዚህ መምጣትህ ደፋር አድራጎት ነው›› ሲል፥ ተሰማ በእምቢታ ራሱን ሲነቀንቅ ስላየው፥ ‹‹እውነቱን ነው፡፡ እኔ ላታልልህ አይደለም ይህን የምለው፡፡ ከማታምንበት ነገር ደፍረህ መውጣት ጀግንነት ነው›› አለው፡፡

«ግልፅ ነው» አለ ደርቤ።

«የለም ግልፅ አይደለም። ሂሩት ስለምትፈራህ ነው!!»

«ለምን ትፈራኛለች?»

«ስለምትወዳት። እንደምትወዳት እኔ አውቃለሁ። አድራጎትህ ሁሉ ለስዋ ያለህን ፍቅር ቁልጭ አድርጎ ያሳየኝ ነበር። ቶሎ አንድ ትልቅ ቦታ ላይ ለመድረስ የምታደርገው ጥረት ሁሉ ለስዋ ባለህ ምስጢራዊ ፍቅር ምክንያት መሆኑ ለኔ ስውር አይደለም። አውቃለሁ። ራስህን አለቃይተሃል። ስቃይህ ይገባኛል. . .

«ግን ሂሩት ይህን ሁሉ አታውቅም ነበር። ገና ትናንት ማታ ነው ያወቀችው። እኔ ነኝ የነገርኩት። እና፥ ደነገጠች። በዚህ ላይ የኢ.ህ.አ.ፓ. ደሊዎች መሆናችንን አንተ እንደምታውቅ ስለምናውቅ ፍርሃት አደረባት። ተፈራ ደግሞ ሂሩትን እንደሚወዳት ታውቅ የለም? የምናደርገው ነገር ጠፋን። በነገራችን ላይ የአብዮት ጥበቃ ሊቀ መንበር ሆነህ መመረጥክን ወዲያውኑ ነበር የሰማነው፤ ግራ ገባን። አስገድደህ የምትወስዳት ስለ መሰላት ሂሩት በጣም ተጨነቀች። ተፈራም ሂሩትን አስገድደህ ስትወስዳት በሃሳቡ እየታው ቅናት አድርቦት ተናደደ።

«ባንድ ጊዜ ዋነኛ ጠላታችን ሆነህ ታየኸን። እና ምን አደረግን መሰለህ? ልናስገድልህ ወደንን። ስህተት ነው። ባንድ ፊት ላንተ፥ በሌላ በኩል ለእህቴ ሀሊናዬ እየተጨነቀ ነው። አእምሮዬ ልክ አይደለም።»

ደርቤ ተክዞ ዝም ብሎ ያዳምጠው ነበር። ተሰማ በሚናገርበት ጊዜ ሂሩት ከፊቱ መጥታ ትደቀን ነበር። አልፎ አልፎ የተከለከለች ፍሬ የሚል አሳብ ይመጣበት ነበር።

በረጂሙ ተነፈሰና፥ «አዎን፥ እንዳልከው ጥሉብኝ እወዳታለሁ» አለ። «የህልውናዬ ቅመም ለሱዋ ያለኝ ፍቅር ነው። ነጋም ጠባም ስለስዋ ነበር ማልመው። በአሳቤ ከስዋ ጋር ስነጋገር የምውልበት ቀን ነበር። ግን አሁን ንቱ ፍቅር መሆኑ ገብቶኛል። አንድ እጂ ብቻውን አያጨበጭብም። ባንድ

አንዳንዶቹ ጌታቸው የሚሰማውን ጩኸት ለማዳመጥ ጆሮአቸውን አቁመው ነበር።

‹‹አድሃሪ! አድሃሪ! ሲሉ አልሰማችሁም! ቀበሌዎች፣ ውይይት ክበቦች ተሰብስበው አድሃሪ! አድሃሪ! ይላሉ። እንዴት ነው አድሃሪ የሚሉት። ለምን አድሃሪ ይሉኛ! እኔ ጌታቸው ነው ስሜ። አይደለም እንዴ፣ ቲጊ? እኔ አድሃሪ ነኝ እንዴ? . . .

‹‹አድሃሪ አድሃሪ እያሉ ለምን እንቅልፍ ይነሱኛል? መኝታ ቤት ድረስ እየገቡ፣ ቢሮዬ እየመጡ፣ በየመንገዱ እየተከተሉኝ አድሃሪ! አድሃሪ! እያሉ ይጮሁብኛል። ነፃነት የለኝም እንዴ! በየግድግዳው ላይ፣ በየበሩ ላይ አድሃሪ! አድሃሪ! እያሉ በትልቁ በቀይ ቀለም የሚፅፉት እኔን ለመስደብ ነው? ቆይ ብቻ! ልክ አስገባቸዋለሁ - አንድ ባንድ!›› ብሎ እንደ ገና ራሱን ጭምድድ አድርጎ ሲይዝ፣ ሀኪሙ ‹‹አይዞህ። አሁን ዝም እናሰኛቸዋለን›› እያለው ወደ ጉዋዳ ይዞት ሄደ።

ትእግስት እያለቀሰች ተከተለቻቸው። የተቀሩት በሀዘን ከንፈራቸውን ይመጡ ነበር። ሁሉም ከንፈሩን ሲመጥ ነበር የሚሰማው። ወይዘሮ አምሳሉ አስር አስር ጊዜ ‹‹ጉድ ነው!›› ይሉ ነበር።

‹‹መርፌ ትወጋቸዋለህ?›› አለው ሀኪሙን ወደ ጉዋዳ ሲገቡ።

‹‹አዎን።››

‹‹እና ዝም ይላሉ?››

‹‹አዎን፣ ዝም ይላሉ።››

‹‹ሁለተኛ አድሃሪ! አድሃሪ! አይሉኝም?››

‹‹አይሉህም። ምን ቆርጦአቸው!›› አለውና፣ ሁለት ትናንሽ እንክብል መድሀኒቶች ከኪሱ አውጥቶ ሰጠውና እንዲውጥ አደረገው።

ጌታቸው መድሀኒቶቹን ከዋጠ በሁዋላ፣ ‹‹ጩኸቱ ቆሟል እንግዲህ! አይደለም?›› አለው።

‹‹ቀጥ ብሉ።››

‹‹እና እንቅልፍ ይወስደኛል?››

‹‹ጭልጥ አድርጎ።››

 ‹‹ሰላዮች! ሰላዮች! ጥቁር አጋሉ

ላእከ አውሬ መስሎ ጥርሱን በመንከስ፥ ቢሬታ ሽጉጥን አውጥቶ
አይሞትም!›› እያለ ሲጠጋቸው፥ ተፈራ በፍጥነት
ተኮሰበት፡፡

ላእከም አከታትሎ ተኮሰ፡፡ ተፈራም ከመውደቁ በፊት ሁለት ጥይት
አከታትሎ በደረቱ ለቀቀበት፡፡

ሂሩት አንጀትዋን በእጆችዋ ደግፋ፥ ‹‹እኔ አላምንም! እኔ አላምንም! አምላኬ
እባክህን ውሸት አድርገው!›› ስትል ከቆየች በሁዋላ፥ እጆችዋን ከሆዱዋ ላይ
አንስታ ተመለከተች፡፡ ትኩስ ደም በእጆችዋ ላይ እየተንጠባጠበ ይወርድ ነበር፡፡ ቡልቅ ቡልቅ እያለ የሚወጣው ደም በጥቁር ሱሪዋ ላይ ኮለል ብሎ ሲወርድ
አየችና፥ ‹‹መቼ ይህ ሆነና ነገሩ? ሰፈሩን ነበር እኮ በቀይ ልናጌጠው ያሰብነው፡፡
አምላኬ ውሸት አድርገው! እውነት አይደለም፡፡ እኔ አላምንም!›› እያለች ዘጭ ብላ
ወደቀች፡፡

ተፈራ በደሙ ውስጥ በደረቱ እየተሳበ ወደ ሂሩት ለመጠጋት የመጨረሻ
ጥረት ካደረገ በሁዋላ፥ እንደ ምንም ብሎ እጅዋን ጨበጠና በደከመ ድምፁ
‹‹ሂሩት! ሂሩት!›› ብሎ ጠራት፡፡

‹‹ተፈራ፥ እውነት ነው እንዴ? ንገረኝ!›› አለችው፡፡

‹‹እውነት ነው ሂሩቴ፡፡ ከሞት ጋር እየተፋጠጥን ነው፡፡ አየዞሽ! ከጥቂት ጊዜ
በሁዋላ ሁሉም ነገር ያልፋል፡፡ ለሚያፈቅሩን ሁሉ የሚቀረው ትዝታችን ብቻ
ነው፡፡ ከፍቅርሽ ጋር ወደ መቃብር መውረድ ደስታ ነው - ሂሩት! ሂሩት!››

‹‹ውሸት ነው በለኝ፡፡››

‹‹እሺ ውሸት ነው፡፡ በርቺ፡፡ እኔም እበረታለሁ፡፡ እኖራለሁ፡፡ እኖራለሁ በይ››
አላት፡፡

‹‹እኖራለሁ!››

‹‹አይዞሽ ትኖሪያለሽ፡፡ አንድ ነገር ብቻ ልለምንሽ፡፡ መቃብሬ ላይ አንድ ፅጌ
ረዳ አበባ ትከይልኝ፡፡ እንዳትጠወልግም ተንከባከቢያት፡፡ ይህን ብቻ ነው
የምጠይቀሽ፡፡ እሺ?››

እጇን ጠበቅ አደረገችው፡፡

ተፈራ፥ በድንጋጤና በፍርሃት ተውጠው ላፋቸውን ከፍተው ወደሚመለከቱዋቸው ወጣቶች ፊቱን አዞረና፥ ከወደቀበት በግድ ቀና ብሎ፥ «ሁላችሁም እጃችሁን ወደ ላይ!›› አላቸው።

ታዘዙት።

‹‹ፊታችሁን ወደ ግድግዳ አዙራችሁ፥ እጃችሁን ወደ ላይ አድርጋችሁ ተጠግታችሁ ቁሙ›› አላቸው።

እንዳዘዛቸው አደረጉ . . .

ከኪዮስኩ ውስጥ ተኩስ እንደ ተሰማ፥ ‹‹ምን ሊያደርጉ ይሆን?›› በማለት ተሰማ ደርቤን ጠይቆት ነበር።

‹‹አላማቸው አልገባኝም›› አለው፤ ተኩሱ በርዶ ፀጥ እንዳለ። ‹‹ላእከ ሰይጣን ነው ብዬሃለሁ›› አለውና አላስችል ብሎት፥ ‹‹ሂሩት! ሂሩት!›› እያለ ከተኛበት ተስፈንጥሮ ተነስቶ ባዶ እጁን ወደ ኪዮስኩ ሮጠ።

‹‹ተሰማ፥ ተመለስ! ተመለስ ብዬሃለሁ!›› እያለ ቢጮህበትም ስላልሰማው፥ ደርቤም ተነስቶ፥ ክላሺኑን ደግኖ ተከተለው።

ደርቤ ከመድረሱ በፊት ተሰማ የኪዮስኩን በር በትከሻውም በእግሩም እያለ ሰብሮት ስለነበረ ተከታትለው ወደ ውስጥ ገቡ።

ወደ ውስጥ የምታስገባውን ስውር በር ተሰማ ያውቅ ነበርና በጨለማ እየተደናበረ ሄዶ ከፍቶ፥ ‹‹ሂሩት! ሂሩት! ሂሩት!›› እያለ ወደ ውስጥ ዘለቀ። ደርቤ ተከተለው።

ክፍሉ ውስጥ ብርሃን ነበር። ተሰማ ጨለማ ውስጥ ቆይቶ በድንገት ብርሃን በማየቱ ለጥቂት ጊዜ ግር ቢለውም፥ ሶስት ሰዎች ወድቀው ታዩት። እህቱ የት እንዳለች ለማወቅ ጊዜ አልፈጀበትም። ሮጦ ሄዶ ላይዋ ላይ ተደፍቶ፥ ‹‹ሂሩትዬ ጥፋተኛው እኔ ነኝ!›› እያለ ይጮህ ጀመር።

ተፈራ ሁለቱ ተከታትለው መግባታቸውን እንዳየ ሽጉጡን ጥሎ፥ የመጨረሻ ጥረት በማድረግ ወደ ሂሩት በይበልጥ ለመጠጋት ሞከረ። እጁን ወደ ሂሩት እንደ ዘረጋ፥ አንድ ጊዜ ብቻ ህቅ ብሎ ፀጥ አለ።

ደርቤ ቀይ መሀረብ ከኪሱ አውጥቶ የተፈራን ፊት ከሸፈነ በሁዋላ፣ ሂሩት ደረት ላይ ተደፍቶ የልብዋን ትርታ አዳምጦ ሲያበቃ ተሰማን የአብዮት ጥበቃ ጉዋደኞችን በፍጥነት እንዲጠራ ነገረው። ተሰማ እንባውን እየረጨ ሮጦ ወጣ።

ደቂቃ በማይሞላ ጊዜ ውስጥ ተሰማና የአብዮት ጥበቃ ጓዶች ተከታትለው ሲገቡ፣ ደርቤ በግራ እጁ የሂሩትን አንገት ቀና አድርጎ ደግፎ ይዞ በቀኝ እጁ ክላሺኑን በሰዎቹ ላይ ደግኖ አገኙት።

ተሰማ እንባውን እያዘራ፣ ‹‹ህይወትዋ አለ?›› ብሎ ጠየቀው።

‹‹ትንፋሽዋ አለ›› አለውና እሱም እንባውን መርጨት ጀመረ።

‹‹ቶሎ ሆስፒታል እናድርሳት!›› አለ ተሰማ።

‹‹በምን መኪና? አለው ደርቤ።

‹‹እንግዲያውስ ቤት እንውሰዳት። ቶሎ በል!›› አለው።

ሂሩት አይኖችዋን ከፈተች። ብዥ ብሎባታል። ትኩር ብላ ደርቤን ተመለከተችው። ከንፈሮችዋን በግድ አላቃ፣ ‹‹ደርቤ ነህ?›› አለችው።

‹‹አዎን፣ ለመናገር አትሞክሪ። ደህና ትሆኛለሽ። በርቺ ብቻ›› አላት።

‹‹ስምህ ያስጠላኛል›› ብላ፣ ህይወት የሌለው ፈገግታ አሳየችው።

‹‹ሲሻልሽ ሌላ ስም ታወጪልኛለሽ። አሁን ዝም በይ ብቻ አላት።

‹‹ተፈራ ምን ነው ዝም አለ?›› ብላ ጠየቀች።

መልስ አላገኘችም። እንባዋ ኮለል ብሎ ወረደ። ቆየችና፣ በጣም በተዳከመ ድምፅ፣ ‹‹እውነት አይደለም በሉኝ. . . ፅጌረዳ አበባ. . . ፅጌረዳ አበባ›› አለችና፣ አይኖችዋን ከደነች። ከተከደኑት አይኖችዋ ውስጥ እንባ ይፈስ ነበር።

‹‹ይህን ስፍራ ማን አሳየህ? አለችው፣ ድንገት ነፍስ በዘራ ድምፅ።

‹‹እባክሽን ለመናገር አትሞክሪ። አላት ደርቤ።

ወዲያው ተሰማ፣ ‹‹እኔ ነኝ›› አላት።

ጆርዋን ማመን አቅቶአት አይኖቸዋን ከደነች። ግን፥ ዝም አላለችም። አይኖቸዋን በግድ ከፍታ ትኩር ብላ እያየችው፥ ‹‹አሁን የት ልትወስደኝ ነው?›› ብላ ጠየቀችው

ተሰማ ተፀፅቶ እኔ ነኝ ብዬ ባልነግራት ይሻል ኖሮአል? ብሎ አሰበ።

‹‹ቤትሹ ከዚያ በሁዋላ ሆስፒታል. . .››

‹‹አሳክመህ አድነህ ልትገድለን?››

ደርቤ በድንገት ብልጭ አለበት። ንዴት ተናነቀው። ጉሮሮው ሲደርቅ ተሰማው።

‹‹እዚህ ብትገድለኝ ይሻላል›› አለችው፥ ድክም ባለ ድምፅ።

‹‹ጉሮሮውን በትንፋሹ ጠረገና በሚንቀጠቀጥ ከንፈር፥ ‹‹አውሬሽን ፈልጊ! እኛ አውሬዎች አይደለንም። የኔ አላማ፥ እስከ ተቻለኝ ድረስ፥ እንዳንቺ ያሉትን ወደ አብዮቱ ሰፈር መመለስ ነው እንጂ መግደል አይደለም!›› አላት።

‹‹አላምንህም›› አለቸው።

‹‹እመኚኝ!›› አላት። ‹‹እኔን ባታምኚ ለሰፊው ህዝብ የመጣውን አብዮት እመኚ!››

‹‹ከአደጋ ጋር ድብ – ብ – ቆሽ መጫወት ይብቃሽ ብሎኝ ነበር ተሰማ. . .›› አለች፥ እየተዳከመ በሄደ ድምፅ።

‹‹እኔም ስልክ የደወልሽልኝ ጊዜ ከሁላችሁም ጋር መገናኘት አሰብኝ ያልኩሽ ለዚሁ ነበር›› አላት።

የንብ ንግስት ስእል ትዝ አለው። ሂሩት የምትናደፍ ንብ መስላ ታየችው። ከንብ ንግስት ጋር የሚገናኝ ሰራተኛ ንብ ወዲያውኑ እንደሚሞት ድንገት ስለተከሰተለት ጡንቻው ሲወጣጠር ተሰማው።

መዳከምዋን ስላየ ክላሺኑን አንግቶ፥ ሂሩትን አቅፎ ይዞአት ተነሳ። ጥቁር ሀር ነዶ የመሰለው ረጅም ጠጉርዋ ተዘናፍሎ ወርዶ ይታይ ነበር።

ደርቤንና ተሰማን ሁለት የአብዮት ጥበቃ ጉዋዶች ብቻ ተከትለዋቸው ሲወጡ፥ ሌሎች ወደ ሁዋላ ቀሩ። ደርቤ ሂሩትን ተሸክሞ ጨለማውን እየሰነጠቀ

ወደ ቤትዋ ገሰገሰ። ኪዮስኩ ከአቶ ጉልላት ቤት እምብዛም ሩቅ አልነበረም። ደርቤ ላንዳፍታ አቶ ጉልላት ስለቀበሩዋቸው መሳሪያዎች አስታወሰ። ‹‹ነገም ሌላ ቀን ነው›› ብሎ መንገዱን ቀጠለ።

መንገዱ ባዶ ነበር። ንፋሱ ምጥ እንደ ያዛት ሴት ያቃስታል።

በከዋክብት የተከበበች ግማሽ ጨረቃ አይናፋር ልጃገረድ መስላ ብቅ ብላለች። ደርቤ ግን የታዩት፥ ጥቁር ሰማይ ላይ የተፈነጠቁ ቀይ ከዋክብት ነበሩ። ጥቁር ሰማይ - ቀይ ከዋክብት። ድንገት ቆም ብሎ የሂሩትን የልብ ትርታ አዳመጠ።

‹‹ትንፋሽዋ አለ›› አለው ተሰማ ቁርጥ ቁርጥ በሚል ትንፋሹ። ደርቤ መልስ አልሰጠውም። ፍጥነቱን ጨመረ።

እርምጃው ወዴት እንደሚመራው ሊታየው አልቻለም። ልቡ ተንሳፈፈ። ብርድ ቢሆንም አልቦታል። ላቡ በማጅር ግንዱ እየተንቆረቆረ ይወርዳል። ጀርባውን አልቦታል - ሸሚዙ ከጀርባው ጋር እስኪጣበቅ ድረስ። ብብቱን አልቦታል - እና ጡንቻዎቹ ስቃይ ይሰማቸዋል። መንገዱ ወዴት ያመራል? የሚል ጥያቄ ከእርምጃው ከትንፋሹ ጋር - ከልብ ትርታው ጋር - ስልት ይዞ ያስተጋባል - አእምሮ ውስጥ።

ጨረቃዋ ጥልቅ - ጥቁር ጉም ውስጥ። የጠቀሰችው መሰለው - እናቱ አስታወሰ. . . እምአእላፍ በእጁ ዕፎ የሰጠውን ጥቅስ አስታወሰ. . .

Man's dearest possession is life. It is given to him but once, and he must live it so as to feel no torturing regrets for wasted years, never know the burning shame of a mean and petty past; so live that, dying, he might say: all my life all my strength were given to the finest cause in all the world, the fight for the liberation of mankind" . . . ኒኮላይ አስትሮ ቪስኪ. . .

ፈገግ አለ። በፈገግታው ውስጥ ፍኖትን አያት።

ከነአቶ ጉልላት ቤት አጠገብ ሲደርስ እንዳጋጣሚ ሆኖ፥ ‹‹ሙሽራዬ›› የተባለው የሰርግ ዘፈን ከሰፈሩ ፀጥታ በላይ ነግሶ ጨለማውን እየጣሰ ደምቆ ይሰማ ነበር. . .



[illegible]

[illegible]

[illegible] ሰዎች ወደ ፊት እንዲሄዱ በግልጽ ይታያል።

በማንኩሳ ማተሚያ ቤት ታተመ
0113 691833

ዋጋ 71.20 ብር

